# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 138 ጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ወይዘሮ አይናለም ንጉሴ

## ባለፉት ስድስት ወራት ከ225 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ተሰበሰበ

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ከ225 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰብ መቻሉን የፌዴራል ገቢዎች ሚኒስቴር አስታወቀ።

በታክስ ኦዲትና በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም ባልተገባ ኪሳራ በማቀብ፣ የታክስ ተመላሽ በመጠየቅና ሀሰተኛ ደረሰኝ በማቅረብ ሊጭበረበር የነበረ 6 ነጥብ 23 ቢሊዮን ብር ኪሳራ ማስቀረት መቻሉንም አስታውቋል።

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ አይናለም ንጉሴ በትናትናው ዕለት በሰጡት መግለጫ፤ ሚኒስቴሩ በግማሽ በጀት ዓመት 228 ነጥብ 23 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ 225 ነጥብ 93 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የዕቅዱን 99 በመቶ ማሳካት መቻሉን ገልፀዋል።

ይህ ገቢ ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር 54 ነጥብ 62 ቢሊዮን ብር ወይንም የ31 መቶ ብልጫ ማሳየቱንም ወይዘሮ አይናለም አመላክተዋል።

የተሰበሰበው ገቢ በየሴክተሩ ሲታይ ከሀገር ውስጥ ታክስ ገቢ 138 ነጥብ 82 ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን የገለጹት ወይዘሮ አይናለም፤ ከውጪ ንግድ ቀረጥና ታክስ ደግሞ 87 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን አብራርተዋል።

ከዚሁ ገቢ በጥሬ ብር በስድስት ወራት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት 182 ነጥብ 85 ቢሊዮን ብር ፈሰስ መደረጉንም አክለው ገልፀዋል።


ባለፉት ስድስት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## «ኢትዮጵያ በቀጣዩ አመት 13 ነጥብ 5 በመቶ እድገት ታስመዘግባለች»

- ዓለምአቀፉ የገንዘብ ድርጅት

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- እ.አ.አ በ2023 ኢትዮጵያ የ13 ነጥብ 5 በመቶ የኢኮኖሚ እድገት እንደምታስመዘግብ ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም (አይ.ኤም.ኤፍ) አስታወቀ። ቢዝነስ ዴይሊ የተባለው ድረ ገጽ በበኩሉ የኤይ.ኤም.ኤፍን መረጃ ዋቢ በማድረግ በተያዘው የፈረንጆቹ ዓመት ከሰሀራ በታች ካሉ አገራት ኢትዮጵያ እና አንጎላ የኢኮኖሚ የበላይነቱን ከኬንያ እንደሚረከቡ አስነብቧል።

በአንጻሩ በኮቪድ 19፣ በድርቅ፣ በሩሲያ- ዩክሬን ጦርነትና በአገሪቱ በነበረው ምርጫ በችግሮች ምክንያት የኬንያ የኢኮኖሚ እድገት ሁለት ነጥብ አራት በመቶ ይሆናል ተብሎ እንደሚጠበቅም አመልክቷል።

አይኤምኤፍ በዚሁ ትንበያው ዘንድሮ የኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ምርት መጠን 126 ነጥብ ሁለት ቢሊዮን


«ኢትዮጵያ በቀጣዩ ... ወደ ገጽ 12 ዞሯል


## ከኤሌክትሪክ ኃይል ኤክስፖርት 40 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገቢ ተገኝቷል

በሪሁ አረጋ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት 39 ነጥብ 83 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ኤሌክትሪክ ኃይል ለጎረቤት ሀገራት ማቅረብ መቻሉን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ገለፀ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እንደሀገር 772 ሚሊዮን 393 ሺህ 74 ኪሎ ዋት ሰዓት የኤሌክትሪክ ኃይል ኤክስፖርት ለማድረግ ታቅዶ ሲሠራ ቆይቷል። በስድስት ወራት ውስጥ 706 ሚሊየን 90 ሺህ 38 ኪሎ ዋት ሰዓት ኃይል ኤክስፖርት ማድረግ ተችሏል።

ከገቢ አንፃር ሲታይ ደግሞ የኤሌክትሪክ ኃይል ኤክስፖርት በማድረግ ወደ 44 ነጥብ 57 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ዕቅድ ተይዞ እንደነበር እና ማሳካት የተቻለው ወደ 39 ነጥብ 83 ሚሊየን ዶላር መሆኑን ገልጸዋል።


ከኤሌክትሪክ ኃይል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል
Ethiopian Electric Power















## ባለፉት ስድስት ወራት ለ1 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል


ገጽ 4







## በገበያ ስርዓቱ ውስጥ እሴት የማይጨምሩ ተዋንያን ለዋጋ ግሽበቱ መንስኤ ሆነዋል

- የዋጋ ግሽበቱን ለማረጋጋት እስከ ፖሊሲ ማሻሻያ የዘለቀ መፍትሄ ይሻል




ገጽ 3

ዜና

# የእንቦጭ አረምን ለመከላከል ሁሉም ባለድርሻ እንዲተባበር ተጠየቀ



እንቦጭን ለመከላከል ብዙ ጥረት ቢደረግም እስካሁን ማጥፋት አልተቻለም

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- ጣና ሀይቅ ላይ ያለውን የተቀዛቀዘ የእንቦጭ አረምን የመከላከል ሥራ ማነቃቃት ተገቢ በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲረባረቡ የጣና ሀይቅና ሌሎች የውሃ አካላት ጥበቃና ልማት ኤጀንሲ አስታወቀ።

በአማራ ክልል የጣና ሀይቅና ሌሎች የውሃ አካላት ጥበቃና ልማት ኤጀንሲ መጤና ተስፋፊ ዝርያ ክትትልና ቁጥጥር ተወካይ ዳይሬክተር አቶ መዝገቡ ዳኜ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በጣና ሀይቅ ዙሪያ የተከሰተውን እንቦጭ የመከላከል ሥራ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ እየተቀዛቀዘ መጥቷል። በመሆኑም ከመቼውም በበለጠ መልኩ የመከላከል ሥራዎችን ማሳደግና ማጠናከር ይገባል ብለዋል።

አሁን ላይ ያለው የእንቦጭ አረም የመከላከል ተግባር ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር የተቀዛቀዘ ቢሆንም በአካባቢው የሚገኙ አርሶ አደሮችን በማስተባበር አረሙን በማሽኖች የማስወገድ ስራ እየተሰራ እንደሆነ የገለጹት አቶ መዝገቡ፤ አሁን ላይ ያለው መሠረታዊ ችግር ማህበረሰቡም ሆነ አመራሩ አረሙን የመከላከሉ ተግባር እንደተጓዳኝ ስራ መታየቱ ነው ብለዋል።

ሀይቁ የሁላችንም ሀብት በመሆኑ ሁሉም አካል የባለቤትነት ስሜትን በመላበስ በትኩረት ሊሠራበት እንደሚገባ ጠቁመው፤ እነኚህን ችግሮች ለመፍታት ከአመራሩ ጋር ውይይቶች እየተደረጉ እንደሆነ አብራርተዋል።

ከግብርና ስራው ጋር ተያይዞ አርሶአደሩ የበጋ መስኖ እንቅስቃሴ ላይ በመግባቱ ከማህበረሰቡ በኩል ጊዜ ስጡን የሚል እሳቤ ቢኖርም አረሙ ፋታ የማይሰጥ ስለሆነ ጊዜው እየገፋ ሲሄድ የማንወጣበት ችግር ውስጥ ልንገባ እንችላለን ሲሉ ያሳሰቡት አቶ መዝገቡ፤ ስራው በተጠናከረ መልኩ መሰራት እንዳለበት አፅንዖት ሰጥተዋል።

እንደ አቶ መዝገቡ ገለፃ፤ ኤጀንሲው የሚሰራው የማስተባበር ስራ ነው። ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትም በቅንጅት መስራት ያለባቸውን እየሰሩ ናቸው። ለአብነትም የተፈጥሮ ሀብት ስራ ተጀምሯል፤ ለሀገራችን ጣና ትልቁ የተፈጥሮ ሀብት በመሆኑ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራ ከሌሎች የአፈርና ውሃ ጥበቃ ከላይኛው ተፋሰስ ከሚሰሩ ሥራዎች ባልተናነሰ መልኩ ትኩረት መስጠት ይገባል ነው ያሉት።

ካለፈው ዓመት ነሐሴ ወር አጋማሽ ጀምሮ በባህርዳር ከተማ አካባቢ የተከሰተውን የእንቦጭ አረም ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ለማስወገድ የተደረገው ጥረት አበረታች መሆኑን ጠቁመው፤ በቀደሙ ጊዜያት የተሻለ ሥራ በመሰራቱ በሀይቁ ላይ ያለውን አረም መቀነስ ቢቻልም በተያዘው ዓመት ይህ ተግባር ተቀዛቅዟል ብለዋል። መጤ አረሙ ለሀይቁ ሙሉ ለሙሉ ችግር በማይሆንበት ደረጃ እስከሚደርስበት ድረስ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ድጋፍ እንደሚጠይቅ ተናግረው፤ በተለይም የፌዴራል መንግስቱ ድጋፍ እንደቀነሰ አንስተዋል።



የአፈ-ንጉሥ ነሲቡ መስቀሉ ቤት

# ጥንታዊ ቤቶች በግለሰቦች ስር መሆናቸው ለአደጋ እንዲጋለጡ አድርጓል

መክሊት ወንድወሰን

አዲስ አበባ፡- የቅርሶችን ደህንነት ማስጠበቅ የሚያስችሉ ደንቦች ቢፀድቁም ጥንታዊ ቤቶች በግለሰቦች ተይዘው መገኘታቸው ደህንነታቸው ላይ ስጋት መደቀኑን የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ከፍተኛ የቅርስ ጥናት ባለሙያ መምህር መኩብብ ገብረማርያም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ቢሮው በቅርሶች ላይ ያለውን ሥልጣን እንዲጠቀም የሚያስችል ደንብ ከፍትህ ቢሮ ጋር በመሆን አፅድቋል። ይህ ደንብ መፅደቁ የቅርሶችን ደህንነት ለማስጠበቅ ምቹ ሁኔታን ቢፈጥርም በተለይ ጥንታዊ ቤቶች በግለሰቦች እጅ ተይዘው መገኘታቸው የቅርሶች ደህንነት ላይ ስጋት ደቅኗል።

ከዚህ ቀደም ቅርሶችን ለማዳን የሚያስችል ደንብ ባለመኖሩ በካዛንቺስ አካባቢ፣ በልደታ ኮንዶሚኒየም፣ በደጃች ውቤ ሰፈር፣ ባሻ ወልዴ ችሎት አካባቢ በመልሶ ማልማት ሰበብ ብዙ ቤቶች ፈርሰዋል ያሉት ባለሙያው፤ በወቅቱ የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ቤቶቹ እንዳይፈርሱ ጥረት ያደረገ ቢሆንም ሳይሳካ ቀርቷል ብለዋል።

ከለውጡ ወዲህ ቅርሶችን ለማዳን የሚያስችል ደንብ መፈረሙ የቅርሶቹን ደህንነት በማስጠበቅ ከተማዋ ከቱሪዝም ዘርፍ የምታገኘውን ገቢ ማስፋት የሚያስችል ሁኔታ ተፈጥሯል ያሉት መምህር መኩብብ፤ ሆኖም ብዙዎቹ ጥንታዊ ቤቶች በደርግ መንግሥት ተወርሰው አንዱ ቤት እስከ ሰላሳ ለሚጠጉ ግለሰቦች ለመኖሪያነት የተሰጡ በመሆናቸው የቅርሶቹ ደህንነት አደጋ ላይ ወድቋል ሲሉ አብራርተዋል። ቤቶቹን ለማደስም በውስጡ ያሉ ሰዎች አቅሙ እንደማይኖራቸው አያይዘው ገልጸዋል።

ከግለሰቦች ባለፈ ብዙ በቅርስነት የተመዘገቡና ዕድሜ ጠገብ የሆኑ ቤቶች በጸጥታ ተቋማት ጭምር እንደተያዙ አስረድተው፤ ለማሳያነት ያህል የሜጀር ጀኔራል ሙሉጌታ ቡሊ መኖሪያ ቤት፤ ግንፍሌ አካባቢ ያለው የወይዘሮ ትደነቅያለሽ ቤት ታድሰው ለሀገሪቷ ገቢ ማምጣት ሲችሉ በግለሰቦች እጅ ሆነው ለጉዳት እየተዳረጉ ነው ብለዋል።

እንደ መምህር መኩብብ ገለጻ፤ በ2013 ዓ.ም የጥንታዊ ቤቶች ብቻ በቅርስነት ተመዝግበዋል። በምዝገባውም በአዲስ አበባ ከ300 ቤቶች በላይ በቋሚ ቅርስነት መመዝገባቸውንና ለ120 ቤቶች የእውቅና ሰርተፍኬት ተሰጥቷል።



ወይዘሮ መሰረት ወልደ ማርያም

# ኮሚሽኑ ባለፉት ስድስት ወራት 1 ሺህ 544 የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠቱን አስታወቀ

በሪሁ አረጋ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ባለፉት ስድስት ወራት 1ሺህ 544 አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፍቃድ መስጠቱን አስታወቀ። ከተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎችም ከ13 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ማግኘቱን ጠቆሟል።

የአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ወይዘሮ መሠረት ወልደማርያም እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ 2ሺህ አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት አቅዶ ወደ ተግባር የገባ ሲሆን፤ ከሀገርና ከአለም ነባራዊ ችግሮች ጋር ተያይዞ ለ1ሺህ 544 ባለሀብቶች አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አገልግሎት መስጠት ችሏል።

በተመሳሳይ መልኩ በግማሽ ዓመቱ ከኢንቨስትመንት ፈቃድና ፈቃድ ነክ አገልግሎቶች፣ከተለያዩ ድጋፍና ጨረታ 16 ሚሊዮን ለመሰብሰብ አቅዶ 13 ነጥብ 58 ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘት ተችሏል ብለዋል።

ኮሚሽኑ በግማሽ ዓመት ውስጥ 16 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት አቅዶ በተለያዩ ምክንያቶች 13 ነጥብ 58 ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘት መቻሉን ዳይሬክተሯ አብራርተዋል።

የኮንስትራክሽንና የቱሪዝም የስራ መስኮች መቀነስ፤ የውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ የመሬት አቅርቦት አለመኖር፤ የተሰሩ የማስታወቂያ ስራዎች አናሳ በመሆናቸውና ከሌሎች ምክንያቶች ጋር ተያይዞ በታቀደው መሰረት ማሳካት አለመቻሉን ያነሱት ዳይሬክተሯ፤ የሀገር አቀፍ እና የአለም አቀፉ ፖለቲካ ሁኔታ የራሱን አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩንም አንስተዋል።

ኮሚሽኑ በግማሽ ዓመቱ ውስጥ 101 ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ፣ 251 ኢንቨስትመንት ለውጥ ማሻሻያ፣ 889 ኢንቨስትመንት ፈቃድ እድሳትና ለ48 ኢንቨስተሮች ምትክ ኢንቨስትመንት ፈቃድ የመስጠት ሥራ መሰራቱንም ወይዘሮ መሰረተ አመላክተዋል።

በተጨማሪም ኮሚሽኑ በከተማ አስተዳደሩ ስር ለሚገኙ 24 የሚሆኑ አምራቾች የጥሬ እቃ ድጋፍ ለማድረግ አቅዶ እንደነበር አውስተው፣ 55 ለሚሆኑ አምራቾች ድጋፉ መስጠቱን ዳይሬክተሯ ተናግረዋል።

ለአምራቾች የተደረገው የጥሬ እቃ ድጋፍ አፈፃፀም ከፍ ያለበትን ምክንያት ዳይሬክተሯ ሲያብራሩም፣ የሙከራ ምርት ማምረትና ከቀረጥ ነፃ ከሚፈቀድላቸው አምራቾች በተጨማሪ 45ቱ ቀረጥና ታክስ ከፍለው በፍራንኮ ቫሉታ የሚያስገቡ በመሆናቸው ነው ሲሉም ገልጸዋል።

ዜና



## «ኢትዮጵያ ካሏት የቀንድ ከብቶች 95 ከመቶው የዝርያ ማሻሻል ይፈልጋሉ»

- ዶክተር ፍቅሩ ረጋሳ
የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ካሏት አጠቃላይ የቀንድ ከብቶች ውስጥ 95 በመቶው የዝርያ ማሻሻያ ያልተከናወነባቸው በመሆኑ ዝርያ የማሻሻል ስራ ላይ ትኩረት መደረጉን የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ፍቅሩ ረጋሳ አስታወቁ።

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ፍቅሩ ረጋሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ካሉት 71 ሚሊዮን የቀንድ ከብት ውስጥ 95 በመቶው የዝርያ ማሻሻያ ስራ ያስፈልጋቸዋል፤ የዝርያ ማሻሻል ስራውን ስኬታማ ለማድረግ ግብርና ሚኒስቴር በትኩረት እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የእንስሳት ዝርያን ማሻሻል ከተጀመረ 70 ዓመት ማስቆጠሩን የገለጹት ዶክተር ፍቅሩ፤ ይሁንና የቀንድ ከብቶቹ የዝርያ ማሻሻል ተግባሩ በተገቢው መልኩ ባለመከናወኑ እንደአገር ያለው የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶች አቅርቦት ደካማ መሆኑን አስረድተዋል።

የእንስሳት ተዋጽኦን ምርታማነትን ለመጨመር ዝርያን በማሻሻል ረገድ ከዚህ በፊት ያለው አፈጻጸም ደካማ ነው። ስለሆነም ያለፈውን ጊዜ ስራ በሚያሻሽል መልኩ ውጤት ለማምጣት የተደራጀ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንዲሁም በተለያዩ ክልሎችና ማዕከላት የተሻሻሉ ዝርያዎችን የማዳቀል፣ የመኖ ልማትን የማሳደግና የእንስሳቱን ጤና በመጠበቅ ረገድ በመመሪያ የተደገፉ ስራዎች በስፋት እየተከናወኑ መሆኑን አስታውቀዋል።

እንደ ዶክተር ፍቅሩ ገለጻ፣ የተሻሻሉት የእንስሳት ዝርያዎች ከሀገር በቀሎቹ ጋር ሲነጻጸሩ የሚያስገኙት ምርት ከፍተኛ ነው።አንድ ዝርያዋ የተሻሻለች ላም 10 ሀገር በቀል ላሞች የሚሰጡትን ጥቅም የምታስገኝ በመሆኑ ዝርያን ማሻሻል ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

በሌሎች ሀገራት ያለው ልምድ ለስጋና ለወተት ተብለው የሚለዩ የእንስሳት ዝርያዎችና የማሻሻል ስራዎች አሉ። ከተሻሻሉ የላም ዝርያዎች በቀን በአማካኝ 15 ሊትር ወተት ማግኘት ይቻላል። በእኛ ሀገር ባለው ሁኔታ ግን ዝርያቸው ካልተሻሻሉ ላሞች በቀን የሚገኘው የወተት መጠን ከ1 ነጥብ 5 ሊትር አያልፍም ብለዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ የእንስሳት ተዋፅኦ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የስነምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር የስራ እድል በመፍጠር የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ጉልህ ሚና አለው።

የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ከማሟላት ባለፈ ከውጪ የሚገቡ የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶችን በመተካት ረገድ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ የቀንድ ከብት ዝርያ የማሻሻል ሥራዎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳላቸው ይታመናል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ያላት የእንስሳት ሀብት አቅም ከፍተኛ ቢሆንም ዝርያ ማሻሻልና የእንስሳት አያያዝ ላይ ችግሮች በስፋት ይስተዋላሉ። ክፍተቶቹን በአግባቡ በመለየት በዕውቀትና በምርምር በታገዘ መልኩ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል።

ዶክተር ፍቅሩ እንዳስታወቁት፤ የህፃናትን መቀንጨር ለመከላከል፣ እንደሀገር ያለውን የስርዓተ ምግብ ጤናማ ለማድረግ እንዲሁም ገቢ ለማሳደግና ለኢንቨስትመንትም አዋጭ የሆነውን የእንስሳት እርባታ ስራ ውጤታማ ለማድረግ መንግስት ከግሉ ዘርፍ ጋር በትብብር እየሰራ ይገኛል።

የማኅበረሰቡን የእንስሳት ተዋጽኦ ምርት ፍላጎት ለማሟላትና ሀገሪቱን ተጠቃሚ ለማድረግ ዝርያን ማሻሻል ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ በመንግስት ደረጃ ልዩ ትኩረት እንደተሰጠው ተናግረዋል።

በመሆኑም የተሻሻሉ እንስሳትን እንዲሁም በዓሳ እርባታ ዙሪያ መሳተፍ የሚፈልጉ ባለሀብቶች ከግብርና ሚኒስቴር ጋር ተቀራርበው ቢሰሩ ለአገር የሚበጁ ውጤቶችን ማግኘትና ምርታማነትን ማሳደግ ይቻላል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# መጪውን የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ ዝግጅት እየተደረገ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ በመጪው የካቲት ወር ለሚካሄደው 36ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ እና 42ኛው የህብረቱ አስፈፃሚዎች ጉባኤ ዝግጅት እየተደረገ ነው። በትናንትናው እለትም እየተደረጉ ያሉ የዝግጅት ስራዎች ግምገማ ተካሂዷል።

እ.አ.አ ከየካቲት 15 እስከ 19 በአዲስ አበባ የሚካሄደው ይህ ጉባኤ በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ሰላሳ ተቋማትን በአባልነት የያዘ ብሄራዊ የዝግጅት ኮሚቴ ተቋቁሞ ስራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ።

ብሄራዊ ኮሚቴውም በትናንትናው እለት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በተገኙበት የእስካሁን የዝግጅት ስራዎችን ገምግሟል።

በግምገማው ላይ እንደተገለጸው፤ ጉባኤውን በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ የሚያስችሉ የዝግጅት ስራዎች በባለድርሻ ተቋማት እየተከናወኑ መሆኑ ተገልጿል።

በዚህ ወቅት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጉባኤው ኢትዮጵያ ከነበረችበት ፈታኝ ሁኔታ እየወጣች ባለችበት ወቅት የሚካሄድ እንደመሆኑ አዎንታዊ ገፅታ ለመገንባት እድል ይፈጥራል ብለዋል።

የህብረቱን ጉባኤ አምና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማካሄድ መቻሉን አስታውሰው፤ የነበሩ ጉድለቶችን በማሻሻል በተሻለ ስኬት ዘንድሮ ማስተናገድ እንደሚገባ አመላክተዋል። ለስኬቱም ባለድርሻ ተቋማት በተናበበ መልኩ ቅንጅትን በመፍጠር እንዲሰሩ አሳስበዋል።



36ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ በቀጣዩ ወር በአዲስ አበባ ይካሄዳል

የብሄራዊ ኮሚቴው ሰብሳቢ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ አምና የነበረውን አፈፃፀም በመገምገም ወደ ስራ መገባቱን ገልፀዋል።

የጉባኤው ተሳታፊ እንግዶች የሚኖራቸው ቆይታ የተሳካ እንዲሆን ከወዲሁ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች በእቅዱ መሰረት እየተከናወኑ እንደሚገኙም ተናግረዋል።

የጉባኤው መካሄድ ለሀገር ገፅታ ግንባታ እና በኢኮኖሚ ረገድ ከፍ ያለ ጥቅም ሊያስገኝ በሚችል ደረጃ ዝግጅት እየተካሄደ መሆኑን ገልፀዋል።

የዝግጅት ግምገማው የብሄራዊ ኮሚቴው አባል ተቋማት በቀሪ ጊዜያት ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩባቸውን አቅጣጫዎች በማስቀመጥ መጠናቀቁን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል-አቀባይ ጽህፈት ቤት የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

# በገበያ ስርዓቱ ውስጥ እሴት የማይጨምሩ ተዋንያን ለዋጋ ግሽበቱ መንስኤ ሆነዋል

## - የዋጋ ግሽበቱን ለማረጋጋት እስከ ፖሊሲ ማሻሻያ የዘለቀ መፍትሄ ይሻል

**ሳሙኤል ወንደሰን**


አዲስ አበባ፡- በገበያ ስርዓቱ ውስጥ እሴት የማይጨምሩ በርካታ ተዋንያን መኖራቸውን፣ ዘርፉን በበላይነት የሚመሩና የሚከታተሉ ተቋማት በቂ የክትትልና የዕርምት ዕርምጃ አለመውሰዳቸው ለምግብ ዋጋ ግሽበቱ ምክንያት መሆናቸውን የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት አስታወቀ። የዋጋ ግሽበቱን ለማስተካከል እስከፖሊሲ ማሻሻያ የዘለቀ መፍትሄ እንደሚሻም ተጠቁሟል።

"የምግብ ዋጋ ግሽበት መንስኤዎችን እና የወደፊት መፍትኤ አቅጣጫዎችን" በተመለከተ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት አምራቾችን፣ የምግብ እጥረት የሚያጠቃቸው አካባቢዎች እና ከተሞችን ማዕከል በማድረግ ያጠናውን ጥናት በትናንትናው እለት ይፋ አድርጓል።

ጥናቱን ያቀረቡት የኢንስቲትዩቱ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ምርምር ማዕከል ኃላፊ ዶክተር ታደሰ ኩማ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። በአሁኑ ሰዓት በቂ ትኩረትና ፈጣን ዕርምጃ መውሰድ ካልተቻለ ሀገራዊ ስጋት ሆኖ መቀጠሉ አይቀሬ ነው። ለዚህ ደግሞ እስከ ፖሊሲ ማሻሻያ ድረስ መሄድ ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል የተቋማት አደረጃጀትና አሰራር በመፈተሽ የገበያ ስርዓትና በህግ በተቀመጠ አሰራር የሚመሩበት ሁኔታ መፍጠር እና በዘርፉ የሚታየው ህገወጥ እና ምክንያታዊ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ መከታተልና ወቅታዊ የዕርምት ዕርምጃ በተከታታይ በትኩረት መውሰድ እንደሚጠይቅም አስረድተዋል።

የዋጋ ግሽበቱን ለመቅረፍ የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅዶች ተነድፈው ሊተገበሩ ይገባል ያሉት ዶክተር ታደሰ፤ ከአጭር ጊዜ አኳያ በዋጋ ግሽበቱ የህብረተሰብ ከፍተኛ ጉዳት የሚደርስባቸው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ክፍሎችን መታደግ እንዲቻል ከውጪ ገበያ መሰረታዊ



ዶክተር ታደሰ ኩማ



አቶ ታከለ አብዲሳ

የምግብ ፍጆታ ምርቶችን በመግዛት አቅርቦትን ማሻሻልና መደገፍ ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል ብለዋል። በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን የገንዘብ ስርጭትና አስተዳደርም ከኢኮኖሚው እውነተኛ ዕድገት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ ይገባል ሲሉ አክለዋል።

በረጅም ጊዜ ዕቅድም የተለያዩ ሥራዎች ሊከናወኑ እንደሚገባ የጠቀሱት አጥኚው፤ አንዱና ዋንኛው የፖሊሲ ዕርምጃ መሆን የሚገባው የምርት አቅርቦትን ከፍላጎት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ ነው። በተጨማሪም የአነስተኛ አርሶ አደሮችን ምርታማነት በበቂ ሁኔታ ማሳደግ የመካከለኛ እና ከፍተኛ እርሻዎችን ኢንቨስትመንት ትኩረት ተሰጥቶ ማሳደግ ተገቢ ይሆናል ብለዋል።

ኢንስቲትዩቱ ከተሰጠው ተልዕኮ አንጻር የዋጋ ግሽበትን ምንጭ በጥናት የለየ ሲሆን ፤ አራት ዋና ዋና ምክንያቶች ተመላክተዋል ያሉት ደግሞ የኢንስቲትዩቱ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ምርምር ማዕከል ተመራማሪ አቶ ታከለ አብዲሳ ናቸው።

አቶ ታከለ እንዳሉት፤ የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም እና በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምግቦች ጋር በተያያዘ የማምረቻ ወጪዎች መናር የግሽበቱ መጠን እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል። በተመሳሳይ የመንግስት ወጪዎችና የገንዘብ ፍሰት ከዕውነተኛ ኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የተጣጣመ ያለመሆኑ እና የገበያ ስርዓት ለግሽበቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በተለይ በገበያ ስርዓቱ ውስጥ እሴት የማይጨምሩ በርካታ ተዋንያን መኖራቸውን ጠቅሰው፤ ዘርፉን በበላይነት የሚመሩና የሚከታተሉ ተቋማት በቂ የክትትልና የዕርምት ዕርምጃ አለመውሰዳቸው ለምግብ ዋጋ ግሽበቱ ምክንያት ናቸው ሲሉ ጠቅሰዋል።

# ባለፈት ስድስት ወራት ለ1 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያው አጋማሽ ለ1 ነጥብ 4 ሚሊየን ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ። ሚኒስቴሩ የበጀት አመቱን የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ከክልልና ተጠሪ ተቋማት ጋር መገምገም ጀምሯል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን በትናንትናው ዕለት በተከፈተው የሚኒስቴሩ የስድስት ወራት ግምገማ መድረክ ላይ እንደገለጹት፤ ለዜጎች በዘንድሮ በጀት ዓመት ጥራትና አስተማማኝነት ያለው ሥራ ለመፍጠር በትኩረት በመሥራት ላይ ይገኛል።

በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ለአንድ ነጥብ ስምንት ሚሊየን ዜጎች ሥራ ለመፍጠር ግብ ተቀምጦ በተቀናጀ መልኩ ሲሠራበት መቆየቱን ገልጸው፤ ለአንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን ተናግረዋል። ከእነዚህም ውስጥ 70 በመቶው በኢንተርፕራይዝ እና 30 በመቶው በቅጥር ሥራ እንደሆነ አብራርተዋል።

የተፈጠሩ የሥራ ዕድሎች በመሬት ላይ ተግባራዊነታቸውን ለማረጋገጥ በ670 ተቋማት በሱፐርቪዥን ማረጋገጥ መቻሉንም አክለው ገልጸዋል።

ግምገማው እንደሚኒስቴር መስሪያቤቱ የተቀመጡ ዕቅዶችን ለማሳካት ጉልህ ሚና አለው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በፋይናንስ አቅርቦት፣ በገበያ ትስስርና በመሳሰሉ ጉዳዮች የተስተዋሉ ክፍተቶችን እንደመማሪያ በመውሰድ ጠንካራ ጎኖችን በማስፋት ለቀሪው አፈጻጸም በቀጣይ በትኩረት እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

የኦሮሚያ ክልል የሥራ ዕድል ፈጠራ ቢሮ ኃላፊ አቶ ማትዮስ ሰቦቃ የክልሉን ቢሮ የመጀመሪያውን ግማሽ ዓመት ሥራ አፈጻጸም ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ ቢሮው ባለፉት ስድስት ወራት አምስት ቢሊዮን ብር ብድር የማመቻቸት፤ 60 ሺህ ሄክታር መሬት አቅርቦት የማዘጋጀት እና ለአንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዜጎች ስልጠና የመስጠት ሥራ ሠርቷል። በዚህም አስራ ሦስት ቢሊዮን ብር የሚገመት የገበያ ትስስር በመፍጠር ጥራትና ዘላቂነት ያለውን ሥራ ዕድል ለዜጎች ለመፍጠር ሲሠራ ቆይቷል።

በግብርና፣ በእንስሳት ሀብት እና በማዕድን ሥራ ዕድል ለመፍጠር በቀጣይነት ገበያው ውስጥ ቆይተው ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ መሆኑንም አብራርተዋል።

በቀጣይም ውስንነቶችን በመቅረፍ በአካባቢው የሚገኙ እምቅ ሀብቶችን በአግባቡ በመምራት ጥራት ያለውና ዘላቂ ሥራ ዕድል ለመፍጠር በተለይ ከግብርናው በበጋ ስንዴ ላይ በማተኮር ለቀሪው ዕቅድ መሳካት በትኩረት እንደሚሠራ ገልጸዋል ።

አዲስ አበባ የስራ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ፍሰሃ ጥበቡ በበኩላቸው፤ ቢሮው በተያዘው በጀት ዓመት 400ሺህ የስራ እድል ለመፍጠር አቅዶ እየተሰራበት ይገኛል ። እስከ መጀመሪያው ግማሽ ዓመት ድረስ ለ284 ሽህ 988 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል ። የተፈጠረው ስራ እድል 84 በመቶ ቋሚ 16 በመቶው ጊዜያዊ ስራ እድሎች ሲሆን ፤ ከእነዚህም 54 በመቶ ሴቶች እንደሆኑ ገልጸዋል።

ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ 1ነጥብ 8 ቢሊየን ብር ብድር ተመቻችቷል ያሉት ኃላፊው፤ ስራ የሚፈጠርባቸው ዘርፎች አምስት ሲሆኑ በስሩ 130 ንኡስ የስራ ዘርፎች አሉት ብለዋል። ከነዚህም ውስጥ ማኑፋክቸሪንግ፣ አምራች ኢንዱስትሪና ከተማ ግብርና ይገኙበታል ብለዋል። ጠቅለል ተደርጎ ሲታይም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሻለ የስራ እድል መፈጠሩን አያይዘው ገልጸዋል።

## ባለፈት ስድስት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እንደ ሚኒስትሯ ማብራሪያ፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በመንግስት በተቀመጠው የክልሎች የጋራ ገቢ ቀመር መሰረት በግማሽ በጀት ዓመቱ የጋራ ገቢ 22 ነጥብ 89 ቢሊዮን፣ለክልሎችና ለከተማ መስተዳድሮች በግዥው ተይዞ የሚሰበሰብ የተጨማሪ እሴት ታክስና የሁለት በመቶ የግብር ቅድመ ክፍያ ተሰብስቦ የተላለፈ 4 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ በአጠቃላይ 27 ነጥብ 72 ቢሊዮን ብር ለባለቤቶቹ ተላልፈዋል። ልዩነቱ ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ 8 ነጥብ 84 ቢሊዮን ብር ብልጫ አለው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሀሰተኛ የታክስ ደረሰኞችን የሚያሰራጩ ሶስት ተጠርጣሪዎች በህግ ጥላ ስር ሆነው ጉዳያቸው እየታየ መሆኑን ያስረዱት ሚኒስትሯ፤ በግብይት ወቅት የታክስ ደረሰኝ የማይቆርጡ ድርጅቶች ላይ በጥናት በመደገፍ 533 ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር በማዋል በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረጋቸውን አውስተዋል።

በኮንትሮባንድ ስራ ላይ የተሰማሩ 708 ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር ማዋል መቻሉንም ገልፀዋል።

በተመሳሳይ መልኩ የሥነ-ምግባር ግድፈት ያሳዩ 11 የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ከስራ እንዲሰናበቱ መደረጉን የገለጹት ወይዘሮ አይናለም፤ 54 ሰራተኞችን ደግሞ ከደረጃ ዝቅ ከማድረግ እስከ አራት ወር የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት እንደተወሰነባቸው ተናግረዋል።

በገቢ አሰባሰቡ ወቅት የግብር ስወራና ማጭበርበርና ህገወጥ ንግድን ለመከላከል በርካታ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም ችግሩ ሙሉ በሙሉ አለመቀረፉ፣ የሲስተም መቆራረጥና የህግ ተገዥነት በሚፈለገው ደረጃ አለመሆኑ ሚኒስትሯ እንደ ችግር አንስተዋል።

## ከኤሌክትሪክ ኃይል...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ገቢ ለማግኘት ከታቀደው የ11 በመቶና በገንዘብ ሲሰላ ደግሞ የ4 ነጥብ 74 ሚሊየን የዶላር ቅናሽ አሳይቷል ሲሉ ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ለተለያዩ ሀገራት ያደረገው የኤክስፖርት መጠን በተናጠል ሲታይም ወደ ጂቡቲ ኤክስፖርት ከተደረገው ኪሎ ዋት ሰዓት ኃይል የ21 ነጥብ 47 ሚሊየን ዶላር ገቢ አስገኝቷል፤ ወደ ሱዳን ኤክስፖርት ከተደረገውም የ18 ነጥብ 37 ሚሊየን ዶላር ሽያጭ ማግኘት መቻሉንም ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።

ዳይሬክተሩ አክለውም፣ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የጂቡቲን የኃይል ሽያጭ አፈፃፀም ከታቀደው በላይ የ8 በመቶ ጭማሪና በብር ደግሞ የአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶላር ጭማሪ አሳይቷል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ወደ ሱዳን ኤክስፖርት ያደረገችው መጠንም ከታቀደው አንፃር የ25 በመቶ አካባቢ ቅናሽ ማሳየቱንና በገንዘብ ደግሞ የ6 ነጥብ 2 ሚሊየን ዶላር ቅናሽ አሳይቷል ሲሉ ገልፀዋል።

በተቋሙ የኃይል ኤክስፖርት እቅድ መሰረት ያልተላከውም ከተቀባይ ሀገራት አጠቃቀም ጋር የተያያዘ መሆኑን የገለፁት ዳይሬክተሩ፣ የሀገራቱ የኃይል ፍላጎትና አጠቃቀማቸው ከፍ ሲል በእቅድ የተያዘው መጠንም ከፍ ይላል ብለዋል።

እቅድ የሚያዘው ያለፈውን ዓመት አፈፃፀም መነሻ በማድረግና እየጨመር ሊሄድ የሚችል ነገር ሊኖር እንደሚችል ታሳቢ ተደርጎ መሆኑን ዳይሬክተሩ ጠቁመው፤ በታቀደውና በተከናወነው እንዲሁም በተሸጠው መካከል ከአጠቃቀም ጋር በተያያዘ ምክንያት ነው ሲሉ ተናግረዋል።



# ርዕሰ አንቀፅ

## ሁላችንም ለሀገራችን ሰላም እንትጋ!

ሰላም የሁሉ ነገር መሰረት ነው። የግለሰብ ፣ የማኅበረሰብ ፣ የሀገርም ሆነ የዓለም ሕልውና መሰረት ነው። ከሰላም ውጪ ብዙ ነገሮችን ማሰብ የሚቻል አይደለም፤ ከዚህም የተነሳ ጉዳዩ ዓለም አቀፍ አጀንዳ ከሆነ ውሎ አድሯል፤ ስለሰላም ያለው ታማኝነት ካልሆነ በቀር ስለሰላም አያገባኝም የሚልን ፈልጎ ማግኘትም ቀላል አይደለም።

በተለይም ለውይይትና ለድርድር በሮችን በመዝጋት ከሚፈጠሩ ግጭቶች ተጠቃሚ ይኖራል ብሎ ማሰብ ከባድ ነው። የሚያስከፍለውም ዋጋ ያልተገባ ከመሆኑም ባለፈ ለስሌት የሚመች አይደለም። በታሪክ ውስጥም የሚፈጥረው ጥቁር ጠባሳ ከፍ ያለና የትውልዶችን አንገት የሚያስደፋ ልብ ሰባሪ ክስተት እንደሚሆን ይታመናል።

ይህ ክስተት በሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ መልኩን እየቀየረ ደጋግሞ በመከሰት ሕዝባችንን ብዙ ያልተገቡ ዋጋዎች እንዳስከፈለ ይታወቃል። ክስተቱ በራሱ የፈጠረው ሀገራዊ ድህነትና ጉስቁልና የትውልዶችን ልብ እስከ ዛሬ የሰበረና አንገት ያስደፋ ፤ የቀደሙ የደመቁ ታሪኮቻችንን ያደበዘዘ ወይም የደበቀ ነው።

አንዳንድ ፖለቲከኞቻችን ሀገራዊ ለሆነው ሰላም ተገቢውን ዋጋ ለመስጠት በቂ ዝግጅትና ቁርጠኝነት ከማጣታቸው የሚቀዳው ይህ ሀገራዊ ችግራችን፤ እነሱ ከትናንት መማር ባለመቻላቸው ዛሬ ላይ በተመሳሳይ መንገድ ተመሳሳይ ዋጋ እንድንከፍል አስገድደውናል።

እንደ ሀገር በለውጡ ማግስት የነበረው ሀገራዊ ሰላምም ሆነ ለውጡን ተከትሎ በሕዝቡ ውስጥ ተፈጥሮ የነበረው መነቃቃትና የለውጥ ተስፋ እንደ ሀገር ሀገርን ማሻገር የሚያስችል አቅም እንደነበረው ይታመናል። ይህንንም ብዙዎች ተስፋ አድርገው ነበር።

በተለይም የለውጡ ኃይል ለውጡን ካለፉት የለውጥ ዘመናት በተለየ ሁኔታ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ያለሁከትና ደም መፋሰስ ለማስቀጠል የደረሰበት ውሳኔና ለውሳኔው የነበረው ቁርጠኝነት በመላው ሕዝባችን አግኝቶ የነበረው ተቀባይነት የለውጡ ባለቤት በራሱ ለሰላም የቱን ያህል የታመነ እንደነበር ያመላከተ ነው።

በርግጥ ለውጡ እንደታሰበው ሰላማዊ በሆነ መንገድ መቀጠል የሚያስችለውን ተቀባይነት በሕዝቡ ውስጥ ቢያገኝም ፤የሰላሙ መንገድ ወደአሰብነው የጥፋት ጎዳና የሚያደርሰን መንገድ አይደለም በሚሉ ኃይሎች ለፈተና መጋለጡ የማይቀር ሆኖ አልፏል።ተፈትኖም ከብዙ መንገጫገጭ በኋላ ቆሞ መሄድ ችሏል።

ይህ ከሁሉም በላይ የሰላም መንገድ የቱንም ያህል በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ቢያልፍ አሸናፊነቱ ለጥያቄ የሚቀርብ አለመሆኑን በተጨባጭ ያሳየ ነው፤ ከዚህም በላይ ሰላም አያተርፈንም ብለው የሚያስቡ ኃይሎች ሰላም ከተንከባከቡት አትራፊ እንጂ አክሳሪ እንዳልሆነ በተጨባጭ ያስተማረ ነው።

ለዚህ በተለይም በመንግስትና በሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተደረገው የሰላም ስምምነት፤ ሰላም የተገዛበት መርህ ምን ያህል ሰላም ለሚያከብራት ብቻ ሳይሆን በአስቸጋሪ ሰዓት ለሚፈልጋት ጭምር ትልቅ አቅም እንደምትሆን ያመላከተ ነው።

ይህ እውነታ ስለ ሰላም የተዛባ አመለካከት ያላቸውም ሆነ፤ ከሰላም አናተርፍም ብለው ለሚገምቱ እና ሰላምን በማናጋት አትራፊ እንሆናለን ብለው ለሚያስቡ ኃይሎች ተግባራዊ ትምህርት የሰጠ፤ ስለሰላም ካላቸው የተሳሳተ አስተሳሰብ ተመልሰው ሰላምን አክብረው እንዲንቀሳቀሱ የተሻለ ዕድልን የሚፈጥር ጭምር ነው።

በሰላም ውስጥ አሸናፊ የሚሆነው ራሱ ለሰላም የተገዛ አስተሳሰብ ነው። ይህ አስተሳሰብ ደግሞ ከሁሉም በላይ ተጠቃሚ የሚያደርገው ሀገርና ሕዝብን ነው። ከዚህ አንጻር ስለ ሰላም የሚያስብ ኃይል እራሱን ለዚሁ ለተቀደሰ ዓላማ ማስገዛት ይኖርበታል።

ወደ ሰላም የመጡ ኃይሎችም፤ ሰላም በየትኛውም ሁኔታና ጊዜ ተሸናፊ እንደማያደርግ ፤ከዚህ ይልቅ አክብሮና ተንከባክቦ መያዝ ለራስ ፣ ለሀገር እና ለታሪክ ከፍያለ ክብር እንደሚያጎናጽፍ በአግባቡ ተረድተው ለዘላቂ ሰላም በታማኝነት ሊንቀሳቀሱ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## ባለሶስት እግሮቹን ማን 'ሃይ' ይበልልን?

ሜሎዲ ከኪስ ሜዳ

የኑሮ ውድነትን ከሚያባብሱ ነገሮች መካከል የነዳጅ ዋጋ ከፍ ማለት ከግንባር ቀደሞቹ መካከል ይመደባል። ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ውስጥ የነዳጅ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩም የሸቀጣ ሸቀጦችና ሌሎች መሠረታዊ ፍላጎቶች ዋጋ ከፍ እንዲል በማድረግ የህብረተሰቡን ኑሮ ፈትኖታል። በተለይም ለነዳጅ የሚያደርገው ድጎማ መነሳቱ በትራንስፖርት ዘርፉ በነበረው ችግር ላይ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ በመሆኑ የሕዝብ የእሮሮ ምንጭ ከሆነ ውሎ አድሯል

በመሰረቱ ድጎማ መነሳትን አስመልክቶ ባለፈው ወር የትራንስፖርት ዋጋ እንዲጨምር ባይደረግም ድጎማ የተነሳባቸውም ሆነ ድጎማው የቀጠላባቸው የሕዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች እንዳሻቸው የዋጋ ጭማሪ ሲያደርጉ ተስተውሏል፤ ሕጋዊ ጉዞ መስመሮችን አቆራርጠው እየጫኑ የተጓዦችን ገንዘብ ብቻ ሳይሆን በአግባቡ (በተቀመጠ የተሳፋሪ ቁጥር) አገልግሎት የማግኘት መብታቸውን ሲነጠቁ በአደባባይ ታይቷል።

ከነዚህ የሕዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች መካከል ለዛሬ ማየት የፈለኩት ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎችን /ባጃጆችን ጉዳይ ነው። እነዚህ ተሽከርካሪዎች በመዲናዋ የሕዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ በሕግ እውቅና ከተሰጣቸው አመታት አልፈዋል። በተለይም ሌሎች የሕዝብ ትራንስፖርቶች በማይገቡባቸው አካባቢዎች ዋነኛ አገልግሎት ሰጪዎች ናቸው።

የእኛ ሰፈር ምንም እንኳ ለከተማ ቅርበት ያለው (ከስድስት ኪሎ በግምት ከ 1 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ያለ ) ቢሆንም፤ ለታክሲም ሆነ ለአውቶብስ መነሻ ባለመሆኑ (ከላይ እየሞሉ ስለሚመጡ) አብዛኛው የአካባቢው ነዋሪ በባለ ሶስት እግር ተሽከርካሪዎች (ባጃጆችን) ይጠቀማል።

እነዚህ ባጃጆች የነዋሪዎችን ፍላጎት ታሳቢ በማድረግ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል። በነዚህ ጊዜያትም በአብዛኛው አሽከርካሪዎች ከተቀመጡ ታሪፎች ውጪ የራሳቸውን ታሪፍ በማውጣት ሕዝቡን ላልተገባ ወጪ ሲዳርጉት ቆይተዋል፤ አሁንም እየዳረጉት ይገኛሉ። ሕዝቡም እነዚህን ሃይሎች ሀይ የሚልለት በመጥፋቱ የሚጠይቁትን ለመክፈል ተገድዷል።

በእርግጥ መንገዱ ስንፍና ካልያዘ በስተቀር በእግር ከ 15 እስከ 20 ደቂቃ የሚወስድ ነው። ይህንን ተሳቢ አድርጎም የመዲናዋ መንገድ ትራንስፖርት

> እነዚህ ተሽከርካሪዎች ወደ ትራንስፖርት አገልግሎቱ የገቡት የነዳጅ ፍጆታቸው ሆነ የግዥ እና የመለዋወጫ ወጪያቸውም ዝቅተኛ መሆኑ በመንግሥት ደረጃ ተጠንቶና አዋጭ መሆኑ ተረጋግጦ መሆኑ መረሳት ያለበት አይመስለኝም

ቢሮ የጉዞ ታሪፉ ሶስት ብር ፤ የሚጫነውም ተሳፋሪ ሶስት ሰው ብቻ እንዲሆን ወስኗል። በመሰረቱ ታክሲም ቢሆን መንገዱ አጭር በመሆኑ ከዚህ በላይ አያስከፍልም ነበር።

ይሁንና እነዚህን ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች የሚመራው ማህበር በራሱ ፈቃድ የአንድ ጉዞ ታሪፉን አምስት ብር አድርጓል፤ የሚጫኑትም ተሳፋሪ (ትራፊክ እስከሌለ ድረስ) ከአምስት ሰው አንሶ አያውቅም። ችግሩ በአደባባይ የሚከናወን ከመሆኑ አንጻር ህብረተሰቡ ችግሩን ተቀብሎ ለመሄድ ተገድዷል።

ከዚህ የከፋው አሳዛኙና የመንግሥት ያለህ ያስባለው እውነታ፤ እነዚህ አሽከርካሪዎች ከሰሞኑ መንግሥት የነዳጅ ድጎማ አነሳ፤ የመለዋወጫ እቃ ዋጋ ጨመረ ብለው በገዛ ፍቃዳቸው ይጭኑበት የነበረውን ዋጋ ከአምስት ብር ወደ ስምንት ብር ያለ ይሉኝታ በማህበራቸው ስም ከፍ ማድረጋቸው ነው።

1.5 ኪሎ ሜትር ለማይሞላ የጉዞ መስመር በአንድ ጊዜ በአንድ ሰው ሶስት ብር መጨመር ምን ማለት ነው፤ ማህበር የሚባለውስ አካል የጉዞ ታሪፍ የማውጣት የሕግ ባለመብት ያደረገው ማነው?" ይህ የትኛውም ባለጤነኛ አእምሮ ሰው ሊያቀርበው የሚችለው ጥቄያ ነው። መልሱም ቢሆን ለማንም የተሰወረ /የሚሰወር አይሆንም።

እርግጥ ባለሶስት እግሮቹም ሆነ ሌሎቹ በዘርፉ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች የመለዋወጫ እቃዎች ዋጋ ሊጨምር ይችላል። እየሆነ ያለው ግን ይህንን እውነታ ታሳቢ ያደረገ ነው ብሎ አፍን ሞልቶ ለመናገር የሚያስደፍር አይደለም። ይህንን ክፍተት ለመሸፈን በአንድ ሰው ሶስት ብር ጨምሮ የተሳፋሪዎችን ቁጥር ከ3 ወደ አምስት ማሳደግ የግድ ሊሆን አይችልም።

እነዚህ ተሽከርካሪዎች ወደ ትራንስፖርት አገልግሎቱ የገቡት የነዳጅ ፍጆታቸው ሆነ የግዥ እና የመለዋወጫ ወጪያቸውም ዝቅተኛ መሆኑ በመንግሥት ደረጃ ተጠንቶና አዋጭ መሆኑ ተረጋግጦ መሆኑ መረሳት ያለበት አይመስለኝም።

አብዛኛው ሕብረተሰብ የአሽከርካሪዎቹን ሕገወጥ ተግባር ቢቃወመውም፤ ችግሩን ማስቆም የሚያስችል አቅም በማጣቱ የጠየቁትን እየከፈለ መሳፈሩን ቀጥሏል። ቀደም ሲል እንዳልኩት ጉዳዩ በአደባባይ በድፍረት የሚካሄድ በመሆኑም ለሚመለከተው ክፍል አቤት ማለቱ ትርጉም የሰጠውም አይመስልም።

እርግጥ ነው አንዳንድ ጊዜ ትራፊክ ፖሊሶች መዳረሻቸው ላይ ቆመው ትርፍ የጫኑት ሲቀጡ እናስተውላለን፤ ያም ቢሆን ግን ህብረተሰቡ ከትርፍ መጫኑ በላይ የእግር እሳት የሆነበት ያልተገባው የዋጋ ጭማሬ ጉዳይ ነው።

አሽከርካሪዎቹ ከታሪፍ በላይ የሚጠይቁት ገንዘብ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድርበት ነው። በጣም የሚያሳዝነው ጭማሪ ለምን የሚል ፤ ለመብቱ የሚከራከር ከተገኘ «ካልፈለክ ውረድ!» የሚል ምላሽ ነው የሚያጋጥመው። ድንገትም የተባለውንም ከፍሎ የመሄድ እድል ላያገኝ ሁሉ ይችላል (አድማ ይዘው ሁሉም እንዳይጫኑ ሊሊያደርጉት ይችላሉ)።

በአካባቢው እየሆነ ያለው ነገር ፍጹም ሕገወጥ ነው፤ ይህንን የአደባባይ የሕግ ጥሰት የሚመለከተው አካል (የአዲስ አበባ መንገድ እና ትራንስፖርት ባለሥልጣን) ፈጥኖ ሊያርመው ይገባል ። እስካሁንም ለችግሩ ፈጥኖ የመፍትሄ እርምጃ (ሕጋዊ እርምጃ ) አለመውሰዱ የቱን ያህል ከፍ ያለ የአሰራር ክፍተት እንዳለበት ያመላከተ፤ የቱን ያህል የተጣለበትን የሕዝብ ሃላፊነት መወጣት በሚያስችል ቁመና ላይ እንደማይገኝ የጠቆመ ነው።

በዚህ ረገድ ባለሥልጣኑ በአካባቢው የተከሰተውንና ነዋሪውን በከፍተኛ ደረጃ ዋጋ እያስከፈለ ያለውን ያልተገባ የትራንስፖርት አገልግሎት በአግባቡ ተከታትሎ አስፈላጊውን እርምጃ ፈጥኖ ሊወስድ ይገባል። እያንዳንዱ የትራንስፖርት አገልግሎት በተቀመጠለት ታሪፍ መሰረት ተግባራዊ መሆኑንም በተጨባጭ ማረጋገጥ ይኖርበታል ። ይህንን በማድረግ ለተሳፋሪዎች ጥያቄ ፈጥኖ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል።

ለዛሬ አበቃሁ።

# ነፃ ሃሳብ



**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

*ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።*

# የአሜሪካ የአጋማሽ ዘመን ምርጫ አንድምታ

**(ክፍል አንድ)**

የዛሬ መጣጥፌ በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ በማትኮሬ በይደር ያቆየሁት ሃሳብ ነው። የአሜሪካን ነገር በምስራቅ አፍሪካ ቀጣናዊ ጂኦፖለቲካዊ ምህዳር ላይ ያለው ተጽዕኖ ከፍ ያለ ስለሆነ በቅርብ ሆኖ እግር በእግር መከታተልንና መተንተንን ግድ ይላል። በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት የገጠመን ተጽዕኖ የአሜሪካንን ጉዳይ ችላ ልንለው የማይገባ እንደሆነ ያረጋግጣል። የአገራችን የውጭ ጉዳይም ሆነ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎቻችን ሲቀረጹም ዓለመአቀፍ ሁኔታውንና አሰላለፉን ለይምሰልና ለላንቲካ ላይ ላዩን ሳይሆን በጥልቀት መተንተን፣ መተርጎምና መበየን ይጠበቅባቸዋል። በተለይ የአሜሪካና የምዕራባውያን ነባራዊ ሁኔታ በጥልቀት መታየት አለበት የሚል እምነት ስላለኝ ነው የአጋማሽ ዘመን ምርጫውን ላነሳሳ የወደድሁት።

የአሜሪካ መንግሥትና ሕዝብ እንደ ሰው ሲወከል አጎት ሳም በመባል ይታወቃል:: ስረወ - ሀረጉ US የሚለው ምህጻረ ቃል ነው:: United States US የተሰኘውን የተለመደ የወል ስም (Uncle Sam) በሚል መጠቀም የተጀመረው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደሆነ ድርሳናት ያትታሉ:: " አጎታችንን ! ? " እንዲህ ካስተዋወቅኋችሁ ሌላ ተያያዥ ጉዳይ ላንሳ። በብዛት ከአሉታዊ ብያኔና አንድምታ/ pejorative ጋር ይያያዛል እንጂ፤ ከዩናይት ስቴትስ ሰሜናዊ ግዛት የሆኑ አሜሪካውያንና ሌሎች ያንኪስ yankees በሚል ቅፅልም ይጠራሉ ::"

Yankees go home ! " አሜሪካ በሃይልና በመንፈስ ከያዘቻቸው አገራት ከካናዳ ፣ ምስራቅ ጀርመን ፣ ቬትናም ፣ ጃፓንና ሌሎች አገራትን፤ ለቃ እንድትወጣ የሚጠይቅ መፈክር ነው:: የእኛዎቹ የ60ዎቹ ትውልድ መፈክሩን በአደባባይ ማስተጋባቱ ያስታውሷል:: በዓለምአቀፍ ግንኙነት፣ በዲፕሎማሲያዊ ማህበረሰብ ኮሪደርና በብዙኃን መገናኛ ደጋግመን የምንሰማው የጨረተ cliche የሚመስል ግን አሁንም ስራ ላይ ያለ አባባል አለ::

"አሜሪካ ስታነጥስ የተቀረው ዓለም ጉፋን ይይዘዋል:: "/When the U.S. sneezes, the world catches a cold./ይህን ምሳሌዊ አነጋገር ለመጀመሪያ ጊዜ በ1813 ዓ.ም የኦስትሪያ ንጉሳዊ ቤተሰብ አባል የነበረው ልዑል ክሌመንስ ዌንዜል ሲጠቀመው፤ "ፈረንሳይ ስታነጥስ የተቀረው አውሮፓ ጉፋን ይይዘዋል:: " በሚል ነበር :: በጊዜው የናፓሊዎን ፈረንሳይ ልዕለ ኃያል ነበረችና::

በሂደት የአሜሪካ ልዕለ ኃይልነት እየገነነ ሲመጣ "ፈረንሳይ " የሚለው ፤ "በአሜሪካ " "አውሮፓ" የሚለው ደግሞ ፤በ " ዓለም " ተተክቶ ፤ " አሜሪካ ስታነጥስ የተቀረው ዓለም ጉፋን ይያዛል " ሆነ:: ከቀደመው የልዑል ዌንዜል አባባል ይልቅ ይህ አባባል ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ ተናኘ:: አሁን አሁን ደግሞ በ" ቻይና "ይተካ ይሆን የሚለውን እድሜ ሰጥቶን አብረን የምናይ ይሆናል።

ለመግቢያ ያህል ይሄን ካልሁ ወደ ተነሳሁበት ነጥብ ላምራ። አይደለም የአሜሪካ የአጋማሽ ዘመን ምርጫ ይቅርና የአሜሪካ ግምጃ ቤት ሚኒስትር ጃኔት የለን ስለ ኢኮኖሚው አንዲት ቃል ጣል ቢያደርጉ፤ አገራችንን ጨምሮ በመላው ዓለም ኢኮኖሚ ላይ በአዎንታ ወይም በአሉታ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀርም። ስለአሜሪካ ምርጫ የምፈተፍተው በአንድም በሌላ በኩልም ጥላው ማጥላቱ ስለማይቀር ነው። የዛን ሰሞኑ ምርጫም ደረጃው ይለያይ እንጂ በእኛም ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀርም።

የአሜሪካ የአጋማሽ ዘመን ምርጫ ከአሜሪካ እንጥሻዎች እንደ አንዱ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ሪፐብሊካኖች እንደ ፎከሩት፤ አሜሪካንን በቀይ ማዕበል የሚያጥለቀልቁ ከሆነ ማለትም የታችኛውን ምክር ቤት ወይም ኮንግረሱን፤ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቱን ወይም ሴኔቱን ጥርግርግ አድርገው የሚያሸንፉ ከሆነ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውም ሆነ፤ የዴሞክራቶች ፖሊሲዎች ሊቀለበሱ ካልሆነም ሊስተጓጎሉ ይችላሉ። አሜሪካ ለዩክሬ የምታደርገው ድጋፍ ሊቀዛቀዝ ፤በአንጻሩ ከፕሬዚዳንት ፑቲን ጋር የነበረው የተካረረ ፖሊሲ ሊለዝብና ወይይት ሊጀመር፤ ለዩክሬን በገፍ ጦር መሳሪያ ማቅረቡና የዶላር ድጋፉ ጋብ ብሎ ለድርድር በሯን እንድትከፍት ግፊት ሊደረግባት ይችላል።

ይሄን ተከትሎ የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃል ኪዳን ድርጅት(ኔቶ) አባል አገራትና የአውሮፓ ሕብረት፤ በዩክሬንና በራሽያ ላይ ላይ የሚያራምዱት ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ ባይቀየር እንኳ በተወሰነ ደረጃ ለዘብ ማለቱ አይቀርም ይላሉ ተንታኞች ፤ ዴሞክራቶችን ሃሳብ ላይ የጣላቸው ሌላው አብይ ጉዳይ የ2020 ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ውጤትን የማይቀበሉና የቀድሞውን ፕሬዚዳንት ቡራኬ ያገኙ እጬዎች መበራከት ነው። እነዚህ እጬዎች አሸንፈው በኮንግረሱም ሆነ በሴኔቱ መቀመጫ የሚያገኙ ከሆነ የዴሞክራሲ ጉዳይ ጥያቄ ላይ ይወድቃል።

አሜሪካ የምትመጻደቅበትና እንደ አንድ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እሴት የምታየው ዴሞክራሲ አጣብቂኝ ውስጥ ይገባል። ከ2ኛው የዓለም ጦርነት ማግስት ጀምሮ እንደ የመንግሥታቱ ድርጅት UN፣ የዓለም ባንክ፣ ዓለምአቀፉ የገንዘብ ተቋም፤ ያሉ ተቋማትን በመመስረት ከ75 ዓመታት በላይ ሉላዊነትን GLOBALIZATION እያቀነቀነች ቤቷ ግን በታሪኳ ታይቶ በማይታወቅ ክፍፍልና ልዩነት እየተናጠ ነው። ከአገሬው ግማሽ ያህል የሚሆነው መራጭ የ2020 ምርጫ ተጭበርብሯል ብሎ የሚያምንና የምትመጻደቅበትን ዴሞክራሲ ጥያቄ ላይ ጥሏል። የሪፐብሊካንና የዴሞክራት አባላት ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ልዩነታቸው ተካሯል። አይን ለአይን ለመተያየት እንኳ አቅቷቸዋል።

ቀኝ አክራሪዎችና ክሪስቲያኖች በህልውናችን ላይ አደጋ ተደቅኖብናል በማለት አሜሪካ ትቅደም! የሚል ሕዝበኛ populist የሆኑትን ትራምፕ እንደ መሲህ ማየት በሪፐብሊካን ፓርቲ ውስጥ ደግሞ ክፍፍል እየፈጠሩ ነው። አሜሪካ እንዲህ በልዩነትና በክፍፍል እየተናጠች ሳለ ዛሬም የዓለም ፖሊስና የዴሞክራሲ ፊደል አስቆጣሪ ለመሆን፤ የምታደርገውን ጥረት የታዘቡ ፤ የራሷ አሮባት የሰው ታማስላለች በማለት በሀሰተኛ መረጃና በሴራ ፖለቲካ ዜጎቿ መከፋፈላቸውን በአብነት ያነሳሉ። ለነገሩ የዴሞክራሲ ነገር አበቃለት የተባለው፤ ፕሬዚዳንት ትራምፕና ወደ 75 ሚሊዮን የሚጠጉ ደጋፊዎቻቸው የ2020 ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ውጤት አልቀበልም ያሉ ዕለት ነው።

ለነገሩ አሜሪካ ከብሔራዊ ጥቅሟ የምታስቀድመው ነገር እንደሌለና ወጥ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እንደሌላት ብዙዎች ይተቻሉ። በነገራችን ቀይ ቀለም የሪፐብሊካን መለያ ሲሆን ሰማያዊ ደግሞ የዴሞክራት ነው። ቀዩ ማዕበል አሜሪካን ቢያጥለቀልቅ ኖሮ፤ ከፍተኛ በጀት የተያዘለት የፕሬዚዳንት ባይደን የአየር ንብረት ለውጥ እና "አሜሪካ ተመለሰች!"/America is back/የተባለለት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎች ጥያቄ ይነሳባቸዋል። በአሜሪካ የአጋማሽ ዘመን ምርጫ ኋይታውስን በያዘው ፕሬዚዳንትና በፓርቲው ላይ እንደሚሰጥ ሕዝበ ውሳኔ ተደርጎ ይወሰዳል።

ኋይታውስን የያዘው ፓርቲ በገባው ቃል መሰረት ኃላፊነቱን ካልተወጣ በኮንግረስና በሴኔቱ የያዛቸውን መቀመጫዎች ሊያጣ ይችላል ተብሎ እንደተሰጋው ኮንግረሱን ለሪፐብሊካኖች አስረክቧል። የዴሞክራት ፓርቲ ደግሞ በጠባብ ልዩነት ሴኔቱን የተቆጣጠረ ሲሆን በጆርጂያ ሕዳር 25 ቀን፣2022 ዓም በተካሄደ ድጋሚ ምርጫ፣ ዴሞክራቱ ራፋየል ዋርኖክ ሪፐብሊካኑን ሔርሻል ወከር በጠባብ ልዩነት በማሸነፍ ዴሞክራቶች ሴኔቱን በ51 መቀመጫ ሲያሸንፉ፤ ሪፐብሊካኖች ደግሞ 49 መቀመጫ ዎችን በመያዝ በሴኔቱ የነበራቸውን ተቀራራቢ ድምጽ አጥተዋል።

ካለፈው ነሐሴ ወዲህ የፕሬዚዳንት ባይደን ተቀባይነት ከ50 በመቶ በመውረዱ፤ በኮንግረሱም ሆነ በሰኔቱ፤ መቀመጫዎችን ልናጣ እንችላለን ብለው ሰግተው የነበር ቢሆንም ውጤቱ የተፈራውን ያህል ሳይሆን ቀርቷል። በርከት ያሉ መቀመጫዎችን ቢያጡ ኖሮ ለሥልጣን ያበቋቸውን ፖሊሲዎች ማስፈጸም ይቸገሩ ነበር በ2024 ዓም በሚካሄደው ምርጫም ባይደንም ሆነ ፓርቲያቸው የመመረጥ ዕድሉን አጣብቂኝ ውስጥ ሊጥለው ይችል ነበር።

በአንጻሩ ዴሞክራቶች በሁለቱ ምክር ቤቶች አብላጫ መቀመጫቸውን ቢያጡ ኖሮ፤ ፕሬዚዳንት ባይደን፤ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል የተለሙትን ዕቅድ፤ በመንግሥት የሚደገፍ የጤና መርሀ ግብራቸውን፤ ጽንስ የማቋረጥ መብትን ፤ የጠመንጃ መያዝ መብትን ለመቆጣጠር የሚያግዙ መመሪያዎችን አውጥቶ ለመተግበር ይችሉ ነበር።

ሪፐብሊካኖች ኮንግረሱን በአብላጫ ድምጽ ስለተቆጣጠሩ የዴሞክራቶች ዕቅዶች ሳንካ ይገጥማቸዋል ተብሎ ተሰግቷል። በጥር 6 ቀን፣ 2021 ዓ.ም የቀድሞው ፕሬዚዳንት ትራምፕ የምርጫ ውጤቱን አልቀበልም ባለማለታቸው፤ ደጋፊዎቻቸው በወቅቱ የምርጫ ውጤቱን ለማጽደቅ በካፒቶል ሒል ተሰብስበው የነበሩ፤ የምክር ቤት አባላትን እንዲያስቆሙ በጠየቁት መሠረት ደጋፊዎቻቸው እንደ ዴሞክራሲ ቤተመቅደስ የሚቆጠረውን፤ ካፒቶል ሒልን በኃይል ጥሰው በመግባት ሒደቱን ከማስተጓጎላቸው ባሻገር የጸጥታ ሰዎች ላይ ጉዳት አድርሰዋል።

ዴሞክራቶችና ሪፐብሊካኖች ይሄ ጥቃት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱና በሕገ መንግሥቱ ላይ የተሰነዘረ ነው በሚል፤ አጣሪ ኮሚቴ አዋቅረው ምርመራ ከጀመሩ ሰነባብተዋል። ምርመራውን እስከ ታህሳስ መጨረሻ እናጠናንቃለን ቢሉም፤ በዚህ የአጋማሽ ዘመን ምርጫ ሪፐብሊካኖች በተለይ በኮንግረሱ አብላጫ መቀመጫ ስላገኙ ይሄ ምርመራ ምዕራፍ ሳያገኝ ይቋረጣል። ትራምፕም ከተጠያቂነት ያመልጣሉ ብለው ሰግተዋል።

በዚህ ምትክ የጆ ባይደን ልጅ ሀንተር ከቻይና ጋር ያልተገባ የስራ ውል ተፈራርሟል እየተባለ ስለሚቀርብበት ክስ፤ የአሜሪካ ወታደሮች ከአፍጋኒስታን በጥድፊያ ተጠራርገው ሲወጡ ስለተፈጠረው ቀውስ እናጣራለን ብለው ምርመራ ሊጀምሩ ይችላሉ እንደተባለው እንቅስቃሴ ጀምረዋል።

ፕሬዚዳንት ባይደን አዳዲስ ተሿሚዎችን በተለይ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሹመት የምክር ቤቱን ይሁንታ ማግኘት ይቸገራሉ።

የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያቸውም በተለይ ለዩክሬን የሚያደርጉት ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ አጣብቂኝ ላይ ሊወድቅ ይችላል። ፕሬዚዳንቱ ይህ ሁሉ ሲሆን እጃቸውን አጣጥፈው አይቀመጡም የአስፈጻሚነትና ድምጽን በድምጽ የመሻር መብታቸውን በመጠቀም ፤ሪፐብሊካኖች በተለይ ስለጽንስ ማቋረጥ፣ ስለስደተኞችና ስለታክስ የሚያቀርቧቸው ሕጎች ቢጸድቁም ስራ ላይ እንዳይውሉ ማገድ ይችላሉ።

የአጋማሽ ዘመን ምርጫው በ2024 ዓ.ም የሪፐብሊካን የፕሬዚዳንታዊ እጩ ማን ሊሆን እንደሚችልም ያመላክታል ተብሎ ይጠበቅ የነበር ቢሆንም ትራምፕ አበክረው እጩነታቸውን ይፋ አድርገዋል። በዚህ የአጋማሽ ዘመን ምርጫ ፕሬዚዳንቱ የደገፋቸው የሪፐብሊካን እጬዎች ማሸነፍ ካልቻሉ ፓርቲው ትራምፕ እጩ ሆነው እንዲቀርቡ ላይደግፋቸው ይችላል። ይልቅ የፍሎሪዳ ገዥ ሮን ዲሳንቲስ በዚህ ምርጫ በ20 በመቶ አብላጫ ስለአሸነፉ የ2024 የሪፐብሊካን ፕሬዚዳንታዊ እጩ ተፎካካሪ ሊሆኑ ይችላሉ።

ዴሞክራቶች እንደፈሩት የአጋማሽ ዘመን ምርጫው ከኮንግረስም ሆነ ከሴኔት መቀመጫዎች ብዙ ስላላሰጣቸው እፎይ ያሉ ይመስላል። ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ ለበርካታ ቀናት የኔቫዳና አሪዞና ድምጽ ቆጠራ ውጤት ባይታወቅም የጆርጂያ ግን አሸናፊውን መለየት ባለመቻሉ በ2ኛ ዙር ምርጫ እንዲለይ ተወስኖ ድምጽ መስጠት ተጀምሯል።

የእነዚህ ምርጫ ክልሎች ውጤት ሲታወቅ ሪፐብሊካኖች ሴኔቱንም ሆነ ኮንግረሱን በጠባብ ልዩነት ሊቆጣጠሩ ይችላሉ ቢባልም ዴሞክራቶችን አላስጨነቀም። እንዲያውም ያሸነፉ ያህል ነው ውጤቱን ያከበሩት። በምርጫው ማግስት ፕሬዚዳንት ባይደን ከነጩ ቤተ መንግሥት በሰጡት መግለጫ ዴሞክራሲ አሸንፏል። ብለዋል።

የ2020 ምርጫ ውጤት የማይቀበሉና በፕሬዚዳንት ትራምፕን ይደገፉ የነበሩ አምስት እጬዎች በመሸነፋቸውና ሪፐብሊካኖች የተሰጋውን ያህል ስላልቀናቸው ነው እንግዲህ ባይደን ዴሞክራሲ አሸንፏል ያሉት። ዴሞክራቶችና የእነሱ ወገን የሆኑ ሚዲያዎች "የምርጫ ከሀዲዎች" (election deniers) የትራምፕ ታማኝ ደጋፊዎች፤ በኮንግረስም ሆነ በሴኔቱ ሊያሸንፉ ይችላል በሚል ዴሞክራቶችና ሉላውያን ማለትም ምዕራባውያንና የአውሮፓ ሕብረት፤ ምጥ ተይዘው ነው የሰነበቱት። ለነገሩ ምጡ ቀለል ያለ ቢመስልም ገና አልተገላገሉም።

የቀድሞው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ዳግም ወደ ሥልጣን የመመለስን ዕድል ያሰጋቸው እነ ኔቶ፣ የአውሮፓ ሕብረት፤ የመንግሥታቱ ድርጅት፣ የዓለም ባንክ፣ ዓለምአቀፉ የገንዘብ ተቋምና በአጠቃላይ ሉላዊነት (Globalization) የሚያቀነቅኑትን ነው። ባለፈው ወር ለንባብ የበቃው The economist መጽሔት በምርጫ ውጤቱ አውሮፓና አጋሮቿ እፎይ አሉ በማለት ነው ሰሞነኛውን ጭንቅ የገለጸው። በቀጣዩ የመጣጥፌ የመጨረሻ ክፍል የምርጫ ውጤቱን አንድምታ ሰፋ አድርጌ የምሄድበት ይሆናል።

ሻሎም !

አሜን።

# ወቅታዊ

# “ኢትዮጵያም የራሷን ችግር በራሷ እንድትፈታ በማድረጉ በኩል ዲያስፖራው የተወጣው ሚና በጣም ትልቅ ነው”

- አቶ ወንደሰን ግርማ

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር

እፀገነት አክሊሉ

በመላው ዓለም ያሉ ኢትዮጵያውያን ከአገር የመውጣታቸው ሚስጢር የተለያየ ቢሆንም ሁሉም ግን በልባቸው ስለ አገራቸው ያላቸው ክብርና ናፍቆት ከፍተኛ ነው። ይህን አገርን የመውደድ ፍቅር የሚወጡት ለአገራቸው በሚያደርጉት ጉልህ አስተዋጽኦ ጭምር ነው። በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካውና በማህበራዊ መስኩ በመሳተፍ አገራቸውን እያገለገሉ ያሉት ጥቂት አይደሉም። የአገር ዲፕሎማት ሆኖ በመቆም፣ በህጋዊ መንገድ ገንዘብ ወደ አገር ቤት በመላክ፣ በኢንቨስትመንት ዘርፉ በመሰማራት ለአገራቸው አለኝታ መሆናቸውን ደጋግመው አስመስክረዋል። አሁንም ተጠናክሮ እየቀጠለ ያለው ይሄው ነው።

ዲያስፖራው በተለይም ባለፉት አራት ዓመታት አገሩን ከምን ጊዜውም በላይ ያሰበበት ወቅት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ለዚህ ማሳያው ደግሞ ከረጅም ዓመታት የባእድ አገር ቆይታ በኋላ ወደ አገራቸው የገቡ ሰዎች ቁጥር መብዛት አንዱ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ባለፉት ሁለት ዓመታት አገር ከውስጥና ከውጭ በተወጠረችበት ጊዜ በገንዘብ፣ በሃሳብ፣ በእውቀት እንዲሁም የሚኖሩባቸውን አገራት ባለሥልጣናት የአገራችንን እውነት እንዲረዱ በማድረግ (በዲፕሎማሲ)፣ በአገራችን ላይ ጫና ሲደረግም አደባባይ ወጥተው በመቃወም በኩል የተወጡት ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

የክፉ ቀን ወዳጅ ደግሞ በማንኛውም መልኩ በተለይም ችግር ሲያልፍ ማመስገን ኢትዮጵያዊ ባህላችን ነውና በችግራችን ወቅት ከጎናችን የነበሩ፣ እናት አገራቸውን አስቀድመው አደባባይ የዋሉ፣ ሌሎችን ያስተባበሩ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ያሏቸውን እድሎች ተጠቅመው በጦርነቱ ምክንያት ችግር ውስጥ የገባውን ወገናቸውን አለሁልህ በማለት ላይ ታች ያሉ ሊመሰገኑ እነሆ ቀኑ ደረሰ።

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት አብረውት ከፍ ዝቅ ሲሉ የነበሩ ለአገራቸው ከፍተኛ ድጋፍ ያደረጉትን የዲያስፖራ አባላትን ዛሬ የሚያመሰግኑበት ቀን ነው። “ኢትዮጵያ” ታመሰግናችኋለች ፤ ስራችሁም እውቅና ይገባዋል በማለት ተዘጋጅቷል። በዚህና በተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር ከሆኑት ከአቶ ወንደሰን ግርማ ጋር ቆይታ አድርገናል።

**አዲስ ዘመን ፡- እስከ አሁን ዲያስፖራው አገሩን ለመገንባት ያበረከተው አስተዋጽኦ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ወንደሰን፡-** ሁሉም አገራት እንደሚያደርጉት ዲያስፖራው አንድ የእድገት አማራጭ ተደርጎ ነው የሚወሰደው። በዚህም የእኛ ዲያስፖራዎች እያበረከቱ ያለው አስተዋጽኦ እጅግ በጣም በርካታ ነው። በተለይም ያላቸውን እውቀት፣ ክህሎት፣ ቴክኖሎጂ እንዲሁም የገንዘብ አቅም በማቀናጀትና ወደአገር ቤት እንዲሸጋገር በማስቻል ነው። በሌላ በኩልም ዲያስፖራው በንግድ፣ በቱሪዝም ዘርፎች ላይ በመሰማራት ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ ነው።

የውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ቤት ይልካሉ፤ በተለያዩ በጎ አድራጎት ስራዎች ላይ የነቃ ተሳትፎን ያደርጋሉ፤ አገራዊ ጥሪዎችን በመቀበልና ፕሮጀክቶች ከፍጻሜያቸው እንዲደርሱ ድጋፋቸውን እያበረከቱም ነው። በኢትዮጵያ ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ ዲያስፖራውን ለመሳተፍ የሁለተኛው አስር ዓመት የዲያስፖራ ፖሊሲ ሰነድ ወጥቷል። በዚህ አማካይነት የተለያዩ ስራዎች እየተተገበሩ ከመሆኑም በላይ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተለያዩ የስራ ዘርፎች ላይ የዲያስፖራው ጉዳይ ከፍ ያለ ትኩረት ተሰጥቶት ሲሰራበት ቆይቷል። ባለፉት አራት ዓመታት ደግሞ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶታል። በተለይም የለውጡ መንግሥት ወደ አመራር ከመጣ በኋላ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሜሪካ፣ አውሮፓ ፣መካከለኛው ምስራቅና አፍሪካ ላይ ከሚገኙ ዲያስፖራዎች ጋር ውይይት አድርገዋል። ይህ ውይይት “ ግንቡን እናፍርስ ድልድዩን እንገንባ“ የሚል ነበር ፤ በዚህም ዲያስፖራው ከአገሩ ጋር ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር ለአገር ቤት የሚያስፈልጉትን ድጋፎች እንዲያደርግ በፊት የነበሩት ልዩነቶች እንዲወገዱ አስችሏል ማለት ይቻላል። ከዚህ ጋር ተያይዞም ብዙ ለውጦች መጥተዋል።

በሌላ በኩልም አሁን አገራችን እየተከተለች ያለው ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ በመሆኑ ሚስዮኖቻችን ለዲያስፖራው እንደቤታቸው ሆነው በማገልገል ለሚፈልጓቸው ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ ተሳትፎዎች የሚገናኙባቸው ቦታዎች ሆነዋል። ይህ ደግሞ ግንኙነቱ የተጠናከረ እንዲሆን እያደረገውም ይገኛል።

በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት ዲያስፖራው የአገሩን ገጽታ በመገንባት፣ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት (ፐብሊክ ዲፕሎማሲው) ላይ ተሳትፎ በማድረግ ዲጅታል ዲፕሎማሲ ጋር በተያያዘ የተወጣው ሚና ዲያስፖራው ከአገሩ ጋር ያለውን ቁርኝት ቁልጭ አድርጎ ያሳየ ነው።

በሰሜኑ ኢትዮጵያ ከተፈጠረው ጦርነት ጋር በተያያዘ አገራችን ላይ ሲፈጠሩ የነበሩ የውጭ ጫናዎችን በመመከት በኩል ያሳዩት ተሳትፎ ቀላል አልነበረም። በዓለም አቀፍ ደረጃም ከ 40 በላይ በሚሆኑ ትልልቅ ከተሞች ከ 70 ያላነሱ ሰላማዊ ሰልፎችን በማድረግ ለአገራቸው ያላቸውን አጋርነት አሳይተዋል።

ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጋር በተያያዘም አፍሪካውያን የራሳቸውን ችግር በራሳቸው መፍታት ይችላሉ ብለው ድርድሩንም ከተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ወደ አፍሪካ ህብረት በማምጣት ተግባራዊ እንዲሆን አስችለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም የአቋም መግለጫዎችን በማዘጋጀት ኢትዮጵያ ላይ ጫና ሊያሳድሩ ያሉትን እንዲያውቁት በማስቻል የማሳመንና የመቀስቀስ (የሎቢና አድቮከሲ) ስራዎችን በመስራት የሎቢ ድርጅቶችን በመቅጠር የኢትዮጵያ እውነትን ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እንዲረዳው ያልተገባው ጫና ደግሞ እንዲለዝብ ዲያስፖራው እጅግ በጣም በርካታ እንቅስቃሴዎችን ነው ያደረገው። ይህም ዲያስፖራው ከአገሩ ጋር ያለው ትስስር ጠንካራ እንዲሆን ለአገሩ ሊያስገኛቸው የሚችላቸውን እሴቶች ምን ያህል ሰፊ እንደሆኑም ያመላከቱ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ዲያስፖራው በኢንቨስትመንት እያደረገ ያለው አስተዋጽኦ ፤ በተለይ በሕጋዊ መንገድ ገንዘብ ወደ አገር በመላክ ኢኮኖሚውን በመደገፍ ያለው ሚና እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ወንደሰን፡-** ዲያስፖራው ካከናወነው የሕዝብ ለሕዝብ ዲፕሎማሲ (ፐብሊክ ዲፕሎማሲ) ባልተናነሰ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብን አሰባስበው ወደ አገር ቤት በመላክ አጋርነቱን አሳይቷል። ባለፉት አራት ዓመታት ከ ሶስት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር በላይ የገንዘብና የአይነት ድጋፎች ተደርገዋል። ለምሳሌ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ፣ በጦርነቱ ለተፈናቀሉና ለተጎዱ ወገኖች ድጋፍና መልሶ ማቋቋሚያ በማድረግ አጋርነታቸውን ያሳዩ ሲሆን ፤ እዚህ ላይ በተለይም ተፈናቃዮችን መልሶ ለማቋቋም ሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በዓይነትና በገንዘብ የመጣው ድጋፍ ተጠቃሽ ነው።

ሌላው ባለፉት አራት ዓመታት በሕጋዊ መንገድ ገንዘብ ወደ አገር በመላክ በኩልም ከ 15 ቢሊዮን ዶላር በላይ ወደ አገር ቤት ተልኳል። ይህ ገንዘብ ለብዙዎች የስራ እድል ለመፍጠር ምክንያት ሆኗል። በጠቅላላው ዲያስፖራው ያደረጋቸው ድጋፎች ሰፊ ከመሆናቸው አንጻር የተገለጹት በጣም ጥቂቶቹ ናቸው።

በየዓመቱ እቅድ አቅደን ከምንለከው አንዱና ግንባር ቀደሙ በሕጋዊ መንገድ ወደ አገር የሚላክን ዶላር ፍሰትን ማሳደግ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘም ሁለት አይነት ስራዎችን እናከናውናለን። አንዱ በአገር ቤት ፍሰቱን ለማሳደግ የሚያስችሉ ምቹና ቀልጣፋ አገልግሎቶች እንዲሁም ተመጣጣኝ ክፍያዎችን የሚጠይቁ ሥርዓቶች እንዲዘረጉ ከፋይናንስ ተቋማት ጋር መስራት ሲሆን ሁለተኛው ሚሲዮኖቻችን ዲያስፖራው ዶላርን ወደአገር ቤት እንዲልክ የሚያበረታቱ ስራዎችን እንዲሰሩ ማስቻል ነው። በሁለቱ በኩል ጠንካራ ስራ እየሰራን ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሶስት ሚሊዮን የማያንስ ዲያስፖራ ያለን አገር ነን። ይህ አቅም ደግሞ ቀላል አይደለም። ባለፉት አራት ዓመታትም ከ 15 ሚሊዮን ዶላር ያላነሰ ገንዘብ ተልኳል። ይህንን በዓመት ስናሰላው ወደ 4 ሚሊዮን ዶላር ይጠጋል። ይህ ግን ከእኛ የሕዝብ ቁጥር ጋር ተቀራራቢ በሆኑት የአፍሪካ አገራት ከሚያገኙት አንድ አምስተኛ ነው። ስለዚህ በከፍተኛ ሁኔታ ማደግ ይጠበቅበታል። ለማሳደግ ደግሞ ከሚሲዮኖቻችንና በአገር ውስጥ ካሉ ተቋማት ጋር መስራት ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን ፡- ዲያስፖራው በዚህን ያህል መጠን ለአገሩ ድጋፉን አጋርነቱን ያረጋግጥ እንጂ አንዳንድ ጊዜ የድጋፍ ሁኔታው ሞቅ እና ቀዝቀዝ የሚልበት ምክንያት ምንድን ነው?**



> አሁን በመልሶ ማቋቋም ስራው ላይ ከገንዘብ ባሻገር የተለያዩ የስነ ልቦና ህክምናዎችና ሌሎች ድጋፎች ስለሚያስፈልጉ ዲያስፖራው እውቀቱንና ክህሎቱን ወደአገር ቤት አሻግሮ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ወደቀደመ ማንነታቸው እንዲመለሱ በማድረግና በማቋቋም ማገዝ ይጠበቅበታል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

**ይህስ እንዳይሆን እንደ አገር ምን መሰራት አለበት ይላሉ?**

**አቶ ወንደሰን፡-** እንግዲህ ዲያስፖራዎቹን የምናያቸው ከአገራቸው ውጪ እንደሚኖር ኢትዮጵያውያን ነው። እናም በአገር ቤት በሚፈጠሩ ነገሮች ላይ እንደ ግለሰብ የተለያዩ አመለካከቶች ሊኖሯቸው ይችላሉ። በዚህም በሚፈጠሩ ነገሮች ደስ ሊሰኙም፤ ሊከፋም ይችላሉ ማለት ነው። ይህ ሁኔታ በስሜት ደረጃ የምንወስደው ነው። ነገር ግን ከአገራቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት እኛ እንደምናምነውም ሆነ የሌሎች አገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው ሁኔታዎችን ተሻጋሪ መሆን እንዳለበት ነው። በየወቅቱ ከሚፈጠሩ ነገሮች ጋር የተያያዘ ሳይሆን ቋሚና ዘላቂ ተሳትፎ ነው የሚያስፈልገው። እስከ አሁን ያለው ተሳትፎ የአገርን ወቅታዊ ችግር ከመፍታት አንጻር የተሰራ ነው። ነገር ግን አገር ሊያድግ የሚችለው መደበኛ በሆነ የዲያስፖራ ተሳትፎ ብቻ ነው። በመሆኑ እውቀትና ቴክኖሎጂን በመደበኛነት በማሸጋገር በአገር ቤት ያሉ ተቋማትን አቅም በመገንባት ስራዎች በተቀላጠፈ ሁኔታ የሚሰሩበትን መንገድ በማመላከት በቱሪዝም ፣ በኢንቨስትመንት ላይ በመሳተፍና ሌሎችም እንዲሳተፉ በማስተዋወቅ መገለጽ አለበት። በመሆኑም እነዚህ ነገሮች እንዲሳኩ የማይዋዥቅ በአገር ቤት ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ተሳትፎ ያስፈልጋል። እኛም እንደ ተቋም የምናምነው ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮውም የሚያሳየው ይህንኑ ነው።

**አዲስ ዘመን፦ የዲያስፖራው ግንኙነቱ እንዳይዋዥቅ፣ በወቅታዊ አገራዊ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ስሜት እንዳይሆን በተለይም በእናንተ በኩል የሚሰራው ስራስ ምን መልክ አለው?**

**አቶ ወንደሰን፦** ዲያስፖራው ከአገር ቤት ጋር ያለው ግንኙነት ዘላቂ አገራዊ ጥቅሞች ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሚያደርጉ በርካታ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል። ጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም ለዛሬ የተዘጋጀው የዲያስፖራው የእውቅና መድረክም አንዱ ዓላማው ተሳትፏቸውን ወደመደበኛ ሁኔታ ማስገባት ነው።

ቅድም እንዳልነው ወቅታዊ አገራዊ ጥሪዎችን፣ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ከዲያስፖራው ሀብት ማሰባሰብ እና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ላይ መስራት ከዚህ በፊት ሄደንበታል። ከዚህ በኋላ የሚኖረን ነገር ተሳትፏቸውን መደበኛ የማድረግና ዲያስፖራው በሚኖርበትና አገርና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር፣ ወዳጅነታችን እንዲጎለብት ባሉበት አገር ያሉ ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ እንዲጎበኙ አምባሳደር ሆኖ የመስራት ጥሪ ነው እየቀረበ ያለው። እነዚህን ስራዎች እውን ለማድረግ የሚያግዙ የተለያዩ ስትራቴጂክ ሰነዶች ደግሞ ተዘጋጅተዋል።

**አዲስ ዘመን ፦ አገር ችግር ላይ በወደቀችበት ወቅት ዲያስፖራው ዲፕሎማት በመሆን የተጫወተውን ሚና እንዴት መግለጽ ይቻላል?**

**አቶ ወንደሰን፦** ያለፉት ሁለት ዓመታት በአገራችን ላይ ምን ያህል አላስፈላጊ ጫናዎች ሲሰነዘሩ እንደነበር ሁላችንም የምናስታውሰው ነው። እነዛ ጫናዎችን ለማስወገድ ደግሞ ዲያስፖራው ያደረጋቸው ጥረቶች በጣም ሰፋፊ ነበሩ፤ በ40 ትልልቅ ዓለም አቀፍ ከተሞች ከ 70 በላይ ሰልፎች ናቸው የተደረጉት። በሌላ በኩል ደግሞ በቲውተር ዲፕሎማሲ ዘርፍ የተሰራው ስራም በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም። የትልልቅ ተቋማት አመራሮችን የአገራት ተመራጮችን በተለያየ መልኩ በማግኘት ያልተገባውን ጫና አቁመው ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ችግር በራሳቸው መፍታተ እንዲችሉና የኢትዮጵያ መንግሥትም የተጣለበትን መንግሥታዊ ሃላፊነት እንዲወጣ በማስቻሉ በኩል ከፍ ያለ ጥረትን ሲያደርጉም ነበር።

በዚህም የተፈለገውን ያህል ጫና ሳይፈጠር ኢትዮጵያም የራሷን ችግር በራሷ እንድትፈታ በማድረጉ በኩል ዲያስፖራው የተውጣው ሚና በጣም ትልቅ ነው። በነገራችን ላይ በተለይም

**እውቅናውን የሚያገኙት የዲያስፖራ አባላት በተለይም በእውቀትና ክህሎት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በገጽታ ግንባታ፣ በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት፣ በሀብት አሰባሰብ ላይ የተሳተፉ ናቸው፣ እነዚህ በጣም በርካታ ቢሆኑም አሁን ላይ የእውቅና ዝግጅቱ የተደረገው ከ40 ለሚበልጡ የዲያስፖራ አባላት ነው**



በአሜሪካና በአውሮፓ ዜግነት አግኝተው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አገራቸውን ከጫና ነጻ ለማውጣት የሚኖሩበትን አገር ባለሥልጣናት በማስገደድ በኩል የተወጡት ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ለምሳሌ በአሜሪካን ምክር ቤት ቀርበው የነበሩት ሁለት ትልልቅ ህጎች ጸድቀው ቢሆን ኖሮ ዛሬ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ማሰብ አይከብድም፤ ነገር ግን ዲያስፖራው ባሳደረው ጫና እነዚህ ሕጎች ተፈጻሚ ሳይሆኑ ለመቅረት ችለዋል።

በመሆኑም ዲያስፖራው ያከናወናቸው ስራዎች የኢትዮጵያን ህልውና ከመታደግ አንጻር እንዲሁም አሁን ለምንገኝበት የራሳችንን ችግር በራሳችን ለመፍታት ለቻልንበት አውድ አብቅቶናል ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፦ አንዳንድ የዲያስፖራ አባላት በተለይም በተቃውሞ ጎራ የተሰለፉት አገሩን ለመደገፍ ቁርጠኝነት ያለውን ዲያስፖራ በመበረዝና የተዛቡ መረጃዎችን በማሰራጨት ጫና ለማሳደር ሲሞክሩ ይስተዋላል። የአገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ለእነሱም ጭምር በማብራራት በኩል እየተሰራ ያለው ስራ ምን መልክ አለው?**

**አቶ ወንደሰን፦** ዋናው ነገር የዲያስፖራ ተሳትፎ ስራችን አግላይ አይደለም። ማለትም የነቃፊና ደጋፊ አካሄድን አንከተልም። ሁሉም የራሱ አቋም ሊኖረው ይችላል ፤ እንደውም ይህንን በማበረታታት ነው የምንጀምረው። ነገር ግን ተቃውሟችንም ሆነ ድጋፋችን ከአገር መሰረታዊ ጥቅም ጋር የተስማማ መሆን አለበት።፡ የምንደግፈው ነገር የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ያስከብራል ወይ? የምንቃወመውም ነገር ልክ እንደዛው ማለት ያስፈልጋል። በመሆኑም ዲያስፖራው ድጋፉም ሆነ ተቃውሞው ከአገሩ ብሔራዊ ጥቅም ጋር የተቃኘ መሆን አለበት የሚለውን ነው የምናምነው። ይህንን ሃሳብ ለማስረጽም በርካታ ስራዎች ይሰራሉ።

ለምሳሌ የዲያስፖራ አገልግሎት በአገር ውስጥ ነው ያለው። ዲያስፖራው ደግሞ በተለያዩ የዓለም አገራት ነው የሚኖረው ። በመሆኑም በዋነኝነት የምንሰራው ከኢትዮጵያ ሚሲዮኖች እንዲሁም የዲያስፖራ መሪዎች ጋር ነው። ከእነሱ ጋር በመሆን የተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ላይ መወያየት እንዲሁም ሌሎች የቅርርብ ስራዎችን በመስራትና በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በመወያየት ዲያስፖራው የጠራ መረጃ እንዲኖረው ይሰራል። ሌላው በቀጥታ ከዲያስፖራው ጋር ለመገናኘት ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ስራ ይሰራል። በዚህም እንደ "ዋት ሳፕ" (whatsApp) ና መሰል ማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም በየደቂቃውና በየሰዓቱ በመገናኘት የመረጃ ልውውጥ እናደርጋለን። በዚህም ኢትዮጵያ ውስጥ ምን ተፈጠረ ለተፈጠረው ነገርስ የዲያስፖራው ሚና ምን ሊሆን ይገባል? በሚለው ላይ እንወያያለን። ነገር ግን ልዩነቶች ያሉና የሚጠበቁ ተፈጥሯዊም ናቸው። ዋናው ነገር ግን በንግግር እና በውይይት ለችግሮቻችን መፍትሔ መፈለግ ነው።

ሁልጊዜም ትልቁን አገራዊ ስዕል ማየት ለሁላችን በተለይም ለመጪው ትውልድ የሚጠቅመው የትኛው ነው? በልዩነቶቻችን ላይ ማተኮር ነው ወይንስ በጋራ በሚያደርጉን ነገሮች ላይ ተሰባስበን መስራት በሚለው ላይ እንወያያለን። ሁልጊዜም የጋራ ተጠቃሚ የሚያደርጉን ነገሮችን ይዘን መሄድ እንዳለብን እንግባባለን።

**አዲስ ዘመን፦ ባለፉት ሁለት ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው ጦርነት በርካታ ውድመት ተከስቷል። እነዚህን ሁኔታዎች ወደቀድሞ ገጽታቸው ለመመለስ (በመልሶ ግንባታ) የዲያስፖራው ሚና ምን ሊሆን ይገባል ይላሉ?**

**አቶ ወንደሰን፦** ይህ ትክክል ነው፤ ከሰላም ስምምነቱ ጋር በተያያዘ አንድ እየተሰራ ያለ ስራ ቢኖር የወደሙ ተቋማትን መልሶ ማቋቋም ነው። ከግንባታና መልሶ ማቋቋም ጋር በተያያዘ ደግሞ በያዝነው በጀት ዓመት ብቻ ከአምስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ማሰባሰብ ተችሏል። በዓይነት የተሰበሰበው ደግሞ ከ10 ሚሊዮን ዶላር በላይ ይገመታል። በመሆኑም ዲያስፖራው አሁንም ድጋፉን እንደቀጠለ ነው። ነገር ግን እቅዳችን ከሰላም ስምምነቱ ቀጥሎ ወደመደበኛ የዲያስፖራ የተሳትፎ ስራዎች መግባት ስለሆነ እዛ ውስጥ የሚያጋጥመን ደግሞ መልሶ ማቋቋም ነው።

በመሆኑም አሁን በመልሶ ማቋቋም ስራው ላይ ከገንዘብ ባሻገር የተለያዩ የሥነ ልቦና ህክምናዎችና ሌሎች ድጋፎች ስለሚያስፈልጉ ዲያስፖራው እውቀቱንና ክህሎቱን ወደአገር ቤት አሻግሮ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ወደቀደመ ማንነታቸው እንዲመለሱ በማድረግና በማቋቋም ማገዝ ይጠበቅበታል። ይህም የሚሆነው ባለበት አገር ገንዘብ እየሰበሰበ የተሰበሰበው ገንበዘብ ደግሞ ለመልሶ ማቋቋሙ መሰረታዊ የሆኑ ተቋማትን እንዲገነቡ በማስቻል በተለይም ከጤናና ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀትና የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ወደ ስራ ተገብቷል።

በመግባቢያ ሰነዱ መሰረትም ዲያስፖራው የወደሙ የትምህርትም ሆነ የጤና መሰረተ ልማቶችን መልሶ በተለይም በተሻለ ሁኔታ ገንብቶ በቁሳቁስ አሟልቶ ለማስረከብ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የአገር ባለውለታ ለሆኑ የዲያስፖራ አባላት የእውቅና ፕሮግራም ያለው ጠቀሜታ፤ እንዲሁም ለዚህ የምስጋና ፕሮግራም የተመረጡ ሰዎች ያበረከቱት አስተዋጽኦ ምን ነበር?**

**አቶ ወንደሰን፦** ከላይ የዘረዘርናቸው ስራዎች ላይ የነቃ ተሳትፎ ያደረጉ ዲያስፖራዎች ናቸው። እውቅናውን የሚያገኙት የዲያስፖራ አባላት በተለይም በእውቀትና ክህሎት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በገጽታ ግንባታ፣ በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፣ በሀብት አሰባሰብ ላይ የተሳተፉ ናቸው። እነዚህ በጣም በርካታ ቢሆኑም አሁን ላይ የእውቅና ዝግጅቱ የተደረገው ከ40 ለሚበልጡ የዲያስፖራ አባላት ነው። እነዚህ ሰዎችን ከላይ በተዘረዘሩት ስራዎች ላይ የነቃ ተሳትፎን በማድረግ በማስተባበር ላበረከቱት አስተዋጽዖ ኢትዮጵያ ታመሰግናችኋላች ስራችሁ እውቅና ይገባዋል ለማለት ነው።

በሌላ በኩልም ዛሬ እነዚህን አካላት እውቅና መስጠታችን ሌላውን ማበረታታትና ማነሳሳት ስለሆነ በተለይም አሁን ከሰላም ስምምነቱ በኋላ የእሳት ማጥፋት ስራን ትተን ወደመደበኛ የዲያስፖራ ተሳትፎ ለመግባት የምናደርገውን ጉዞ ለማጠናከር እንደ ድልድይም የሚያገለግለን ነው።

አሁን የመጡብንን ጫናዎች ተረባርበን በማሸነፍ አንዱን ምዕራፍ ዘግተናል ከዚህ በኋላ ወደመደበኛ የዲያስፖራ ተሳትፎ ስራችን መግባት አለብን ሌሎች አገራትም ቢሆን የተቀየሩት በዚህ መንገድ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። በመሆኑም ዲያስፖራው በቋሚነት ክህሎትና እውቀትን ወደ አገር ቤት በማሸጋገር በኢንቨስትመንትና በቱሪዝም ዘርፍ ላይ በስፋት በመሳተፍ ራሳቸውም ኢንቨስት በማድረግ ሌሎችም መጥተው በኢንቨስትመንቱ ላይ እንዲሰማሩ በመቀስቀስና አገራቸውን በማስተዋወቅ የአገራቸውን ገጽታ በመገንባት በሚኖሩበት አገርና በአገራቸው መካከል እንደ ድልድይ ሆነው በማገልገል የአገራት ግንኙነት እንዲጠናከር ሚናቸውን እንዲወጡ ምቹ መደላደልን የሚፈጥር ነው።

**አዲስ ዘመን፦ ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**

**አቶ ወንደሰን፦** እኔም አመሰግናለሁ

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# የአምራች ዘርፉን የማጠናከር ስራዎች - በኢንዱስትሪ ማዕከሏ ከምቦልቻ

አንተነህ ቸሬ



አቶ ሀብታሙ ኃይሌ

**በኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር በተያዘው 2015 በጀት ዓመት ባለፉት ስድስት ወራት ስድስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ሳስመዘገቡ 46 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ ተሰጥቷል። ፈቃድ የወሰዱት ፕሮጀክቶች ከ17ሺ 990 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል እንደሚፈጥሩም ይጠበቃል። ከዚህ በተጨማሪም የ182 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ፍቃድ ማደስም ተችሏል**

**በኢንዱስትሪ ማእከልነት ከሚታወቁት የአገሪቱ ከተሞች አንዷ የኮምቦልቻ ከተማ መሆኗ ይታወቃል። ከተማዋ በኢንዱስትሪ ከተማነቷ ፊትም ትታወቃለች፤ አሁንም በኢንዱስትሪ ማእከልነቷ ቀጥላለች።**

በ1943 ዓ.ም እንደተመሰረተች የሚነገርላት የቀድሞዋ «ቢራሮ» የአሁኗ ኮምቦልቻ ከተማ፣ ከ 1965 ዓ.ም ጀምሮ በማስተር ፕላን የምትመራ ዘመናዊ ከተማ ሆናለች። ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በሪጂኦፖሊታን ከተማ አስተዳደር መዋቅር እየተዳደረች የምትገኝ ሲሆን፣ በ14 የከተማ እና በስድስት የገጠር ቀበሌዎች የተዋቀረችም ናት። በኢንዱስትሪው ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚያስፈልጉ የተለያዩ መሰረተ ልማቶች ያላትም ናት። በተለይ በውሃ አቅርቦት በኩል ስማቸው በበጎ ከሚነሱ የኢትዮጵያ ከተሞች መካከል አንዷ ናት።

ኮምቦልቻ ለኑሮ ምቹ መሆኗ እንዳለ ሆኖ በእጅጉ የምትታወቀው ግን በኢንዱስትሪ መነኸሪያነቷ እና የኢንቨስትመንት መዳረሻነቷ ነው። ከተማዋ የበርካታ አምራች ድርጅቶች መገኛ ናት። ከአዲስ አበባ በደሴ አርጎ ወደ ትግራይ የሚዘልቀው ዋና መንገድ ከምቦልቻን ሰንጥቆ ነው የሚያልፈው። በከተማዋ የሚገኙት የደረቅ ወደብ (በዓመት እስከ 50 ሚሊዮን ብር የሚያ ስገኝ)፣ የአውሮፕላን ማረፊያና የኢንዱስትሪ ዞን እንዲሁም በከፊል የተጠናቀቀው የአዋሽ- ኮምቦልቻ- ሀራ ገበያ የባቡር ሃዲድ ኮምቦልቻን ለኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተመራጭ ካደረጉ ምክንያች መካከል ይጠቀሳሉ፡ ከዚህ በተጨማሪም ከተማዋን ከጅቡቲ ወደብ ጋር የሚያስተሳስራትና የደረቅ ጭነት መተላለፊያ የሆነ አውራ ጎዳና መኖሩ ለኢንዱስትሪ መነኸሪያነቷ ትልቅ ሚና እንዳለው ይታወቃል።

ከተማዋ ለተለያዩ ትላልቅ ከተሞች ያላት ቅርበትም ሌላው ተፈላጊ የሚያደርጋት ነው። ለጅቡቲ ወደብ 440 ኪሎ ሜትር፣ ለአዲስ አበባ በ375 ኪሎ ሜትር፣ ለአሰብ ወደብ በ390 ኪሎ ሜትር፣ ለሰመራ ከተማ በ 161 ኪሎ ሜትር ለክልሉ ዋና ከተማ ባህርዳር ደግሞ በ505 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ መገኘቷም ለኢንቨስትመንት ተመራጭ ከተማ እንድትሆን አስችሏታል።

በመልካም የኢንቨስትመንት መነቃቃትና ጉዞ ላይ የነበረችው ኮምቦልቻ፣ የሰሜኑ ጦርነት ለከፍተኛ ውድመት ዳርጓታል። የሰሜኑ ጦርነት በኮምቦልቻ ከተማ ከ 10 ቢሊዮን ብር በላይ ውድመት ማስከተሉን መረጃዎች ያመለክታሉ። በርካታ የአምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የውድመቱ ሰለባ ሆነዋል። በአብዛኛው ንብረትነታቸው የኢንቨስተሮች የሆኑ ከ270 በላይ ኮንቴይሮች ከኮምቦልቻ ደረቅ ወደብ ተዘርፈዋል። ከገንዘብ በተጨማሪ ከተማዋ ከፍተኛ ማኅበራዊ ውድመትም ደርሶባታል።

ከዚህ የጦርነቱ ውድመት በማገገም የኮምቦልቻን የኢንዱስትሪ ማዕከልነት ለማስቀጠል የከተማዋ አስተዳደር ከአማራ ክልል መንግሥትና ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመተባበር ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። የኮምቦልቻ ሪጂኦፖሊታን ከተማ አስተዳደር የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ ኃላፊ አቶ ሀብታሙ ኃይሌ ስለከተማዋ አጠቃላይ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ፣ በተለይም ስላለፉት ስድስት ወራት የኢንቨስትመንት ዘርፍ አፈፃፀም፣ ለ«አዲስ ዘመን» ጋዜጣ የሰጡትን ማብራሪያ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

## ኢንቨስትመንት በኮምቦልቻ

በኮምቦልቻ ሪጂኦፖሊታን ከተማ ከ 53 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ 519 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አሉ። እነዚህ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች 885 ነጥብ አምስት ሄክታር መሬት የሚሸፍኑ ናቸው። በማምረት ላይ ከሚገኙት ፕሮጀክቶች በተጨማሪ ግንባታ አጠናቀው በማሽን ተከላና መሰል ሂደቶች እንዲሁም በግንባታ እና በቅድመ ግንባታ ደረጃዎች ላይ የሚገኙም አሉ። በአምራች፣ በኮንስትራክሽን፣ በሆቴልና ቱሪዝም እና በማኅበራዊ ዘርፎች ላይ የተሰማሩት የኮምቦልቻ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች፣ ከስምንት ሺ700 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል ፈጥረዋል።

በኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር በ2015 በጀት አመት ባለፉት ስድስት ወራት ስድስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ላስመዘገቡ 46 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ ተሰጥቷል። ፈቃድ የወሰዱት ፕሮጀክቶች ከ 17ሺ 990 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል እንደሚፈጥሩም ይጠበቃል። ከዚህ በተጨማሪም የ 182 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ፍቃድ ማደስም ተችሏል።

## የኮምቦልቻ የኢንቨስትመንት የትኩረት አቅጣጫዎች

የኮምቦልቻ ሪጂኦፖሊታን ከተማ ዋነኛ የኢንቨስትመንት የትኩረት ማዕከል የአምራች ዘርፍ ኢንቨስትመንት ነው። ከዚህም መካከል የጨርቃ ጨርቅ እና የምግብ ማቀነባበር ፕሮጀክቶች ተጠቃሾች ናቸው። ዘርፎቹ ከፍተኛ የገበያ ድርሻ ያላቸው በመሆናቸው ከተማዋ መሰል የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ለመሳብና ለማስተናገድ ልዩ ትኩረት ትሰጣለች።

## የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ተሳትፎና ማበረታቻዎች

በኮምቦልቻ ከተማ በኢንቨስትመንት ስራ ላይ ተሰማርተው ከሚገኙ ባለሀብቶች መካከል አብዛኞቹ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ናቸው። ከአምራች ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መካከል በውጭ ባለሀብቶች የተያዙት ሰባት ብቻ ናቸው።

## የጦርነቱ ውድመትና የማገገሚያ ተግባራት

ኮምቦልቻና አካባቢው በሰሜኑ ጦርነት በእጅጉ እንደተጎዳ ይታወቃል። ጦርነቱ በኮምቦልቻ ከተማ ከ10 ቢሊዮን ብር በላይ ውድመት አስከትሏል። በርካታ የአምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የውድመቱ ሰለባ ሆነዋል። ጉዳት የደረሰባቸው አምራቾች ከዚህ ውድመት እንዲያገግሙ የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ። በቅድሚያ ተቋማቱ የደረሰባቸውን ጉዳትና ችግሮቻቸውን ማጥናት አስፈላጊ በመሆኑ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ከክልሉ የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ጋር በመተባበር የተቋማቱን ጉዳት የማጥናትና ችግሮቻቸውን የመለየት ተግባሮች ተከናውነዋል። በተጨማሪም ከባንኮችና እርዳታ አድራጊ ድርጅቶች ጋር ትስስር ፈጥረው የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያገኙ ጥረቶች ተደርገዋል። ባለሀብቶቹን ወደ ስራ እንዲመለሱ የሚያበረታቱ በርካታ የማነቃቂያ ሥልጠናዎችም ተሰጥተዋል።

የኢንቨስትመንት ዘርፍ ባለድርሻ አካላትን በመለየትና በተደጋጋሚ መድረክ በመፍጠር መግባባትና የጋራ መግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የመግባት፤ ነባር ኢንቨስተሮችን ዳግም ኢንቨስት እንዲያደርጉ ለይቶ የመመልመል እና ወደ ተግባር እንዲገቡ የማድረግ እንዲሁም ለአራት ጊዜያት ልዩ ልዩ የኢንቨስትመንት ፓናሎችን በማካሄድ ለኢንቨስተሮችና ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ የመፍጠር ተግባራት ተከናውነዋል።

ውድመት ደርሶባቸው ስራ ያቆሙ ፕሮጀክቶች ወደ ስራ እንዲመለሱ ለማድረግና ለማበረታታት የተቀናጀ የባለድርሻ አካላት መድረክ በመፍጠር ወደ ስራ እንዲመለሱ የሚያስችል ጥረት እየተደረገ ነው። ዘወትር ማክሰኞ የከተማዋ ከንቲባ የከተማዋን ኢንቨስትመንቶች በመጎብኘት የማበረታታት፣ ችግሮቻቸውን የመመልከትና የመፍታት ተግባራትን ያከናውናሉ። ነባር ባለሀብቶች ተጨማሪ ፕሮጀክቶችን እንዲገነቡም ይበረታታሉ። ከዚህ በተጨማሪም የገጽ ለገፅ ፕሮሞሽን ስራዎችም ይከናወናሉ፤ ይህም ውጤታማ የሆኑ ዘርፎች ስራቸውን በማስተዋወቅ የገበያ ትስስራቸው እንዲጨምር ያስችላቸዋል፤ የኢንቨስትመንት አማራጮችንና ምቹ ሁኔታዎችን በማስተዋወቅ የገፅታ ግንባታ ስራ ለማከናወን ያግዛል።

ከወሎ ዩኒቨርሲቲ፣ የኮምቦልቻ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እና ከኮምቦልቻ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበርም የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተግባራት የሚሰጡ ሲሆን፣ አምራቾች አገልግሎቱን የሚያገኙት በቴክኒክ ክህሎት፣ በጥራትና ምርታማነት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና በስራ ፈጠራ ማዕቀፎች ነው።

ከጦርነቱ ውድመት ለማገገም የተሰሩ ስራዎች ውጤቶችን አስገኝተዋል። ከ44 መካከለኛና ከፍተኛ አምራቾች መካከል 36 አምራቾች ወደ ስራ ተመልሰዋል። ከእነዚህ ተቋማት መካከል አስሩ በሙሉ አቅማቸው እያመረቱ ይገኛሉ፤ እነዚህ ድርጅቶች ቀደም ሲልም ጠንካራ አቅም የገነቡ ስለነበሩ በሙሉ አቅማቸው ወደ ስራ ሊመለሱ ችለዋል። ሌሎቹ ወደ ስራ የተመለሱት ተቋማት እየሰሩ ያሉት ደግሞ ከ55 እስከ 60 በመቶ በሚሆነው አቅማቸው ነው። ስምንት ተቋማት ግን እስካሁን ወደ ስራ አልተመለሱም፤ወደ ስራ እንዲመለሱ የሚያስችላቸውን የማገገሚያ ብድርም አላገኙም።

## የአገልግሎት አሰጣጥ ዝግጁነት

የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር በከተማዋ በኢንቨስትመንት ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶችን ፈጣንና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስተናገድ የሚያስችለውን የአሰራር ሥርዓት እየተገበረ ይገኛል። ለአብነት ያህል የከተማዋ ከንቲባ በየሳምንቱ ማክሰኞ የኢንቨስትመንትና የኢንዱስትሪ ዘርፍ ጉዳዮችን ይመለከታሉ። በዕለቱ የኢንቨስትመንት ባለጉዳዮችንና ቅሬታዎችን ያስተናግዳሉ፤ የኢንቨስትመንት ተግባራትን ይጎበኛሉ። ከዚህ በተጨማሪም የከተማዋ የኢንዱስትሪና የኢንቨስትመንት መምሪያ የመስክና የቢሮ አገልግሎቶችን በመዘርጋት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

## ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች

የኮምቦልቻን የኢንዱስትሪ ማዕከልነት ለማስቀጠልና በጦርነቱ ባደረሰው ጉዳት የታጣውን ለማካካስ ከከተማዋ ቀጣይ የኢንቨስትመንት የትኩረት አቅጣጫዎች አንዱ የአምራች ዘርፉን ማጠናከር ነው። በተለይም ለግብርና ማቀነባበርና ለጨርቃ ጨርቅ ምርት ዘርፎች ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል። እነዚህ ዘርፎች ብዙ የሥራ እድሎችን የሚፈጥሩ እና ለወጪ ንግድም ትልቅ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ በመሆናቸው በዘርፎቹ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ከ180 እስከ 200 ሄክታር መሬት እንዲዘጋጅ ይደረጋል። የክልሉ መንግሥት የኢንቨስትመንት መሰረተ ልማቶችን ያሟላል።

## የኢንቨስትመንት መሰናክሎች

በኢንቨስትመንት መነኸሪያነቷ የምትታወቀው ኮምቦልቻ ከተማ በተለይም የሰሜኑ ጦርነት ባደረሰው ውድመት ምክንያት በኢንቨስትመንት ስራዋ ላይ እክል የሚፈጥሩ መሰናክሎች አሉባት። ከእነዚህም መካከል ክልሉ በጦርነቱ በመጎዳቱ ምክንያት ከሦስተኛ ወገን የፀዳ (ክልሉና ከተማዋ በራሳቸው አቅም) የካሳ ክፍያን እንዲሁም የመሬት፣ የመሰረተ ልማትና የፋይናንስ አቅርቦትን እውን በማድረግ ረገድ ያለው ክፍተት ተጠቃሽ ነው። የአምራች ዘርፉ ከደረሰበት ጉዳት አገግሞ ወደ ስራ እንዲመለስ የሚያስችለውን በቂ የሆነ የፋይናንስ ድጋፍ አለማግኘቱም በቀጣይ ጊዜያትም ተፅዕኖው እንዲቀጥል የሚያደርግ ጥል ሌላው መሰናክል ነው።

የፋይናንስ ተቋማትና የኢንቨስትመንት ግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች ልዩ አሰራር በመከተል በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች መደገፍ ይኖርባቸዋል፤ መደበኛው አሰራር በእነዚህ አካባቢዎች የሚገኙና ጉዳት የደረሰባቸው ተቋማት በፍጥነት ወደ ስራ እንዲመለሱ የማድረግ አቅሙ የተገደበ በመሆኑ የተለየ አሰራር መከተልና መተግበር ያስፈልጋል። ከፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ጋር በተደረገ ምክክር ለ15 የአምራችና አገልግሎት ሰጪ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከአንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ የፋይናንስ ድጋፍ ተደርጓል። በየጊዜው የሚታዩ ለውጦች ቢኖሩም በርካታ አምራቾች አሁንም በቂ ብድርና እንደማሽን ያሉ ሌሎች ግብዓቶችን አላገኙም። በጦርነት ለወደሙ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የተለየ የድጋፍና የአሰራር ሥርዓት በመንግሥት በኩል አለመነደፉና ማበረታቻ አለመዘርጋቱ በከተማዋ የኢንቨስትመንት ፍሰት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያሳድር ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

# ጎሜ

# አገልግሎትን በምልጃ ¡

**ምሕረት ሞገስ**

ዘውዴ መታፈሪያ ራሱ በከተማ አስተዳደሩ በአንዱ ወረዳ ውስጥ እየሰራ የሚኖረው ደግሞ በሌላ ወረዳ ላይ በመሆኑ እንደፈለገው ከወረዳው በፍጥነት አገልግሎት ማግኘት አልቻለም። እርሱም የሚታየው እንደሌላው ተገልጋይ በመሆኑ መታወቂያ ማግኘት እልህ አስጨራሽ ትዕግስትን ጠይቆታል። ሰሞኑን ለአንድ ጉዳይ ለመመዝገብ የግድ የታደሰ መታወቂያ ያስፈልግሃል መባሉን ተከትሎ ወደሚኖርበት ወረዳ ጎራ አለ። እንደቀልድ አምስት ሰዓት አካባቢ ከሥራው ወጥቶ ወደ ወረዳው ሔደ፤ በዛ ፍጥነት እንኳን መታወቂያ ሊያገኝ ቀርቶ የሚያናግረውና ቀጠሮ የሚሰጠው ሰው አላገኘም። የወሳኝ ኩነት ሰራተኞች ስብሰባ ላይ መሆናቸውን ሰማ።

በማግስቱ ከስራ አስፈቅዶ አራት ሰዓት አካባቢ በወረዳው ተገኘ፤ ሆኖም ከእርሱ በፊት በአስሮች የሚቆጠሩ ተገልጋዮች እንደርሱ መታወቂያ ለማሳደስ ወረፋ ይዘው እየተጠባበቁ መሆኑን አወቀ። ‹‹በምን ያህል ሰዓት ይደርሰኝ ይሆን?›› ሲል ለራሱ ግምት ለማስቀመጥ አንድ ሰው ገብቶ ሂደቱን አጠናቅቆ እንደሚወጣ ለማረጋገጥ ሞከረ፤ ሆኖም ተስፋ አስቆራጭ ሆነበት። ከአምስት ሰዓት እስከ ስድስት ሰዓት ወረፋ ቢጠብቅም ከሶስት በላይ ሰው መታወቂያ አላደሰም። በአንድ ሰዓት ውስጥ ሶስት ሰው ብቻ መታወቂያ ካላሳደሰ ሰላሳ ሰው የሚደርሰው በትንሹ ከሶስት ቀን በኋላ ይሆናል ብሎ ለራሱ ገመተ። በስጨት ብሎ ችግሩ እንዲቃለል በመገመት ወደ ኃላፊው ቢሮ ጎራ ለማለት አስቦ ከተገልጋዮቹ ሃሳብ መሰብሰብ ጀመረ።

ሲያጠያይቅ መታወቂያ ለማደስ የተመደቡት ሰራተኞች ሥራውን የማያውቁ ከተገልጋዩ ቁጥር ጋር የማይመጣጠኑ መሆናቸውን ሰማ። ሌሎችም የጋብቻ፣ የልደት ሰርተፍኬት የሚያወጡ ሰዎችም በተመሳሳይ መቸገራቸውን አረጋገጠ። ለምሳ ሲወጡ እና ሁሉም ሲበተኑ እስኪ ሲረጋጋ ብሎ እርሱም ምሳ ለመብላት ወጣ። የሚበላውን በልቶ ማወራረጃውን ጠጥቶ ወደ ወረዳው ሲገባ ወረዳው የቅቤ ገበያ መስሏል። ጭራሽ ጫጫታው በዝቷል። ገሚሱ የመጣሁት በጠዋት ነው፤ ሲል ገሚሱ ትናንት መጥቼ ስላልደረሰኝ ነው ይላል። ጭራሽ በአንድ ሰዓት ሶስት ሰው ማስተናገድ ቀርቶ እስከ አስር ሰዓት ምንም ዓይነት ሰው እንዳልተስተናገደ ሲያውቅ ወደ ኃላፊው ቢሮ ለመሄድ አላመነታም ነበር። ነገር ግን ኃላፊውም በቢሮ አልነበረም። አልፎ ለመሄድ ወስኖ ወደ ወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ቢሮ አቀና። ሆኖም ፀሐፊዋ ዋና ስራ አስፈፃሚው ወደ ወረዳው ማህበረሰብ ለስራ መውጣቱን ነገረችው። በሁኔታው ተማሮም ወደ ማምሻ ቤቱ ሔደ።

እንደልማዳቸው ተሰማ መንግስቴ፣ ገብረየስ ገብረአምላክ ቀድመው እየተጨዋወቱ እና እየጠጡ ጠበቁት። ውሎውን ሲነግራቸው እየሳቁ ተሰማ ለዘውዴ ‹‹አንተም ያው ነህ።›› አለው። ዘውዴ በጣም ተበሳጨ። ‹‹ምን ማለትህ ነው? ›› ሲል ደነፋ። ተሰማ አልተበሳጨም። ‹‹ይኸው አንድ መታወቂያ ለማውጣት ሁለት ቀን ሙሉ በሥራ ሰዓት ቢሮህ አልተገኘህም። በተዘዋዋሪ ሌላው አገልግሎት ፈልጉ እዚህ የመጣው ሰው በአንተ እየተማረረ ነው›› ሲል መለሰለት። ‹‹ይሄ እና የእኔ ሥራ የሚገናኝበት ሁኔታ የለም። እኔ ባልኖርም የምሰራውን ስራ ከእኔ በታች ሊሠራው ለሚችል ሰው ውክልና ሰጥቻለሁ። ማንም ተገልጋይ የሚንገላታበት ሁኔታ የለም።›› አለ።

ገብረየስ በበኩሉ ‹‹ሆኖም ይሄ ችግር አንተን ብቻ ሳይሆን መላው የከተማዋን ነዋሪ ያሰቃየ ነው። ስለዚህ መፍትሔ ለማምጣት አንተ ምን አደረግክ?›› ሲል ጥያቄ አቀረበ። ዘውዴ ተገልጋዮችን ጠይቄ ኃላፊዎችን ለማግኘት ሞክሬያለሁ ነገር ግን አልተሳካልኝም አለ። ተሰማ እየሳቀ፤ ‹‹ያው እነርሱም ለመገልገል ሔደው ይሆናል።›› አለ። ዘውዴ ተበሳጨ። ለተሰማ፤ ‹‹ አንተ ነገሩን ቀልድ አድርገኸዋል ነገር ግን ቀልድ አይደለም።›› አለው።

ተሰማ ‹‹ ምን ላድርግ የኢትዮጵያም ሆነ የአዲስ አበባ የመንግስት ተቋማት ችግር ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። ትኩረታቸው ተገቢውን አገልግሎት በፍጥነት እና በጥራት ከመስጠት ይልቅ ዓላማ እና ፍላጎታቸው የተለያየ ነው።›› አለው። ዘውዴ ደግሞ ‹‹ እርሱስ እውነትህን ነው። ሕዝቡ ሲንገላታ አቋራጭ መንገድ ይፈልጋል። ያ ደግሞ የገቢ ምንጭ ከሆነ ውሎ አድሯል። ነገሩ እንኳን የመንግስት ሰራተኞች አንዳንድ ጊዜ አሰራር ላይም ችግር መኖሩ የሚካድ አይደለም።›› አለ።

ገብረየስ በበኩሉ ‹‹ለዛች ሱቄ የንግድ ፍቃድ ዕድሳት ታኅሣሥ 30 ያልቃል ሲባል፤ ታኅሣሥ 27 ሔድኩኝ ስብሰባ ላይ መሆናቸው ተነገረኝ። ታኅሣሥ 28 ብሔድም የገባ ሰራተኛ አልነበረም። ታኅሣሥ 29 እና ታኅሣሥ 30 የእረፍት ቀናት ናቸው። ጥር 1 ለማሳደስ ቢሯቸው ስሔድ፤ ለዕድሳቱ መክፈል ያለብኝ 102 ብር ብቻ ነበር። ቀኑ ስላለፈ 2ሺ ስድስት መቶ ብር መክፈል ግዴታህ ነው አሉኝ። ምን ማለት ነው? እኔ ቀኑን አላሳለፍኩም ቀኑን ያሳለፋችሁት ራሳችሁ ናችሁ። ብልም ምላሽ የሚሰጠኝ አልነበረም። ምክንያቱም እነርሱ ጥግብ ያሉ አገልጋዮች ናቸው። ደንበኛ ንጉስ ነው የሚለውን አባባል አባባል ብቻ አድርገውታል። የምን ንጉስ። አገልጋይን ማን ይቆጣል? አቤቱታ ቢቀርብ መልሱ በቅሎ ገመዷን በጠሰች በራሷ አሳጠረች እንደሚባለው ይሆናል።

አቤቱታ ማቅረብ ችግርን ማቃለል፤ መፍትሔ ማግኘት ሳይሆን በራስ ጥፋት ችግር ላይ እንደመውደቅ ነው። ለኃላፊው ለምን ፈጣን አገልግሎት አይሰጥም? በገዛ ጥፋታችሁ አመላልሳችሁን እንዴት ራሳችሁ መልሳችሁ ትቀጡናላችሁ? ብዬ ጠይቄ ነበር። ሆኖም ደረሰኙ የሚቆረጠው በዛሬው ቀን በመሆኑ በ102 ብር ዛሬ ላይ የፍቃድ ማደስ ክፍያን ማስፈፀም አንችልም አለኝ። ከ200 እጥፍ በላይ ስታስከፍሉን እንዴት እፍረት አይሰማችሁም? ብለን ብንጠይቅም ችግራችንን ከማየት እና አቤቱታችንን በተገቢው መንገድ ከመመለስ ይልቅ ማመናጨቅ ጀመረ። ጭራሽ ያቀረብነው ጥያቄ ወሬ ሆኖ ሰራተኞቹ ጋር ተዛብቶ ተራባ።

መቼም የሃቀኛ ስንቁ እውነት ነውና እኔም ስንቄን ቋጥሬ ጥያቄዬ ትክክል ነው ብዬ ነገር ግን ምላሽ አጥቼ ባላጠፋሁት ጥፋት መክፈል ካለብኝ ሌላ 250 እጥፍ ተቀጥቼ የንግድ ፍቃዴን አሳደስኩ።›› ብሎ ምሬቱን ሲያጠናቅቅ ተሰማ ቀጠለ፤ እኔ ደግሞ ቢቆይም ካርታ ለማግኘት ያየሁትን መከራ ለመግለፅ ይቸግረኛል። ተገልጋይን እንደጠላት የምናየው፤ ግን ምን ሆነን ነው? መሃንዲሱ ወይ በእጅህ ና አላለኝ፤ ወይ ተገቢውን አገልግሎት አልሰጠኝ፤ ካርታ ይቀየርልኝ የገበርኩበት መሬት ይካተት ብልም ማን ሰምቶኝ? ለተመሳሳይ ጎረቤቶቼ ሁሉ ካርታ ተሰጥቶ እኔ ግን ለዓመታት ተመላለስኩ በመጨረሻ እንደምንም ከስሼ ተጣልቼ ተለማምጬ ደጅ ጠንቼ ምላሽ አገኘሁ። አሁን ተገልጋይ መሆንን ሳስብ የምመኘው ሞትን ብቻ ነው።›› አለ።

ዘውዴ ደግሞ የሚጠጣውን እየተጎነጨ፤ ‹‹ከሰው ጋር ሲኖር አገልግሎት ሲሰጥ መተሳሰብ እና መረዳዳት እንጂ የራስን ጥቅም ለማስቀደም መሞከር ተገቢ አይደለም። አጉል ብልጠት አያዋጣም። ሰበብ እየፈለጉ ተገልጋይን በማንገላታት በእጅ መንሻ ለመስራት መሞከር ብዙ ርቀት አያስኬድም፤ የሚያስከትለው ጭራሽ ውድቀትን ነው። አንድ አገልጋይ አንድ ሰሞን ሲያንገላታኝ ከረመ፤ ጉዳዬን በስንት ምልጃ በጨረስኩ በሶስተኛው ቀን እኔው ጋር ሊገለገል መጣ፤ የበላበትን ወጪት ሰባሪ የተደረገለትን ውለታ የሚረሳ ውለታ ቢስ ያስተማረውን ሕዝብ የሚያሰቃይ ከሃዲ እንደሆነ አስቤ ሕዝብን ሲያንገላታ ለኖረ ተገልጋይ እያንገላቱ ማሳየት ነው። ብዬ ለራሴ አሰብኩኝ፤ ግን ደግሞ አገልግሎትን በማጓተት እምነት የማይጣልበት ሰው ሆኖ መገኘትን ሳስብ ቀፈፈኝ።

እርግጥ ነው፤ ጥጋብ ወደ ርሃብ ይነዳል፤ ከልክ ያለፈ ጥጋብ ወደ ችግር መግፋቱ አይቀርም። ምንም እንኳ በጥጋቡ ሲያንገላታኝ ቢከርምም ዋጋውን ማግኘቱ አይቀርም ብዬ በተገቢው መልኩ አገለገልኩት ግን ደግሞ በተገቢው መልኩ ማገልገሌን የተቀበለበት መንገድ የሚያስቅ ነበር። ‹እኛ እኮ የገባን ነን ፤ መቅጣት ያለብንን እንቀጣለን› ብሎ ሳንቲም ሊያስጨብጠኝ ፈለገ። አይሆንም ስለው ነገሩ ጥርስ እና ከንፈር ሲደጋገፍ ያምራል፤ መደጋገፍ ጉልበት ይሆናል እንደጋገፍ ብዬ እንጂ ማታለሌ ወይም ሙስና መስጠቴ አይደለም አለኝ ፤ ስቄበት አሰናበትኩት፤ የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጣጣ እንደሚባለው፤ አንዳንድ ሰው አንድ ጊዜ ጥቅም ባገኘበት መንገድ ሁልጊዜ የሚሳካለት ይመስለዋል።

እርሱ ሕዝብ እያታለለ ስለሚዘርፍ ሌሎች እርሱን በሚያባብሉበት መንገድ እኔን ለማባበል እና ለማታለል ሞከረ። እኔ ግን ትክክለኛውን መንገድ ተከትዬ ተገቢውን አገልግሎት ሰጥቼዋለሁ። በመጨረሻም የአገር ልጅ የማር እጅ ብዬ ለሀገራችን በእውነተኛ መንገድ እንስራ ወገን ሀገርን የሚረዳና በችግር ጊዜ የሚደርስ አለኝታ ነውና በችግር ጊዜ እኔን እና መሰል ተገልጋይ ዜጎችን ከምታንገላታ ሁሉም እጅ ላይ የምትወድቅበት ጊዜ ሊያጋጥም ስለሚችል ተጠንቀቅ ብዬ አስተምሬ ሸኘሁት ።›› አለ።

ገብረየስ በበኩሉ፤ ‹‹የመታወቂያው ጉዳይ የተወሳሰቡ ችግሮች ያሉበት ነው። ለረዥም ጊዜ አገልግሎቱ ተቋርጦ ነበር። በትንሽ ማረሻ ትልቅ እርሻ የሚል ብሒል ተይዞ በቀላል ወጪ ብዙ ጥቅም ማስገኘት ኢኮኖሚን ይገነባል ተብሎ የተለያዩ የአሰራር ስርዓቶች ተዘረጉ፤ ነገር ግን በተለይ መታወቂያ ማደስ ቆሞ ስለነበር ከተከማቸው ስራ ጋር የሚመጣጠን የሰው ሃይል አላሰማሩም። በተጨማሪ አንዳንዶቹ ገና የአሰራር ስርዓቱ ያልገባቸው አዲሶች ናቸው፤ እነዚህ ሁሉ ችግሮች ተደማምረው ተገልጋይ ላይ ችግር ይፈጥራሉ። ዕድሉን ለመጠቀም የሚሞክሩ ደላሎች ሲጨመሩበት ያለ ሳንቲም በትክክለኛው መንገድ መታወቂያም ሆነ ሌሎች አገልግሎቶችን ማግኘት ብርቅ መሆኑ አያስገርምም።›› አለ።

ዘውዴ እንደልማዱ ከመቀመጫው ቀድሞ እየተነሳ ከሌሊቱ አስር ሰዓት ተነስቶ ወረፋ ይዞ መታወቂያ ማሳደስ የግድ መሆኑን ስለተረዳ ቀድሜ ወደ ቤቴ ሄጄ በሌሊት ብነሳ ይሻለኛል፤ ምንም እንኳ የሚተካኝን ሰራተኛ ወክዬ ስራዬ ላይ ባልገኝም ተወካዬ ሙሉ ለሙሉ እኔን ወክሎ ሊሰራ የሚችልበት ሁኔታ ሊስተጓጎል ስለሚችል በጊዜ ወደ ቤት መሔድ ይሻለኛል ብሎ ጠረጴዛውን ተመርኩዞ ተነሳ።

> "የመታወቂያው ጉዳይ የተወሳሰቡ ችግሮች ያሉበት ነው። ለረዥም ጊዜ አገልግሎቱ ተቋርጦ ነበር። በትንሽ ማረሻ ትልቅ እርሻ የሚል ብሒል ተይዞ በቀላል ወጪ ብዙ ጥቅም ማስገኘት ኢኮኖሚን ይገነባል ተብሎ የተለያዩ የአሰራር ስርዓቶች ተዘረጉ፤ ነገር ግን በተለይ መታወቂያ ማደስ ቆሞ ስለነበር ከተከማቸው ስራ ጋር የሚመጣጠን የሰው ሃይል አላሰማሩም። በተጨማሪ አንዳንዶቹ ገና የአሰራር ስርዓቱ ያልገባቸው አዲሶች ናቸው፤ እነዚህ ሁሉ ችግሮች ተደማምረው ተገልጋይ ላይ ችግር ይፈጥራሉ።..."

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# የደቡብ ኢትዮጵያ ሙዚቃዊ ጥበባት

ዋለልኝ አየለ

ባለፈው ሳምንት ጥምቀት የመላው ኢትዮጵያ ድምቀት መሆኑን አይተናል። ሆኖም ግን በዝርዝር ትኩረት ያደረግነው የጃንሜዳው ድምቀት ላይ ነበር። ዛሬ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ልንሄድ ነው። ምክንያቱም እዚህ አካባቢ ከጥምቀት ሰሞን ጀምሮ በጥር ወር ውስጥ የሚካሄዱ በርካታ የሙዚቃ ትዕይንቶች አሉ። ይህ የሚታየው በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ ጋርዱላ፣ ዲራሼና አካባቢው ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሰሞኑን የመገናኛ ብዙኃን ላይ እንዳየነው የጌዲዮ ዘመን መለወጫ ሰሞን ስለሆነ የተለያዩ ትርዒቶች እየቀረቡ ነው። ይህን ሌላ ጊዜ በዝርዝር የምንመለስበት ይሁንና ከጥምቀት ሰሞን ጀምሮ የሚካሄደውን የጋርዱላና አካባቢዋ የፊላ ሥርዓተ ክዋኔና ምንነት እናያለን።

ስለዚህ የሙዚቃ አይነት ብዙም አልተባለም ማለት ይቻላል። ስለውጭው ዓለም እንጂ ስለራሳችን እንደማናጠና እና እንደማናውቅ መገለጫችን ሆኗል። ዓለም የሚያቀለጻጽሳቸው እነ ሞዛርትና ቤትሆቨን ናቸው። እነዚህ የሙዚቃ ተምሳሌቶች በ18ኛውና 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ብቅ ያሉ ናቸው። ኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ግን ከእነርሱ ሺህ ምናምን ዓመታት በፊት ዜማን ፈጥሯል። ዳሩ ግን እንኳን በዓለም በኢትዮጵያም የሙዚቃ ፈጣሪ እየተባሉ የሚጠሩ የውጮች ናቸው። ምክንያቱ ምንም ሳይሆን ጠንክረው ሰርተውባቸዋል፤ ጠንክረው አስተዋውቀዋቸዋል።

አንድ የታወቀ ነገር ካለ በዚያው ላይ ብቻ መረባረብ ነው። ያልተወቁትን ለማስተዋወቅ ጥናት አይደረግም። ለዚህም ነው የሙዚቃ ቅኝቶቻችን እንኳን ስንት እንደሆኑ አንድ ወጥ እይታ የለም። አንዳንዶቹ አምስት ናቸው ይላሉ፤ አብዛኞቹ ደግሞ አራት ናቸው ይላሉ። አንዳንዶቹም ከአራትም ከአምስትም በላይ ናቸው ይላሉ። ለዛሬው ስለፊላ የሙዚቃ ምንነትና ቅኝቶች እናውራ። ዋቢ ያደረግነው በፍሬው ተስፋዬ የተጻፈውን ‹‹ፊላና ሌሎች ሙዚቃዊ ጥበባት በጋርዱላ ዲራሼ›› መጽሐፍ ነው።

በኢትዮጵያ ሙዚቃ ላይ የተሰሩ ጥናቶችና ምርምሮች የአካታችነት ችግር እንዳለባቸው ፀሐፊው ጠቅሰዋል። የሙዚቃ ቅኝቶች በሰሜን ኢትዮጵያ በተለይም በወሎ አካባቢ ብቻ የተወሰኑ ናቸው። ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ ያሉትን የአገሪቱን የሙዚቃ ቅኝቶችና ስልቶች አላጠኑም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደረጉ ጥናቶች ግን የጋምቤላና የደቡብ ኢትዮጵያ ሙዚቃዎች እየተጠኑ ነው።

በጋሞ ከፍታ ቦታዎች የሚገኙ ዶኮዎችና የጋርዱላ ዲራሼዎች የሚጫወቷቸው ሙዚቃዎች ‹‹ሆሞፎኒክ›› ምድብ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። በተለይም የፊላ ሙዚቃ በኢትዮጵያ ብቸኛ ባለሰባት ኖታ የሙዚቃ መሳሪያ ነው። በመጀመሪያ ፊላ ምንድነው? የሚለውን እንመልከት።

ፊላ ሦስት ትርጓሜዎች አሉት። ፊላ ሙዚቃ ነው፤ ፊላ ውዝዋዜ (ዳንስ) ነው፤ ፊላ የሙዚቃ መሳሪያ ነው። ፊላ እንደ ሙዚቃ መሳሪያ ሲታይ ከአንድ ሜትር እስከ አምስት ሜትር ርዝመት ያለው የትንፋሽ መሳሪያ ነው። የሚዘጋጀው ከቀርቀሃና ከሸንበቆ ነው። እነዚህ ከሸንበቆና ከቀርቀሃ የሚዘጋጁ የሙዚቃ መሳሪያዎች በአንድ በኩል ክፍት፣ በሌላኛው በኩል ድፍን ናቸው። የፊላ የሙዚቃ መሳሪያ እንደ ዋሽንት አንድ (ነጠላ) ብቻውን አይሆንም፤ በስብስብ ነው፤ ስብስቡ ዝቅተኛው 24 ሲሆን እስከ 32 እና 48 ይደርሳል።

የመሳሪያዎቹ ብዛት ያስፈለገበት ምክንያት የተለያየ ድምጽ ለማውጣት ነው። አጨዋወቱ የራሱ ምትና ስልት አለው። ከትንሿ ቀጠን ያለች ድምጽ ይጀምርና እስከ 24ኛው ወፍራም ድምጽ ድረስ ይዘጋጃል። ለአቀማመጥ እንዲያመች በታችኛው በኩል የክር ማስገቢያ ቀዳዳ ይኖረዋል። ሁሉንም ፊላዎች በአንድ ክር በማስተሳሰር በጥንቃቄ ግድግዳ ላይ ይቀመጣል።

እነዚህ 24 የፊላ የሙዚቃ ድምጾች በሦስት ዋና ዋና ደረጃዎች (በባለሙያዎች ቋንቋ ቤዞች) ይመደባሉ። ይሄውም ካሳንታ (ወፍራም ድምጽ) ፣ አታንትያ (መካከለኛ ድምጽ) እና ፍት ፍታ (ቀጫጭን ድምጽ) በመባል ይመደባሉ። መሳሪያዎቹም በዚህ መልክ የተዘጋጁ ናቸው። በጨዋታ ጊዜ እያንዳንዱ መሳሪያ የሚያወጣው ድምጽ ቀዳሚና ተከታይ በመሆን



የፊላ ጨዋታ ከጥምቀት ሰሞን ጀምሮ ባሉት ሳምንታት ይከናወናል፣

ነው። መካከለኛና ወፍራም ድምጽ የሚያወጡት ከቀርቀሃ የሚዘጋጁት ፊላዎች ናቸው። ቀጭን ድምጽ የሚያወጡት ደግሞ ከሸምበቆ የሚዘጋጁት ናቸው። የፊላ ሙዚቃ በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ ስለሆነ ከጃዝ ጋር እንደሚመሳሰል የአፍሪካ ጃዝ አባት የሚባሉት ሙላቱ አስታጥቄ ተናግረዋል።

ፊላ ውዝዋዜ (ዳንስ) ነው። የፊላ ውዝዋዜ ለየት የሚያደርገው ነገር ተወዛዋዡ ራሱ የመሳሪያው ተጫዋች ነው። ተወዛዋዥ ለብቻው አያስፈልገውም። ውዝዋዜውን የሚመሩት በፊላ ጨዋታ ውስጥ የሚገኙ ሦስት መሪዎች ናቸው። እነዚህ መሪዎች ራሳቸው ፊላ እየነፉ ከመሀል አቋርጠው በመውጣት ውዝዋዜውን ይመሩና እንደገና ፊላ ወደመንፋቱ ይመለሳሉ። ለፊላ ጨዋታ አዲስ የሆነ ሰው የአጨዋወት ስልታቸው ግራ ያጋባዋል።

የፊላ ጨዋታ በአገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ዝግጅቶች ይታያል። ከ1998 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በአርባ ምንጭ ይታይ በነበረው ‹‹ሺ ኮከቦች›› የሙዚቃ ፌስቲቫል፣ በብሔር ብሔረሰቦች ቀን እና የዓድዋ ድል በዓላት በሚከበሩባቸው ጊዜያት በአገር አቀፍ ደረጃ ይታያል፤ ሙዚቃዎቹም በቴሌቭዥን ጣቢያዎች ይታያሉ።

የሙዚቃ መሳሪያዎቹ የተለያየ አይነት አላቸው። የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች ሎላት፣ ማይራ፣ ኩሉታት፣ ታርባ፣ ሐናት፣ ሉላ፣ ካሳ፣ ካልጋ እና ሀምቡፓ የሚባሉት ናቸው።

ሎላት የሚባለው ከሳላ ቀንድ ወይም ከአጋም እንጨት ይዘጋጃል። ከተዘጋጀ በኋላ በቅቤ ታሽቶ ጭስ ባለበት ይቀመጣል፤ ይሄውም እንዲወዛ በማለት ነው። ከፍየል ጺም አካባቢ በሚገኝ ቆዳና ፀጉር ይዋባል። ቁመቱ እስከ 40 ሴንቲ ሜትር ይሆናል። ይህ መሳሪያ በሁለቱም ጫፍ ቀዳዳ ያለው ሲሆን አንደኛው ሰፊና ሌላኛው ቀጭን ነው። አነፋፉ በሰፊው በኩል ሲሆን በቀጭኑ በኩል ደግሞ በጣት ያዝ ለቀቅ በማድረግ የተለያየ ድምጽ እንዲያወጣ ይደረጋል።

ሎላት ለዲራሼ ማህበረሰብ የሙዚቃ መሳሪያ ብቻ አይደለም። መግባቢያም ነው። እያንዳንዱ ቤተሰብና መንደር የየራሱን ሎላት ያውቃል። ለሆነ ጉዳይ የሚጠራሩት በሎላት ነው። ማታ ከሥራ ሲገቡም መጥተናልና ተዘጋጁ የሚል መልዕክት የሚያስተላልፉት በሎላት ነው። አነፋፉም እንደየ መልዕክቶቹ ይለያያል። አንድ ጊዜ ሲሆን ምን እንደሆነ፣ ሁለት ጊዜም ሦስት ጊዜም... ከሆነ መልዕክቱን የአካባቢው ማህበረሰብ ያውቀዋል።

ሌላው የትንፋሽ መሳሪያ ማይራ የሚባለው ነው። ከቀጫጭን ሸምበቆ ይዘጋጃል። እነዚህ ቀጫጭን ሸንበቆዎች ስድስት ሲሆኑ ከላይ ክፍት ከታች ድፍን ናቸው። ቁመታቸው የተለያየ ሲሆን ከትልቅ ወደ ትንሽ ይደረደራሉ። በቃጫ ገመድ ከታሰሩ በኋላ በቁልቋል ወይም በቅንጭብ ደም ይጣበቃሉ። ከቁልቋልና ቅንጭብ የሚወጣ ደም የማሚጨጭ ባህሪ ያለው ነው። የማይራ አደራደር በድምጹ አወራረድ መሰረት ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ወይም ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ነው።

ማይራን የሚጫወቱት ወንዶች ሲሆኑ በጃንሜዳው ጥምቀት ላይ ከምናየው ሀርሞኒካ ጋር ይመሳሰላል። አጨዋወቱም ልክ እንደ ሀርሞኒካ ከንፈር ላይ በማድረግ ከግራ ወደ ቀኝ ወይም ከቀኝ ወደ ግራ በማመላለስ የሚጫወቱት የትንፋሽ መሳሪያ ነው። የማይራ ጨዋታ ለወጣቶች የፍቅር መገለጫ ሲሆን አዋቂዎችም ጀግንነትንና ማንነትን ለመግለጽ ይጫወቱታል።

ይሄኛው የትንፋሽ መሳሪያ ደግሞ ከዋሽንት ጋር ይመሳሰላል፤ ዲራሼዎች ኩሉታት ይሉታል። ኩሉታት የሚዘጋጀው አንድ ወጥ ከሆነ ሸምበቆ ወይም ቀርቀሃ ነው። ቁመቱ እስከ 50 ሴንቲ ሜትር የሚደርስ ሲሆን በሁለቱም ጫፍ ክፍት ነው (እንደ ዋሽንት ማለት ነው)። በእኩል ርቀት የተበሱ አራት ቀዳዳዎች ይኖሩታል። አጨዋወቱም ልክ እንደ ዋሽንት በሁለት እጅ ተይዞ ቀዳዳዎችን በጣት በመያዝና በመልቀቅ ነው። ይህን ጨዋታ የሚጫወቱት በብዛት ሴቶች ናቸው። በነገራችን ላይ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚዘወተረው ዋሽንት ሴቶች ሲጫወቱት አይስተዋልም።

ከዘመናዊው ሳክስፎን ጋር የሚመሳሰለው የሙዚቃ መሳሪያ ደግሞ ታርባ ይባላል። የሚሰራው የቀርቀሃ አንጓዎችን አንዱን በአንዱ ላይ በመሰካት ነው። ጥንት የነበረው አገልግሎት አደጋ መከሰቱን ለማሳወቅና ትልቅ ሰው ሲሞት ለማርዳት ነው። በሁሉም እጅ ላይ አይገኝም፤ ኃላፊነት ለተሰጣቸው ሰዎች ብቻ ነው። አሁን ላይ ግን ይህ መሳሪያ እምብዛም አይታይም።

ሐናት የሚባለው የሙዚቃ መሳሪያ ደግሞ ከረጅም የሳላ ቀንድ የሚዘጋጅ ነው። በአፉ በኩል የሚነፋ ሲሆን ዋና አገልግሎቱም ከለቅሶ ሥርዓት ጋር የተያያዘ ነው። ሐናት ሲነፋ ከተሰማ በአካባቢው ሰው እንደሞተ ይታወቃል። የለቅሶ ስነ ሥርዓቱና መጠናቀቁም በሐናት ይደረጋል። ይህን መሳሪያ አሁን ላይ ለማዘጋጀት ስለሚያስቸግር (የሳላ ቀንድ) ያለውን በጥንቃቄ መያዝ ነው።

ሌላው የመጥፋት ደረጃ ላይ የደረሰው መሳሪያ ሉላ የሚባለው ነው። የሚዘጋጀውም ከድኩላ ቀንድ ነው። እርሻ የሚውሉ አርሶ አደሮችና እረኞች ወደቤት ሲገቡ የሚጠራሩበት ነው።

የዲራሼ ማህበረሰብ ከሚጠቀማቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች ለየት ያለው ደግሞ ሀምቡፓ የሚባለው ነው። የሚዘጋጀው ከዛፍ ፍሬ ነው። ፍሬው የሚገኘው ማህበረሰቡ ሺጫራ ብሎ ከሚጠራው ሐረግ መሰል እሾሃማ ተክል ነው። የፍሬውን ጠንካራ ቅርፊት በመተው በውስጡ የሚገኙ ትንንሽ ፍሬዎች በማጽዳት ሦስትና ከዚያ በላይ ቀዳዳዎች እንዲኖሩት ይደረጋል። አንደኛው ቀዳዳ የሚነፋበት ሲሆን የቀሩት በጣት እየተሸፈኑና እየተለቀቁ ድምጽ እንዲያወጡ ይደረጋል።

የጋርዱላ ማህበረሰብ የክር የሙዚቃ መሳሪያዎችም አሉት። አንደኛው ሾንቃ የሚባለው ሲሆን ከክራር ጋር ይመሳሰላል። ቀደም ሲል ከእንጨት፣ ከቃጫ ገመድ፣ ከቆዳና ከጅማት የሚዘጋጅ ቢሆንም አሁን ግን ከሲባጎና ሌሎች ዘመናዊ ክሮች እየተዘጋጀ ነው። ትምባ የሚባለው የምት የሙዚቃ መሳሪያ ደግሞ በአማርኛ ከበሮ ከሚባለው ጋር የሚመሳሰል ነው። አሰራሩም ሆነ አገልግሎቱም ከከበሮ ጋር ይመሳሰላል።

ይሄኛው ደግሞ የሙዚቃ መሳሪያ ብቻ ሳይሆን የእግር ጌጥም ነው። ሉሌት ይባላል። ከመዳብ የሚዘጋጁ ትንንሽ ቃጭሎች ናቸው። በቀጭን ጠንካራ ክር ከተሳሰሩ በኋላ የሴቶች ቁርጭምጭሚት ላይ ይታሰራሉ። ይህ ቁርጭምጭሚታቸው ላይ የታሰረ ቃጭል በተንቀሳቀሱ ቁጥር እያቃጨለ ሙዚቃ ይፈጥራል። ድምጹም እንደ አረማመዳቸው ይሆናል፤ በዚህም ማን እንደሆነች ለመለየት ያስችላል።

እንግዲህ በእነዚህ የሙዚቃ መሳሪያዎች (የትንፋሽ፣ የክር፣ የምት፣ ቃጭል) የሚጫወቱት ጨዋታ የተለያየ መልዕክት ያለው ነው። ለሀዘን፣ ለደስታ፣ ለፉከራ የሚውሉ ናቸው። አንዳንዶቹ መሳሪያዎችም የማህበረሰቡ መግባቢያና መጠሪያ ናቸው። ጨዋታዎችም እንደየወቅቱ ይከናወናሉ። በዝናብ ወቅት፣ በበጋ ወቅት፣ በሰርግ ወቅት ይጫወቷቸዋል። ጨዋታዎችም የየራሳቸው መጠሪያዎች አሏቸው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካ ባህልና ሚዲያ ጥናት የሦስተኛ ዲግሪ ተማሪ እና የመጽሐፉ ደራሲ ፍሬው ተስፋዬ በ2012 ዓ.ም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ በሰጡት አስተያየት፤ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የፊላና ሌሎች የሙዚቃ ጥበባትን የሚያጠና ተመራማሪ ተመድቧል። ፌስቲቫሉን በተባበሩት መንግሥታት የባህል፣ የትምህርትና ሳይንስ ድርጅት (ዩኔስኮ) ለማስመዝገብ በክልሉ ባህልና ቱሪዝምና በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ እየተሰራ ነው።

እንደ አቶ ፍሬው ገለጻ፤ የፊላና ሌሎች የደቡብ አካባቢ ሙዚቃዎች ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ግብዓት የሚሆን ክምችት ያለባቸው ናቸው። ግን በሥርዓት አልተጠኑም፤ አልተዋወቁም። እንኳን በአፍሪካና በዓለም ደረጃ በኢትዮጵያ ራሱ በሚገባ አልተዋወቁም። አፍሪካ የሰው ዘር ብቻ ሳይሆን የሙዚቃ ጥበባት መገኛም ሆኗን የሚያሳይ ነው፤ የጃዝ መነሻ ነው። በመሆኑም በቀጣይ መተዋወቅና መጠናት እንዳለበት አሳስበዋል።

# በቀጣዮቹ ሦስት አመታት ለሰባ ሚሊዮን ዜጎች ብሄራዊ የዲጂታል መታወቂያ ይሰጣል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በመጪዎቹ ሶስት አመታት ሰባ ሚሊዮን ዜጎችን የዲጂታል መታወቂያ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ እየሰራ መሆኑን በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የብሄራዊ መታወቂያ ፕሮግራም አስታወቀ።

አገልግሎቱ የነዋሪዎችን ትክክለኛ ማንነት እና መረጃ በአስተማማኝ ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚረዳ አዲስ ስርአት እንደሆነ ፕሮግራሙ ገለጸ።

የብሄራዊ መታወቂያ ፕሮግራም የምዝገባ ዳይሬክተር አቶ ሄኖክ ጥላሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ይህ ፕሮግራም የማይለወጡ ብለን የምንላቸውን የጣት አሻራ፣ የአይን ብሌን እና የፊት የገጽታ ምስል እንዲሁም መሰረታዊ ከሆነው የግለሰብ ስም፣ ጾታ፣ አድራሻ፣ እድሜ፣ዜግነት መረጃዎች ጋር በማጣመር አስተማማኝ በሆነ መልኩ አንዱ ከሌላው የሚለይባቸውን ማንነት የማረጋገጥ ስራ መስራት የሚያስችል ነው።

መታወቂያው ሙሉ ለሙሉ ዲጂታል እና ያለካርድ




የመለያ ቁጥር ብቻ በመያዝ ማንኛውንም አገልግሎት መጠቀም የሚያስችል ሲሆን፤ ካርድ ለሚፈልጉም መስጠት እንደተጨማሪ ስራ እየተሰራ ነው። እስካሁን ከ1 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በተለያዩ አይነት መንገዶች መዝግበናል ሲሉም አቶ ሄኖክ ገልጸዋል።

አቶ ሄኖክ በዋናነት ከብሄራዊ ባንክ ጀምሮ በፋይናንስ ሴክተሮች ፣ትምህርት ሚኒስቴር፣ኢትዮ ቴሌኮም፣ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ ጤና ተቋማት ፣አለም አቀፍ ተቋማት እንዲሁም መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በአጋርነት እየሰሩ እንደሆነ ተናግረዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ አንድ ሰው አንድ የመለያ ቁጥር ብቻ የሚኖረው ሲሆን፤ አገልግሎቱን በሀገር ውስጥ ካሉ ዜጎች በተጨማሪ በህጋዊነት ለሚኖሩ ነዋሪዎች በሙሉ ህጋዊ የሆነ ማንነትን የሚገልጽ መረጃ በመያዝ ካልሆነም አገልግሎቱን በሚጠቀም ሰው በምስክርነት መጠቀም ይችላሉ።

እስካሁን ባለው አዲስ አበባ ከተማ ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ቢሆንም በክልሎች እና ገጠራማ በሆኑ ስፍራዎች ጠቅላላ ሀገሪቱን ተደራሽ ለማድረግ እንደሚሰሩ አቶ ሄኖክ ገልጸው፤ አገልግሎቱ ፈጣን፣ አስተማማኝ እና ግልጽ እንዲሁም ተጠያቂነት እንዲኖር ከማድረግ ባለፈ መጭበርበርን፣ ኪሳራን እና የሀብት ብክነት በመቀነስ ዘመናዊ አገልግሎት ለመስጠት እና ለመጠቀም በማስቻል የሀገርን ኢኮኖሚን ያሳድጋል ሲሉ ተናግረዋል።

አገልግሎቱ የማንነትን መረጃ ከመስጠት ባለፈ የተለያዩ የትምህርትም ሆነ የጤና የተሟላ መረጃን በቀላሉ ለማግኘት ይረዳል። ለተቋማት አገልግሎት የሚሰጡትን ግለሰብ ማንነት በአጭር ጊዜ እና ወጪ አስተማማኝ መረጃ ይሰጣል። በመሆኑም ህብረተሰቡ ያለውን ተጨማሪ መረጃዎችን በድረገጽ ላይ በመመልከት እንዲመዘገቡ ጥሪ አቅርበዋል።

ከአንድ አመት በላይ የሆነው ይህ ፕሮጀክት ስርዓቱን የመሞከር እና ተግባራዊ የማድረግ ስራ ሲሰራ የቆየ ሲሆን፤ በአገር አቀፍ ደረጃ ተደራሽ በማድረግ እና እስከ 2018 ሰባ ሚሊየን ኢትጵያዊያንን ለመመዝገብ እየሰራን ነው ያሉት አቶ ሄኖክ፤ በ2025 ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ እንዲሁም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዲጂታል ስርአት ጋር በቅንጅት ለመስራት መታቀዱን ተናግረዋል።

## «ኢትዮጵያ በቀጣዩ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ዶላር እንደሚደርስም አስታውቋል።

በኢትዮጵያ በተለይ ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ የኢኮኖሚ እድገቱ ያንሰራራል የሚል ተስፋ እንዳለ የጠቀሰው አይኤምኤፍ፤ ከአፍሪካ ቀዳሚ የውጭ ኢንቨስትመንት መዳረሻዎች ከሆኑ አገራት መካከል ኢትዮጵያ ከኬንያ በተሻለ አምራች ኢንዱስትሪዎችን እየሳበች እንደምትገኝ አመልክቷል። ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ዘርፎችን እና ፕሮጀክቶችን እያሳደገች መሆኗንም በበጎነት አንስቷል።

ከሰሜኑ ጦርነት አስቀድሞ በምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በመገንባት ስኬታማ ሀገር ተደርጋ እንደምትወሰድም ያስታውሳል።

በግብርና፣ በኢንዱስትሪ እና በመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንት የሚመራ ኢኮኖሚዋ ከ15 ዓመታት እስከ 2019 በነፍስ ወከፍ በየዓመቱ በአማካይ ሰባት በመቶ ፈጣን እድገት ማስመዝገቡንም የዓለም ባንክ መረጃ አመልክቷል።

እ.ኤ.አ. በ2018 ስልጣን የተረከቡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንዲተገበር ውሳኔ ያሳለፉበት ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ትልቅ የለውጥ ጉዞ ጅማሮ እንደነበር፣ የቴሌኮም፣ የባንክና የስኳር ዘርፎችን ወደ ግል የማዞር ሂደት ጅማሮ በመልካም እንደሚጠቀስም ዘገባው አስነብቧል።

እ.ኤ.አ. በህዳር 2020 በሰሜን ኢትዮጵያ የተቀሰቀሰው ጦርነት ኢኮኖሚው ላይ ተጽእኖ ቢያሳርፍም የሰላም ስምምነቱ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ወደነበረበት መመለስ እንደሚቻል ተስፋ ማድረጉንም ያነሳል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዛፉ እየሱስወርቅ ዛፉ በበኩላቸው፣ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሁኔታ ተስፋ ሰጪ ፣ የተሻለ እና ምክንያታዊ ዕድገት ሊያሳይ ይችላል ብለው እንደሚጠብቁም ይጠቅሳሉ።

ለዚህ እንደምክንያት ከሚያነሱት ውስጥ አንዱ በኢትዮጵያ አንጻራዊ ሰላም መስፈኑን ነው። ሰላምን ሙሉ በሙሉ ማረጋገጥ ወሳኝ ነው፣ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ጥርጣሬ የሚያስገቡ ነገሮችን ማስተካከል ያስፈልጋልም ባይ ናቸው።

በሀገር በቀል ኢኮኖሚው የወደፊት የኢኮኖሚ ሂደት የውጭ ተጨማሪ ብድር ለማግኘት የዕዳ ጫናን ለማቃለል የተወሰነ እፎይታ ማግኘት ወሳኝ መሆኑ ይታመናል። መተግበር ለሚጀመረው ሁለተኛው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ልማት ዕቅድ ወሳኝ ይሆናል ነው የሚሉት አቶ ዛፉ።

የብሄራዊ ባንክ ገዢው አቶ ማሞ ቀደም ሲልም ከአለም ባንክና አይኤምኤፍ ጋር ሲሰሩ የነበሩ መሆናቸው የውጭ ምንዛሬ ችግርን ለመፍታት በሚደረገው ድርድር ላይም የኃላፊው በጎ ሚና ትልቅ እንደሚሆን አቶ ዛፉ ይናገራሉ።




**ከፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም**

# የተቋሙ ታራሚዎችን የማረምና የማነፅ እንቅስቃሴ በወፍ በረር ሲቃኝ

ውድ የአምዳችን ተከታታዮች በዚህ ሳምንት ዕትማችን በደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ስር ከሚገኙ ማረሚያ ቤቶች መካከል የወራቤ ማረሚያ ተቋምን የማረምና የማነጽ የሥራ እንቅስቃሴን አስመልክተን ያዘጋጀነውን ጽሑፍ ይዘንላችሁ ቀርበናል፤ መልካም ንባብ።

የደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሉባባ ጀማል እንደሚገልጹት፤ በክልሉ ውስጥ በ13 ዞኖችና በሁለት ልዩ ወረዳዎች 15 ማረሚያ ቤቶች ይገኛሉ። ከእነዚህ ማረሚያ ቤቶች መካከል አንዱ የወራቤ ማረሚያ ቤት ነው።

ፍርደኛ ታራሚ ተቀምጠው መዋል የለባቸውም በሚል መርህ ሁሉም ታራሚዎች በቀለም ትምህርትና በስልጠና ላይ ይሳተፋሉ። በሰለጠኑበት የሙያ መስክም ተደራጅተው እንዲሰሩ ይደረጋል የሚሉት ኮሚሽነር ሉባባ፤ ተቋሙና ኅብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥራት ያለው ዕቃ በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ እንደሚያቀርቡ አመልክተዋል።

የወራቤ ከተማ ነዋሪዎች የወራቤ ማረሚያ ቤትን መጥተው እንዲጎበኙና የታራሚ የእደ ጥበብ ምርቶችን እንዲገዙ ባዛር ማዘጋጀታቸውን መዘጋጀቱን የሚያስታውሱት ኮሚሽነሯ፤ ኅብረተሰቡ ስለማረሚያ ቤት ያለውን አመለካከት መቀየር የሚያስችል ተግባር መከናወኑን ይገልፃሉ።

እንደ ኮሚሽነሯ ገለፃ፤ በወራቤ ማረሚያ ተቋም ባህላዊ አልባሳት በብዛት ይመረታል፤ ከአካባቢው ከሚገኙ የመንግስት ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ከአስተዳሩ ምክር ቤት ጋር ውይይት በማካሄድ አጋጥሞ የነበረውን የገበያ ቦታ ችግር ተፈትቶ በከተማ ውስጥ ሱቅ መከፈቱን አስገንዝበዋል።

በተከፈተው ሱቅ የታራሚዎች ምርት ማቅረብ ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪም በከተማዋ ወስጥ በሚገኙ የመንግስት ተቋማት ጋር በመነጋገር በአነስተኛ ዋጋ ታራሚዎች በአጃቢ ወጥተው እንዲሰሩ ይደረጋል። በዚህም ተግባርም ታራሚዎች ሆኑ ተቋሙ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ኮሚሽነር ሉባባ ይገልፃሉ።

የወራቤ ማረሚያ ተቋም ኃላፊ ኮማንደር አወል ሁሴን በበኩላቸው፤ የህግ ታራሚዎች በሰሩት ወንጀል ተፀጽተው የበደሉት ሀገር፣ ተቋምና ግለሰብ ይቅርታ በመጠየቅ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያመጡ ይሰራል።

ለህግ ታራሚዎች የቀለም ትምህርትና የሙያ ስልጠና ይሰጣል የሚሉት ኃላፊው፤ በሰለጠኑበት ሙያ የሥራ ዕድል ፈጠራ ይከናወናል። ከገጠር አካባቢ ለመጡ አርሶ አደሮች የግብርና ሙያ እንዲማሩ ይደረጋል፤ ከሰለጠኑ በኋላ ገንዘብ በሚያገኙበት የሙያ መስክ ተደራጅተው እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታ ይመቻቻል። በሥራ ላይ መሰማራታቸው እነሱ በመታሰራቸው ምክንያት ቤተሰቦቻቸው እንዳይቸገሩ በማረሚያ ቤት ውስጥ ሰርተው ቤተሰቦቻቸውን እንዲያስተዳድሩ ዕድል ይፈጥራል።

አብዛኛው ታራሚ ወንጀል የሚፈጽሙ ባለማወቅ ነው፤ እንዲያውቁ መማርና መሰልጠን አለባቸው፤ በዚህ መሠረት በተቋሙ የሚሰጠው የቀለም ትምህርት እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ ብቻ ነበር። ከቀጣይ ዓመት ጀምሮ ግን በየዓመቱ 9ኛ፣ 10ኛ እያልን እስከ 12ኛ ክፍል ለመክፈት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት መግባባት ላይ ተደርሷል። በዚህ መሠረት የቅድመ ዝግጅት ሥራ በመከናወን ላይ እንደሚገኝ ኮማንደሩ ይገልፃሉ።

በቴክኒክና ሙያ መስክ የማሸከርከር ስልጠናን ጨምሮ በ13 የሙያ አይነቶች እንደሚያሰለጥኑ የሚናገሩት ኮማንደር አወል፤ የማሽከርከር ስልጠና የሚሰጠው ከወራቤ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ነው። ኮሌጁ በሁሉም የሙያ መስክ አሰልጣኞችን መድቦ እያሰለጠነ እንደሚገኝ አመልክተዋል።

ታራሚዎች በሰለጠኑበት ሙያ መሠረት በማድረግ ተደራጅተው እንዲሰሩ በማረሚያ ቤቱ ውስጥ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል። ያመረቱት ምርትም መሸጥ እንዲችሉ የገበያ ትስስር ተፈጥሯል። በዚህ መሠረት በማረሚያ ቤት ውስጥ 36 ማህበራት አሉ። እነዚህ ማህበራት ምርታቸውን የሚሸጡበት የገበያ ቦታ በከተማ ውስጥ እንዲያገኙ መደረጉን ኃላፊው ይገልፃሉ።



ታራሚዎች በሰለጠኑበት ሙያ በአጃቢ እየወጡ እንዲሰሩ ከተለያዩ ተቋማት ጋር ስምምነት ተደርጓል። በተለይም ከወራቤ ዩኒቨርሲቲ ጋር ውል በመፈፀም መልካም ሥነ ምግባር ያላቸው ታራሚዎች ወጥተው እንዲሰሩ ይደረጋል። ዩኒቨርሲቲው ለእነሱና ለአጃቢዎች በውሉ መሰረት ክፍያ ይፈፃማል ይላሉ።

ከመንገዶች ባለስልጣና ጋር በተደረገው ስምምነት ታራሚዎች በቱቦ ማምረት ሥራ እንዲሰማሩ ተደርጓል። ከወራቤ ሆስፒታልና ከሌሎች መንግስታዊ ተቋማት ጋር ውል በመፈፀም ታራሚዎች ወጥተው የሚሰሩበት ሁኔታ ተመቻችቶላቸዋል።

ታራሚዎች በተለያዩ ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ የሚደረገው የስራ ባህልን ለምደው እንዲወጡና የመገፋት ስሜት ተሰምቷቸው ከማረሚያ ቤት ሲወጡ በቀለኛ እንዳይሆኑ በማሰብ መሆኑን የሚገልፁት ኃላፊው፤ በዚህ መልኩ በቀለኛ ሳይሆኑ የተፀፀቱና የታረሙ፣ ትላንትን በክፋት የሚያዩ፣ ለነገ ራዕይ ሰንቀው ብሩህ አዕምሮ ይዘው እንዲወጡ እየሠሩ መሆኑን ይገልፃሉ።

የወራቤ ማረሚያ ተቋም የማረምና ማነጽ የሥራ ሂደት አስተባባሪ ኢንስፔክተር ልጃለም መንግስቴ እንደሚገልጹት፤ ማረሚያ ማዕከሉ ከወራቤ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በመተባበር ታራሚዎች አምራች ዜጎች እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ስልጠና ይሰጣል። ከሚሰጣቸው ስልጠናዎች መካከል አንዱ የአሽከርካሪነት ሙያ ነው።

የአሽከርካሪነት ስልጠና የሚሰጠው ለህግ ታራሚዎችና ለተቋሙ ሰራተኞች ሲሆን፤ ስልጠናው በህዝብ አንድ፣ በደረቅ አንድ፣ በባጃጅና በሌሎች የአሽከርካሪነት ሙያ መሆኑን የሚገልጹት አስተባባሪው፤ የማሽከርከር ሙያ ለመውሰድ በርካታ ታራሚዎች ፍላጎት አላቸው፤ ከዚህ አንፃር 10ኛ ክፍል ያጠናቀቁ፣ መልካም ሥነ ምግባር ያላቸው፤ ደጋጋሚ ያልሆኑና የረጅም ጊዜ ፍርደኞችን በመመልመል ስልጠናውን እንዲወስዱ ይደረጋል።

የህግ ታራሚዎች የሙያና ስልጠና ተወካይ ስንታየሁ ንጋቴ በበኩሉ፤ የህግ ታራሚዎች ተቀምጠው እንዳይውሉ በተለያዩ የቴክኒክና ሙያ ስልጠናዎች እንዲሳተፉ የመቀስቀስ ስራ እንደሚያከናውን ይናገራል።

የህግ ታራሚዎች መሰልጠን በሚፈልጉት የሙያ መስክ መረጃ በማሰባሰብ መስፈርቱን የሚያሟሉ ታራሚዎች ተመዝግበው እንዲሰለጥኑ እንደሚያበረታታ የሚናገረው ታራሚ ስንታየሁ፤ ይህን ኃላፊነት ያገኘው በማረሚያ ቤት በቆየባቸው ሰባት ዓመታት ውስጥ መልካም ስነ ምግባር በማሳየቱ በህግ ታራሚዎች በመመረጡ መሆኑን ይገልፃል።

በቆይታው በሙብራት ዝርጋታ፣ በልብስ ስፌትና በሽመና ሙያ ሰልጥኖ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አግኝቻለሁ የሚለው ታራሚ ስንታየሁ፤ ማረሚያ ቤቱ በተለያዩ የሙያ መስኮች የህግ ታራሚዎችን ማሰልጠኑን ይገልፃል።

አስረኛ ክፍል ላጠናቀቁ ታራሚዎች በሌቪል አንድ ደረጃ በአራት የሙያ መስኮች ስልጠና ይሰጣል፤ 10ኛ ክፍል ላላጠናቀቁ ታራሚዎች ደግሞ በሲሲ ደረጃ አጫጭር ስልጠናዎችን እንዲከታተሉ እንደሚደረግ የሚናገረው ታራሚ ስንታየሁ፤ በያዝነው በጀት ዓመት 304 ወንዶችና 15 ሴቶች በድምሩ 319 ታራሚዎች የአጭር ጊዜ ስልጠናዎችን አግኝተው የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ለመውሰድ ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን አመላክቷል።

## ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ስለ ጤና ስፖሊሲ አውጪዎች የቀረቡ ምክረ ሀሳቦች

ዘርፈ ብዙ ፖሊሲዎች በከፍተኛ ቁርጠኝነት በመተግበራቸው፣ በአገር አቀፍ በማክሮ ደረጃ እድገት መመዝገቡ፣ የተቀናጀ የጤና ዘርፍ እቅድ መታቀዱና መተግበሩ፣ የጤና መሠረተ ልማቶች መሻሻል እና የጤና ተቋማትን የአቅርቦት እና ዝግጁነት መሻሻሎች መኖራቸውና ከዓለም አቀፍ እና ከመንግሥት ለጤናው ዘርፍ የሚመደበው በጀት ቀስ በቀስ እያደገ መምጣቱና የማህበራዊ ጉዳዮች በከፍተኛ ሁኔታ መሻሻል መኖሩን በጤናው ዘርፍ የእናቶች እና ጨቅላ ህፃናት ዙሪያ የተመዘገቡ ዋና የስኬት ቁልፎች ናቸው። የስኬት ቁልፎቹ የተለዩት የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከጤና ሚኒስቴር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የእናቶች እና ጨቅላ ህፃናት የጤና ክብካቤ ሽፋን፣ የሞት መጠን ቅነሳን አስመልክቶ አገር አቀፍ መረጃዎችን በመተንተን የተመዘገቡ ውጤቶችን በመፈተሽ በተዘጋጀው ጥናት ላይ ነው።

በሰነዱ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ባለፉት 30 ዓመታት ውስጥ የእናቶችና የጨቅላ ህፃናት ሞትን በአስደናቂ ሁኔታ ብትቀንስም፤ አሁንም በእናቶችና የጨቅላ ህፃናት ሞት በከፍተኛ ደረጃ ላይ ከሚገኙ አገሮች ተርታ እንደምትገኝ ተጠቁሟል። አገራችን ባለፉት ዓመታት ውስጥ በሁሉም የሥነ-ተዋልዶ ጤና፣ የእናቶች፣ የጨቅላ ህፃናት እና የልጆች ጤና ክብካቤ መጨመር እና ሞትን በመቀነስ ላይ ናት። በጤና ባለሙያዎች በመታገዝ የሚደረጉ የወሊድ አገልግሎት የቅድመ ወሊድ ክትትል እና በጤና ተቋም የመውለድ ሽፋን ጨምሯል። ነገር ግን የጨቅላ ሕፃናት ሞት መቀነስ አዝጋሚ ሊባል የሚችል ሲሆን፤ ይህም በከተማ እና በገጠር፣ በተማረ እና ያልተማረ ማሕበረሰብ መሀል፣ እጅግ ድሃ እና ሀብታም መካከል እንዲሁም አርብቶ አደርና አርብቶ አደር ያልሆኑት መካከል ሰፊ ልዩነቶች አሉ።

በኢትዮጵያ የሥነ-ተዋልዶ ጤና፣ የእናቶች፣ የጨቅላ ህፃናት እና የልጆች ጤና ክብካቤ ሽፋን መጨመር ቢኖርም በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል ከፍተኛ ልዩነቶች አሉ። ምንም እንኳን ሽፋኑ ቢጨምርም በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚታየው አለመመጣጠን በተለይም በገጠር እና በከተማ መኖሪያ አካባቢ፣ በክልሎች፣ በድሃና በሀብታም እንዲሁም በትምህርት ደረጃ ከፍተኛ ልዩነት አለ። በአብዛኛዎቹ የእናቶች እና የህጻናት ጤና ክብካቤ እንዳገር ከፍተኛ ሽፋን የታየው በተለይም በገጠር አካባቢ በድሃዎች ያለው የጤና ሽፋን እየጨመረ በመምጣቱ ሲሆን በመሃከላቸው ያለው ልዩነት እያነሰ የመጣ ቢሆንም፤ በገጠር እና በድሃው የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ ያለው የጤና አገልግሎት አጠቃቀም አሁንም በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ሰነዱ አመላክቷል።

ሰነዱ ለፖሊሲ አውጪዎች በዋናነት ስድስት ጥናታዊ ምክረ-ሃሳቦችን ያቀረበ ሲሆን እነሱም፡-

- የእናቶች እና የሕፃናት ጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ይበልጥ ማሳደግ፡- አሁንም የጤና አገልግሎቶች ለብዙ ነፍሰ ጡር እናቶች ተደራሽ አይደሉም። ገጠር አካባቢ ነዋሪ ለሆኑ፣ ድሃ እና ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ ያሉ ሴቶች ከጤና አገልግሎት ተደራሽነት አኳያ ልዩ ትኩረት ሊደረግ ይገባል። የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብርን በሚገባ በመጠቀም የበለጠ የጤና አገልግሎት ፍላጎት መፍጠር፤ አገልግሎቶችን በጤና ኬላዎች እና ጤና ጣቢያዎች ተደራሽነትን ማሳደግ እንዲሁም በሁሉም ጤና ተቋማት የእናቶች ማቆያ ቦታዎችን እና የአምቡላንስ ትራንስፖርትን ጨምሮ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ለማዳረስ የበለጠ ርብርብ መደረግ አለበት።
- በኢትዮጵያ የጤና አገልግሎት አጠቃቀም ላይ ያለውን ከፍተኛ አለመመጣጠን መቀነስ፡- የእናቶችና የሕፃናትን ጤና ክብካቤ ሁሉን አቀፍ ሽፋን በሁሉም ቦታ በማዳረስ በተለይም ድሃዎች አገልግሎቱን እንዲያገኙና እንዲጠቀሙ ርብርብ ማድረግ፣ ተጨማሪ የጤና መሠረተ ልማት እና የጤና ባለሙያዎችን ማስፋፋት፣ ከአዳዲስ አሰራሮች ጋር ማቀናጀት፤ በተለይም በአርብቶ አደር ክልሎች ትኩረት ማድረግ እንዲሁም በእናቶች እና ድንገተኛ የወሊድ እና ህፃናት ጤና ሽፋን ላይ ያለውን አለመመጣጠን በአንጻራዊ ሁኔታ ዝቅተኛ ሽፋን በታየባቸው እንደ አማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች ልዩ ትኩረት ያስፈልጋል።
- የጤና ተቋማትን የጤና አገልግሎት አቅርቦትና ዝግጁነትን በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል፡- የቅድመ ወሊድ፣ የወሊድ እና የድህረ ወሊድ አገልግሎት አቅርቦትን ማሳደግ እና በጤና ተቋማት ላይ የበለጠ መዋዕለ ንዋይ (ኢንቨስትመንት) ማዋልና በጤና ተቋማት ውስጥ የእናቶችን የመውለድ ፍላጎትን ጨምሮ የአገልግሎት አቅርቦትን ለመጨመር እንዲሁም የጥራት መሻሻልን ትኩረት ያደረጉ አሰራሮች መዘርጋት ያስፈልጋል።
- የሥርዓተ-ጤናውን ማጠናከር፡- ባለፉት ሦስት አስርት ዓመታት ውስጥ የተመዘገቡት አበረታች የጤናው አገልግሎት እድገቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የበለጠ ትኩረት መስጠት ይገባል። ለዚህም ጤና ተቋማትን ማስፋፋት፣ የጤና ባለሙያዎችን በአይነትና በቁጥር መጨመር፣ ሀብት ማሰባሰብ፣ በቂ በጀት መመደብ፤ የቅንጅታዊ አሰራርን መዘርጋት፣ በጤና ተቋማት ለነፍሰጡር እናቶች የመቆያ ቦታዎችን ማስፋፋት፣ ሁሉም ሴት እና ህጻናት የሕይወት አድን የጤና ክብካቤዎችን ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም የጤና ሥርዓቱን አቅምን በማጠናከር ወደፊት የሚገጥሙትን ተግዳሮቶች ለመቋቋም ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።
- የጤና መረጃዎችን በአግባቡ በመጠቀም የጤና ሽፋንን ማስፋፋት፡- ኢትዮጵያ ለመረጃ ቅድሚያ በመስጠት በመረጃ የተደገፈ የጤና ፕሮግራሞችን ቅድሚያ በመስጠትና በመተግበር ረገድ የሚያስመሰግን ልምድ አላት። በመረጃ ላይ የተመረኮዙ ስትራቴጂዎች የእናቶችና የህፃናት ጤና ላይ የተገኙ ውጤቶችን ይበልጥ ለማሻሻል አወንታዊ ተፅእኖ ስላላቸው፤ የጤና ማስረጃዎችን ለማላመድና ቅድሚያ በመስጠት እና የእናቶችና የህፃናት ጤና ፕሮግራሞችን የማስፋፋት ልምዶች የበለጠ ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው።
- የሴቶችን አቅም ማጎልበት፡- የሴቶችን የጤና ግንዛቤ ማጎልበት፣ ለዚህም የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ማሳዳግ እንዲሁም በዋና ዋና የስነ ተዋልዶ፣ የእናቶች እና የህፃናት ጤና አገልግሎቶች አጠቃቀም ላይ የግንዛቤ ማስፋፊያ መርሃ ግብሮችን መተግበር እና ሴቶች በራሳቸው ጤና ፍላጎት ላይ የመወሰን አቅማቸውን ማሳደግ እስካሁን በዘርፉ የተገኘውን ውጤት የበለጠ ለማስፋፋት ጉልህ ሚና ስለሚያበረክት የፖሊሲ አውጪዎች እንዲተገበሩት በሰነዱ ተጠቁሟል።

## ከአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የዓለም ጤና ድርጅትና የምርምር ሥነምግባር መመሪያዎች

**ዳንኤል ዘነበ**

በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት ማንኛውም ሰው ጤነኝነቱ ተጠብቆ የመኖር መብት እንዳለው ይደነግጋል። ይህን ታሳቢ በማድረግ በዓለም ላይ የጤና ችግር ለማቃለል ብሎም ለማስወገድ የሚያስችሉ ምርምሮች ይካሄዳሉ። የማህበረሰቡን ጤና ችግር ለመለየት የሚደረጉ ምርምሮችም በሳይንሳዊ ዘዴ የተደገፉና የምርምር ሥነምግባርን የተከተሉ መሆን የግድ ይላል። እነዚህ በሰዎች ላይ የሚደረጉ ምርምሮች ጥንቃቄ የሚሹ በመሆናቸውን እና ምርምሮቹ ሰዎችን የሚጠቅሙ እንጂ የሚጎዱ እንዳይሆኑ ተመራማሪዎች የምርምር ሥነ - ምግባር መርሆዎችን ሊከተሉ እንደሚገባ የዓለም ጤና ድርጅት የጤና ምርምር ሥነ- ምግባር መመሪያዎች ያስረዳሉ። የጤና ምርምሮች የሚመሩባቸው እርስ በርስ ተወራራሽ የሆኑ 25 ያህል መመሪያዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ፀድቀው ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛል። የዓለም ጤና ድርጅት የምርምር ሥነምግባር መመሪያዎች ውስጥ አበይት የሆኑት ተዳሰው እንደሚከተለው በአጭሩ ለአንባቢያን ቀርበዋል። የመጀመሪያው ክፍል እንደሚከተለው ቀርቧል።

### ሳይንሳዊና ማህበራዊ ጠቀሜታዎችና መብቶችን ማክበር

የማህበረሰቡን ጤና ለመጠበቅ፣ የጤና ሥርዓት ደረጃን ለማሳደግ፣ በዘርፉ አዲስ ዕውቀትን ለማመንጨት ታሳቢ ተደርገው በሰዎች ላይ የሚሰሩ የጤና ምርምሮች የሥነምግባር መገለጫቸው ሳይንሳዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ነው። ምንም እንኳን ሳይንሳዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ለምርምር መሰረታዊ መገለጫ ቢሆንም ተመራማሪዎች፣ የጤና ምርምር ሥነምግብር ኮሚቴዎችና ምርምሩን የሚደግፉ አካላት በምርምሩ የሚሳተፉ ሰዎችን መብት መጠበቅ፣ ማክበርና ከለላ መስጠት እንዲሁም በፍትሃዊነት ማሳተፍ ይጠበቅባቸዋል። ይህ ሳይንሳዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ከሚገለጽባቸው ባህርያት ውስጥ ምርምሩ የያዘው የመረጃ ጥራት፣ ለማህበረሰቡ የጤና ችግር አዳዲስ ፖሊሲዎችን ጨምሮ መፍትሄ ከማመንጨት አኳያ ያለው አበርክቶ ምን ያህል እንደሆነ መመዘን የሚሉት ይገኙበታል።

ማህበራዊ ጠቀሜታን ምርምሩ ሊያመጣ በሚችለው መረጃ አስፈላጊነት ላይ የሚያተኩር ነው። ከምርምሩ የሚገኘው መረጃ የማህበረሰቡን የጤና ችግር ለማቃለልና የጤና አጠባበቅ ሥርዓቱትን ለማሻሻል ለሚደረገው ምርምር ስኬት ወሳኝ ከመሆኑ ባሻገር ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በምርምር የሚገኘው ውጤት ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ ላይ የሚያተኩረው ደግሞ ሳይንሳዊ ፋይዳው ነው። ትክክለኛ መረጃ ምርምሩ ዓላማ አድርጎ የተነሳባቸው መላምቶች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ ያስችላል። ምርምሩ ሳይንሳዊ ፋይዳ እንዲኖረው በሰዎች ላይ የሚተገበሩ ምርምሮች ተሳታፊዎችን ከጉዳት መጠበቅን ታሳቢ በማድረግ መተግበር ይኖርበታል። ምርምሩ የማህበረሰቡን የጤና ሥርዓት ለማሻሻል አስተዋጽኦ የሚኖረው ተመራማሪዎችን፣ ሐኪሞችንና ህሙማንን ጨምሮ ሌሎች ባለድርሻ አካላት በምርምሩ መተማመን ሲችሉ ነው። በጥቅሉ በሰዎች ላይ የሚካሄዱ ምርምሮች የተሳታፊዎችን እና የማህበረሰቡን መብት በመጠበቅና በማክበር መከናወን ይኖርባቸዋል።

### የምርምሩ ተሳታፊዎች ፍትሃዊ ተጠቃሚነትና ኃላፊነት

ምርምሩ የሚካሄድበትን አካባቢ ማህበረሰብ በፍትሃዊነት ማሳተፍ ስኬታማ ምርምርም ለማካሄድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። ይህም በምርምር መነሻ ዕቅድ የጤና ችግር ያጋጠመውን ማህበረሰብ በተገቢው መንገድ መካተቱን እና ምርምሩ በማህበረሰቡ ተቀባይነትና ተአማኒነት እንዳለው ማረጋገጥ ያስችላል። ስለሆነም ለምርምሩ ብቁና ወካይ የሆኑ ተሳታፊ ናሙናዎችን ከማህበረሰቡ በፍትሃዊነት መርጦ ማካተት ተመጣጣኝ ተጠቃሚነትና ኃላፊነት እንዲኖራቸው የሚያስችል በመሆኑ፤ በዚህ አግባብ መተግበር ይኖርበታል። ይህን መሠረት አድርጎ ምርምሩ ካልተካሄደ ተአማኒነትን ያጣል። ስለዚህ አስገዳጅ ሳይንሳዊ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ለምርምሩ ወካይ የሆኑ በተጠቀሰው አግባብ መርጦ ማካተት ይገባል።

ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሲባል ምርምሩ በተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የጤና ችግር ላይ ብቻ ማተኮር የለበትም። ይልቁንም የተለያዩ የማህበረሰቡ የጤና ችግሮችን ለማስወገድ ያለመና ሁሉንም ተደራሽ ሊያደርግ ይገባል። በምርምሩ ለጉዳት በቀላሉ ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ እንደ ሕፃናት፣ ነፍሰጡሮችና በመውለድ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን የመሳሰሉት የማህበረሰቡ ክፍሎች በምርምሩ እንዳይሳተፉ ማድረግ ሊያጋጥም የሚችለውን ተጓዳኝ ጉዳት እንደሚቀንስ ይታሰባል። እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች በምርምሩ እንዳይሳተፉ ማድረግ በበሽታው ላይ የሚደረገው ምርምር ምሉእ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ በሽታውን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ላይ ውስንነት እንዲያጋጥምና ምርምሩ ኢ-ፍትሃዊ እንዲሆን ያደርገዋል። ስለሆነም በበሽታዎች ላይ ምሉዕ የሆነ ምርምር አድርጎ አስፈላጊውን መረጃ በማግኘት የማህበረሰቡን የጤና ችግር ለማስወገድ ማሰብ ይገባል። በተጨማሪ የምርምሩን ተደራሽና ለማረጋገጥ ቀደም ሲል በተለያየ ምክንያት ያልተሳተፉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ማበረታታት ማሳተፍ ያስፈልጋል።

በአንድ ምርምር ላይ የደረሰው የጉዳት መጠንና ተቀባይነት ለመገምገም ተመራማሪዎች፣ የጤና ሥነምግባር ኮሚቴዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የምርምሩ ማህበራዊ ፋይዳና ሳይንሳዊ ዘዴ በአግባቡ መዳሰሱን ማረጋገጥ አለባቸው። ይህ በምርምር ሂደት በተሳታፊዎች ላይ የሚያጋጥም ጉዳትን ለመቀነስ ወሳኝ ነው። በመሆኑም የመረጃን ጉዳቶችና ጥቅም የሚገመግምና የሚወስን ፤ የመረጃ ደህንነትን ቁጥጥር ኮሚቴ ማዋቀር፤ ምርምሩ ጉዳት ያስከትላል ተብሎ ሲታመን ማቆም የሚያችል ግልፅ የሆነ መስፈርት ማስቀመጥ፤ የግለሰቦችን ምስጢራዊ መረጃ በአስተማማኝነት መጠበቅ መቻል፤ አላስፈላጊ ተግባራትን አለመፈጸም፤ ለምሳሌ ቀደም ሲል የተወሰደ የደም ናሙና ቢኖር አዲስ የደምና ሙና ወስዶ ምርመራ አለማድረግ፣ የምርምሩ ተሳታፊዎች የጉዳት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ከመጣ ምርምሩን አቋርጠው እንዲወጡ መደረግ ይኖርበታል።

### በመድኃኒት ሙከራ የምርምር ተቆጣጣሪ መምረጥ

ገለልተኛ የምርምር ተቆጣጣሪ ቡድን በመምረጥ የመድኃኒት ሙከራ ማካሄድ አንጻራዊ ጠቀሜታውን ለማወቅ ወሳኝ ነው። በሙከራ ተቆጣጣሪዎች በኩል ያሉትን ተሳታፊዎች በነሲብ (Random) መምረጥ የተሻለ ዘዴ ነው። ይህም ተመራማሪው የምርምሩ ተሳታፊዎችን ናሙና ሲመርጥ ሊያጋጥም የሚችለውን ስህተት መቀነስ ያስችለዋል፤ የምርምር ውጤቱ ተመራማሪው ያደረገውን የሙከራ ለውጥ እንጂ ሌላ ውጫዊ ችግር አለመሆኑን እንዲያረጋግጥ ይረዳዋል። የሙከራ ተቆጣጣሪ ትክክለኛ ውጤት ለማግኘት ተመራማሪዎች በመረጧቸው የሙከራ ናሙና ተሳታፊዎች ላይ የታየውን ለውጥ ሙከራ ካልተደረገባቸው ወይም በምርምሩ ሳይሳተፉ ተመሳሳይ የጤና ሁኔታ ላይ ከነበሩ ሰዎች ጋር በማነጻጸር የምርምሩን ውጤታማነት ያሳያሉ።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የተዘነጋው የሥጋ ደዌ በሽታ

**ሰላማዊት ውቤ**

«የሥጋ ደዌ በሽታ ታማሚ ነኝ። በዚህ ምክንያት በሕብረተሰቡ መገለሌ ለረጅም ጊዜ ከኖርኩበት አካባቢ እንድርቅ አድርጎኛል። ቤት ንብረቴን መሸጥ ነበረብኝና ቤት ንብረቴንም አሸጦኛል» ይሄን አስተያየት የሰጡን በተለምዶ ቆሼ እየተባለ የሚጠራውና ዘነበወርቅ ወይም አለርት ሆስፒታል አካባቢ ነዋሪ የሆኑ እናት ናቸው። ወይዘሮ ዘውዴ ዘበነ ይባላሉ። የተወለዱት ሥፍራውን ለመንገር ፈቃደኛ ባልሆኑበት የገጠር መንደር እንደሆነም ነግረውናል። እንዳጫወቱን ከትውልድ መንደራቸው የወጡት በ15 ዓመታቸው ነው። ምክንያታቸው ደግሞ ወርቅ በወርቅ ናት ተብሎ በገጠሩ ማህበረሰብ ዘንድ በሚነገርላት አዲስ አበባ ከተማ ሰርቶ ለመለወጥ ነበር።

ሆኖም ሸገር ላይ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ስላልሆነላቸው ለጋውን የታዳጊነት ዕድሜያቸውን ከአሜሪካ ጊቢ እስከ ካዛንቺስ በሚባሉ አረቄ ቤቶች ኮማሪነት ነው ያሳለፉት። እንደዚህም ሆነው መልከ መልካም ነበሩና እሳቸውን ብለው በየአረቄ ቤቱ ጎራ የሚሉ በርካታ ወዳጆች በማፍራታቸው ደህና ገንዘብ መያዝ ችለዋል። የራሳቸው ቪላ ቤትና መጠጥ ቤትም ለመክፈት በቅተዋል። ቢሆንም ትዳር ሞክረው አያውቁም። ፈጣሪ ከደህና ወዳጆቻቸው መካከል ከአንዱም ልጅ አልሰጣቸውም። በዚህ ሁኔታ በካዛንቺስ ከአራት አሥርት ዓመታት በላይ ኖረዋል። ሆኖም ከጊዜ በኋላ የሥጋ ደዌ በሽታ ተጎጂ በመሆናቸው ከካዛንቺስ በመልቀቅ አሁን ላይ እየኖሩ ወዳሉበት ዘነበወርቅ አካባቢ ለመሄድ ተገደዱ።

«ከጣት ጥፍሬ ነው የጀመረኝ። የጥፍሬን ስሮች እየጠዘጠዘ ያመኝ ነበር። በብርቱም ያሳክከኝ ገባ። ጆሮዬን ጭምር ስለሚበላኝ አከዋለሁ። የኋላ የኋላ አፍንጫዬንም ይይዘኝ ገባ» የሚሉት እናት ዘውዴ እንዳወጉን እነዚህን አዳዲስ ምልክቶች ቢያዩም ደፍረው ወደ ሆስፒታል አልሄዱም።

እጅ እግራቸው ቆሳሰለ። እንዲህ ሆነው መውጣት አፈሩ። ይሄን ያዩትና በመጠጥ ቤታቸው የቀጠሯቸው ሰራተኞቻቸው ጥለዋቸው ጠፉ። መቆሳሰላቸውን ያየ የአካባቢው ሰው ሁሉ ተጠየፋቸው። ደፍሮ የሚጨብጣቸው ቀርቶ ከርቀት ሰላም የሚላቸው አጡ። የሚያውቃቸው ሰው ሲያያቸው እንዳላየ ማለፍና መንገድ አሳብሮ መሄድ ጀመረ። በለቅሶና በሌሎች ማኅበራዊ ኩነቶችም መሄድ አቆሙ። ሰው እንዳያያቸው ይደበቁም ጀመር። በዚህ መካከል በሰው ጥቆማ አለርት ሆስፒታል ሄዱ። ዘግይተው በመሄዳቸው እጅ እግራቸውን ከቁስሉ ማዳን ባይቻልም ለወራት አልጋ ይዘው በተደረገላቸው ሕክምና በሕይወት መቆየት ቻሉ።

ግን ወደ ቤታቸው ቢመለሱም የቅርብ ጎረቤቶቻቸው እንኳን ሊቀርቧቸው አልቻሉም። እጅና እግራቸው በቁስሉ እጅግ ተጎድቶ ነበርና «ዘውዴ ቆማጣዋ» የሚል ቅጽያ ስም ሰጧቸው። በዚህ መልኩ በደረሰባቸው መገለልም ቤት ንብረታቸውን በቀላል ዋጋ ሸጠው ዘነበወርቅ አካባቢ ቆሼ ከትመው በቅርበት ሕክምናቸውን በመከታተል በልመና መኖር ጀመሩ።

«ዘውዴ ተቆምጣ ትለምናለች ብሎ ካዛንቺስ ጉድ አለ» ይላሉ። ከዚህ በኋላ ዘውዴ ማንንም መፍራት አቆሙ። መደበቃቸውም ቀረና በ36 ቁጥር አውቶቡስ ከዘነበወርቅ ካዛንቺስ በመመላለስ «ከማያውቁት መንፈስ ቅድስ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል» ብለው ኑሯቸውን በልመና ተያያዙት።

«በልጅነቴ ቢሞትም አባቴ የሥጋ ደዌ በሽተኛ መሆኑን የቆማጣ ልጅ እያሉ ከሚሰድቡኝ ጎረቤቶቻችን ተረድቻለሁ» የሚሉት ሌላው የሥጋ ደዌ ተጠቂ አቶ ዘገየ ብሩ ሆኖም እሳቸውም ሆኑ ቤተሰባቸው ለበሽታው ትኩረት ሳይሰጡትና ወደ ሆስፒታል ሄደው በመመርመር መላ ሳይፈልጉለት መኖራቸውን ያወሳሉ። በፊታቸውና በሰውነት ክፍሎቻቸው ላይ የተለያዩ ቁስሎች ይወጡባቸው እንደነበር ያነሳሉ። ከጊዜ ብዛት ቁስሎቹ ፀንተው የአልጋ ቁራኛ እንዳደረጓቸውና ሲመረመሩ የስጋ ደዌ በሽታ ተጠቂ መሆናቸው መረጋገጡንም ይገልፃሉ።



በዚህም ምክንያት በሕብረተሰቡ የተለያየ መገለልና መድሎ ሲደርስባቸው መቆየቱንና ተደብቀውና ራሳቸውን አግልለው ለመኖር መገደዳቸውን ይናገራሉ።

በኢትዮጵያ ስጋ ደዌ ተጠቂዎች ብሔራዊ ማህበር የፋይናንስና አስተዳደር ኃላፊ አቶ አብይ አባተ እንደሚሉት ከበሽታው ጋር ተያይዞ በህብረተሰቡ ውስጥ ስር የሰደደው የአመለካከት ችግር ተጠቂዎቹ ራሳቸውን አግለው እንዲኖሩ አድርጓቸዋል። በዚህ የተነሳ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በዘነበወርቅ በተለይም ቆሼ በሚባለው ቦታ በሀረር ገንደ ሴሮ፤ በኦሮሚያ ሻሸመኔ ኩየራ፤ በሌሎች በተከለሉ ሥፍራዎች ለመኖርና በጫናው ራሳቸውን ለማግለል መዳረጋቸውን ማሳያ ያደርጋሉ። ማህበሩ 20 ሺህ የሚጠጉ አባላት አሉት» የሚሉት ኃላፊው አመለካከቱ በቀላሉ ሊወገድ ባይችልም አሁን ላይ ለውጥ እንዳለም አንስተዋል።

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአካል ጉዳተኞች የአድቮካሲና መብት ጥበቃ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሲሳይ ጥላሁን እንደሚሉት ተጠቂዎቹ ለመገለል የሚዳረጉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ናቸው። በሽታው በሕብረተሰቡ ዘንድ ባለው የተዛባ አመለካከት ከሰው ወደ ሰው እንደሚተላለፍ ተደርጎ ይታሰባል። በዚህም የተነሳ ተጠቂዎቹ ራሳቸውን አግልለው በከፋ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ለብቻቸው እንዲኖሩ የተደረገበት ነበር። በሽታው በፈጣሪ ቁጣ እንደመጣባቸውም አድርጎ መቁጠር አለ። ከዚህ በፊት የነበረው መገለል በቃላት ሊገለፅ ከሚችለው በላይ ከባድ ነበር። አሁን ላይ ተሻሽሎ ለውጦች መጥተዋል። ሕብረተሰቡ ውስጥ ሆነው በሽታውን በሕክምና እየተከታተሉ የሚሰሩበትና የሚኖሩበት ሁኔታም ተፈጥሯል።

ይሁንና አሁንም በርካታ ቁጥር ያለው የሕብረተሰብ ክፍል እነሱን የሚያይበት አተያይ ትክክል ባለመሆኑ እንደ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው በየጊዜው በተለይም በየዓመቱ በዓሉ በሚከበርበት ወቅት ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እንደ አገር ይሰራሉ። በሥጋ ደዌ በሽታ ምክንያት የአካል ጉዳት የሚደርስባቸው ሰዎች እንደማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል መሥራት እንደሚችሉ ማሳየት አስፈላጊም ነው። ዘንድሮም በዓሉ የፊታችን ጥር 22 «የሥጋ ደዌን በሽታ አንዘንጋ» በሚል መሪ ቃል በፓናል ውይይትና በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ንቅናቄዎች ተከብሮ ይውላል። እ.ኤ.አ. ከ1953 ጀምሮ ጥር 30 ቀን የዓለም የሥጋ ደዌ ቀን ተብሎ መከበር የጀመረ ሲሆን በአገራችን ዘንድሮ ለ24ኛ ጊዜ ይከበራል። በዓሉ እንደ አገር የሚከበረው በተጠቂዎቹ ላይ ስር ሰዶ ያለውን አመለካከት መቅረፍ በሚያስችል ሰፊ ንቅናቄና ፓናል ውይይት ነው።በዚህም በሕብረተሰቡ ዘንድ ያለውን የተዛባ አመለካከት በመቅረፍ የተሻለ አስተሳሰብ እንዲሰፍንና ተጠቂዎቹም በሕብረተሰቡ ውስጥ ሆነው እኩል ተጠቃሚና ተሳታፊነታቸውን እንዲያረጋግጡ ያስችላል።

ከክርስቶስ ልደት በፊት መከሰቱ የሚነገርለት የሥጋ ደዌ በሽታ መንስኤው ማይኮባክቲሪየም ሌፕራይ ነው። በሰው ቆዳ ላይ, እንዲሁም በmucous membranes እና በነርቭ ሥርዓት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። እንደ ዓለም ጤና ድርጅት መረጃ በዓለም ላይ ወደ 11 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች በበሽታው ይሰቃያሉ።

# ዓለም አቀፍ



## ኡጋንዳ የነዳጅ ሀብቷን በኃላፊነት እንደምታስማ ገለጸች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኡጋንዳው ፕሬዝዳንት ዩዌሪ ሙሴቬኒ ሀገራቸው የነዳጅ ሀብቷን በኃላፊነት ታለማለች ሲሉ መናገራቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

የበለፀጉ ሀገራት ሰዎች ከቅሪት አካል የነዳጅ ኢንቨስትመንት አካባቢው እንዲርቁ በሚያሳስቡበት በዚህ ወቅት የምስራቅ አፍሪካዊቷ ሀገር ከፀሀይ፣ ከንፋስ እና ከውሃ የምታገኘው ሃይል በተጓዳኝ ከነዳጅ ሃይል ለማግኘት እንደምትሰራም ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል።


መንግሥት የአካባቢ ጥበቃን ደህንነት ለማረጋገጥ ሕጎች እና ሌሎች ዘዴዎች ቀደም ብለው ዘርግተዋል ሲሉም ተደምጠዋል። ሙሴቬኒ ይህን ያሉት ኡጋንዳ በሀገሪቱ መሀል ምዕራብ በሚገኘው በኪንግፊሸር አይል ፊልድ ከሚገኙት ጉድጓዶች በአንዱ የነዳጅ ቁፋሮ ስራ ስትጀምር ነው።

የነዳጅ ጉድጓዶች ቁፋሮ ዓለም አቀፉ የቻይና ኩባንያ እንደሚከናወን የተነገረ ሲሆን የአየር ንብረት ተሟጋቾች በነዳጅ ፕሮጀክቱ ላይ በተለይም ድፍድፍ ነዳጅን ወደ ታንዛኒያ ታንጋ ወደብ የሚወስደው የነዳጅ ቧንቧ መስመር (ኢኮፕ) አስመልክተው ዘመቻ አድርገዋል።

በተመሳሳይ መልኩ የቧንቧ መስመሩ ዝርጋታ ስነ-ምህዳሮችን አደጋ ላይ እንደሚጥል እና ማህበረሰቡን ለሰብዓዊ መብት ረገጣ ተጋላጭ እንደሚያደርግ አክቲቪስቶችም ገልጸዋል። ዩጋንዳ ግን የጋራ ፕሮጀክቱን ለመቀጠል ወስናለች።

ባለሥልጣናቱ ቀደም ሲል ነዳጁን በመሬት ውስጥ እንዲተው እና አረንጓዴ ኃይልን በማጎልበት ላይ እንዲያተኩር ግፊት ቢደረግም ዩጋንዳ አሁንም በሃይል ድህነት ውስጥ በመሆኗ አብዛኛው የአገሪቱ ሕዝብ አሁንም የማገዶ ተጠቃሚ መሆናቸውን ተነግሯል።

ከ15 ዓመታት በፊት በአገሪቱ ከተገኘው 6 ነጥብ 5 ቢሊዮን በርሜል ድፍድፍ ነዳጅ ከምችት 1 ነጥብ 4 ቢሊየን በርሜል ለገበያ አዋጭ ነው ተብሏል። የአገሪቱ ባለስልጣናት ኡጋንዳ በአሁኑ ወቅት በምስራቅ ካራሞጃ ክልል ውስጥ የጂኦሎጂካል ካርታ በማዘጋጀት ላይ እንደምትገኝና አዲስ ዙር የነዳጅ ፍለጋ ፍቃድ በቅርቡ ይፋ እንደምታደርግ ተናግረዋል።




## አሜሪካ ከቻይና ጋር ጦርነት የመግጠም አቅም እንደሌላት ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ዓለም አቀፉ የስትራቴጂክ ጥናት ማዕከል ባወጣው ጥናት መሰረት አሜሪካ አሁን ላይ ከቻይና ጋር የመዋጋት አቅም እንደሌላት ዎልስትሪት ጆርናል ጥናቱን ዋቢ አድርጎ ዘግቧል።

በጥናቱ መሠረት አሜሪካ ያላትን የተለያዩ ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች ለዩክሬን መለገሷ የጦር መሳሪያ እጥረት እንደገጠማት ተገልጿል።

አሜሪካ ቻይና የሀይል የበላይነቴን ለመውሰድ እየተጋች ነው በሚል በይፋ በስጋትነት ከፈረጀቻት ዓመታትን ያስቆጠር ሲሆን ይሄንን ተከትሎም ሁለቱ ሀገራት ፍጥጫቸው እንደቀጠለ ነው።

የንግድ ጦርነት፣ የቴክኖሎጂ እና ሌሎች ፉክክሮች የቀጠለ ሲሆን ባሳለፍነው ዓመት የአሜሪካ ከፍተኛ ባለስልጣናት ታይዋንን መጎብኘታቸውን ተከትሎ ውጥረቱ ከፍ ብሏል።

ዩክሬን ከሩሲያ ጋር የጀመረችውን ጦርነት በድል እንድትወጣ በሚል በየጊዜው ለኪቭ የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን ሰጥታለች።

ከዚህ በተጨማሪም የአሜሪካ ጦር መሳሪያ አምራች ኢንዱስትሪዎች በፍላጎቱ ልክ እያመረቱ አለመሆናቸው ለዋሽንግተን ካዝና መራቆት በምክንያትነት ተጠቅሷል።

አሁን ላይ አሜሪካ ከቻይና ጋር ወደ ጦርነት ብታመራ ከአንድ ሳምንት በላይ መዋጋት እንደማትችል ተቋሙ በጥናቱ ላይ ጠቅሷል።

ቻይና ከአሜሪካ ጋር ስትነጻጸር በወታደራዊ ቴክኖሎጂ መስከ አምስት እጥፍ ቀድማ መሄዷን የጠቀሰው ይህ የጥናት ማዕከል ዋሽንግተን ለጉዳዩ ትኩረት እንድትሰጥ አሳስቧል።

አሜሪካ ለዩክሬን ከመጋዝኖቿ እያወጣች ለዩክሬን ከሰጠቻቸው ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች መካከል የአጭር እና መካከለኛ ርቀት ሚሳኤሎች፣ የአየር መቃወሚያዎች እና ወታደራዊ አውሮፕላኖችን ከግለሰብ ትከሻ ላይ ተተኩሶ መምታት የሚችለው ከስምንት ሺህ በላይ ጃቪየር ሚሳኤል እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ።

# ስፖርት



# በኦሳካ የሴቶች ማራቶን ኢትዮጵያውያን የአሸናፊነት ግምት አግኝተዋል

ቦጋለ አበበ

የፈረንጆቹን የክረምት ወቅት ተከትሎ በብዛት ይካሄዱ የነበሩ የማራቶንና የጎዳና ላይ ውድድሮች በሀገር አቋራጭ ሩጫዎች ተተክተዋል። በዚህ ሳምንት መጨረሻም ከጎዳና ላይ ውድድሮች ይልቅ መሰናክሎች የሚበዛበት አገር አቋራጭ ውድድር በስፋት ይካሄዳል። ይሁን እንጂ ክረምቱ በማይጠነክርባቸው አንዳንድ የዓለማችን ከተሞች አልፎ አልፎ የጎዳና ላይ ውድድሮች ይካሄዳሉ። ከነዚህም መካከል በመጪው እሁድ በጃፓኗ አሳካ ከተማ የሚካሄደው የሴቶች ማራቶን ውድድር ተጠባቂ ነው።

በሌላው ዓለም እምብዛም የማይታወቀውን የሴቶች ብቻ የጎዳና ላይ ውድድሮችን በማዘጋጀት ከሚታወቁት ሀገራት መካከል አንዷ ጃፓን ስትሆን፤ አሳካ ይህን ሴቶች ብቻ የሚሳተፉበትን ማራቶን ታሰናዳለች። ይህ የማራቶን ውድድር እአአ ከ1982 አንስቶ ሴት የማራቶን ሯጮችን ብቻ በማወዳደር 42ኛ ዓመቱን ዘንድሮ ያስቆጥራል። በጃፓን ሶስተኛዋ ትልቅ ከተማ በሆነችው አሳካ የሚደረገው ይህ ውድድር በሺዎች የሚቆጠሩ አትሌቶችን ያሳትፋል። በዓለም አትሌቲክስ ዕውቅና ያለው ይህ ውድድር ከጃፓናዊያን አትሌቶች ባሻገር የሌሎች ሀገራትን ታዋቂ አትሌቶችን የሚያሳትፍም ነው። ውድድሩ እአአ ከ2011 አንስቶ ተወዳዳሪዎች ያልፉባቸው የነበሩ አቀበትና ኮረብታማ ስፍራዎችን በማስወገዱ ፈጣን ሰዓት የሚመዘገብበት ሆኗል። በዚህም የአትሌቶች የተሳትፎ ፍላጎት እንዲጨምር ምክንያት ሆኗል።

ከቀናት በኋላ የሚካሄደው ይህ ውድድር ኢትዮጵያዊያን እና ኬንያዊያን የማራቶን አትሌቶች የሚካፈሉበት እንደመሆኑም ከፍተኛ ፉክክር ሊካሄድበትና የቦታው ፈጣን ሰዓት ሊመዘገብበት እንደሚችል ተገምቷል። የቦታው ክብረወሰን ባለፈው ዓመት በጃፓናዊቷ አትሌት ሚዙኪ ማሱዳ ሲያዝ፤ አትሌቷ የገባችበት ሰዓትም 2:20:52 ነው። ይሁንና የምስራቅ አፍሪካዊያኑ ሀገራት አትሌቶች ፈጣን ሰዓት በሰከንዶች የተሻለ በመሆኑ በዚህ ዓመትም አዲስ ሰዓት ይመዘገባል በሚል ይጠበቃል። በውድድሩ ተካፋይ የሚሆኑና ለአሸናፊነት ከፍተኛ ቅድመ ግምት ከተሰጣቸው አትሌቶች መካከልም ኢትዮጵያዊያኑ ሄቨን ኃይሉ እንዲሁም ሲሳይ መሰረት ተጠቃሽ ናቸው።




የፊታችን እሁድ በኦሳካ በሚካሄደው የሴቶች ማራቶን ኢትዮጵያውያን አትሌቶች እንደሚያሸንፉ ይጠበቃል፣

ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በዚህ ውድድር የተካፈሉ ሲሆን፤ እአአ በ2010 አማኔ ጎበና እንዲሁም እአአ በ2019 ፋጡማ ሳዶ አሸናፊዎች ነበሩ። ጃፓን እአአ በ2007 የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናን ባስተናገደችበት ናጋይ ስታዲየም ፍጻሜውን የሚያደርገው ውድድር ዘንድሮም በቀዳሚነት ይገባሉ በሚል ይጠበቃል። ከተወዳዳሪ አትሌቶች መካከል ባላቸው ፈጣን ሰዓት ሁለተኛ ደረጃ በመያዝ የተቀመጠችው አትሌት ሄቨን ኃይሉ 2:20:19 የሆነ ሰዓት አላት። አትሌቷ ይህንን ሰዓት ያስመዘገበችው እአአ 2021 በአምስተርዳም ማራቶን ሲሆን፤ በወቅቱ በአንድ ሰከንድ ብቻ ቀድማት ሁለተኛ ደረጃን የያዘችው ኬንያዊት አትሌት በዚህ ውድድርም ተፎካካሪዋ ትሆናለች በሚል ይጠበቃል።

ኬንያዊቷ አትሌት ማውሬን ቼፕኬሞይ በወቅቱ ከሄቨን ጋር እልህ አስጨራሽ ውድድር በማድረግ ነበር ቀድማት የገባቸው። ያስመዘገበችው 2:20:18 የሆነ ሰዓትም የግሏ ምርጥ በመባል ተመዝግቦላታል፤ ይኸውም የዚህ ውድድር አሸናፊ ያደርጋታል በሚል በውድድሩ አዘጋጆች እንድትጠበቅ አድርጓታል። ነገር ግን በአንድ ሰከንድ ልዩነት በተከታይነት ስሟ ከሰፈረው ኢትዮጵያዊቷ ሄቨን ጋር እጅግ ፈታኝ የአሸናፊነት ፍልሚያ እንደሚገጥማትም ተገምቷል። ማራቶንን እንዲሁም ሌሎች የጎዳና ላይ ውድድሮች ላይ በመሮጥ የዓመታት ልምድን ያካበተችው አትሌቷ በጃፓኗ አሳካ ፈጣን ሰዓት በማስመዝገብ በተፎካካሪዋ ላይ ድልን በመቀዳጀት በውድድሩ ሌላኛዋ አሸናፊ ኢትዮጵያዊት አትሌት ለመሆንም ትሮጣለች።


አምና በዙሪክ ማራቶን ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ያጠናቀቀችው ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት ሲሳይ መሰረትም ለአሸናፊነት ከሚጠበቁት አትሌቶች መካከል አካቷታል። በውድድሩ ሶስተኛዋ ባለ ፈጣን ሰዓት አትሌት ስትሆን፤ በዙሪክ ያስመዘገበችው 2:20:50 የሆነ ሰዓትም የግሏ ምርጥ ነው። አትሌቷ በዓመቱ በበርሊን ማራቶንም ተሳትፎ ያደረገች ቢሆንም ርቀቱን የሸፈነችበት ሰዓት በስምንት ደቂቃዎች የዘገየ ነበር። በጎዳና ላይ ሩጫዎች ልምድ ያላት ሲሳይ በዚህ ውድድር ላይም ለሀገሯ ልጅ እንዲሁም ለኬንያዊቷ አትሌት ፈተና ልትሆንባቸው እንደምትችልም ተገምቷል፡፡


መሠረት ማኑፋክቸሪንግ ኃ/የተ/የግ/ ማኅበር
MESERET MANUFACTURING



ቆርቆሮዎችን በተለያየ ቀለም ያገኛሉ!
0923 39 4308/0923 30 4566/0113811017

0.40MM 28



የበረንዳ ቤት
ጣራ ታይልስ
መደበኛ ጣራ ቆርቆሮ
ኤጋ:300,400,500
CORRUGATED
GREEN,RED,BLUE



0923 39 4308/0923 304566/0113811017



## በድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር ሶዶ ዲስትሪክት 002/2015

በደቡብ መንገዶች ባሥልጣን የሶዶ ዲስትሪክት ጽ/ቤት በ2015 በጀት ዓመት በስሩ ላሉ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚሆኑ ተሽከርካሪዎችን ማለትም የጭነት አይሱዙ መኪና እና ሚኒባስ መኪና ብቁ ተጫራቾችን አወዳድሮ መከራየት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም፡-

1. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ የሚያስችለውን የዘመኑን ግብር የተከፈለበትን ከሚፈለገው አገልግሎት የተዛመደ የንግድ የሥራ ወይም የአገልግሎት ሥራ ፈቃድ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ምስክር ወረቀት እና በአቅራቢነት ዝርዝር ውስጥ ተመዝጋቢ ስለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተጫራቾች ዋጋቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ የፋይናንስ ፕሮፖዛሉን በተለያየ ፖስታ በማድረግ አንድ ዋና እና አንድ ኮፒ ‹‹ኦሪጅናል›› እና ‹‹ኮፒ›› በማለት እና የጨረታ ማስከበሪያውንም በተለየ ፖስታ ለብቻው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ደ/መ/ባ/ሶዶ ዲስትሪክት ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 4 ቀርበው መውሰድ ይችላሉ፡፡
4. የጨረታው አሸናፊ የሚወሰነው በጨረታ ሰነዱ ውስጥ በተመለከቱት መስፈርቶች መሠረት ሲሆን ጨረታው መስፈርቱን ለሚያሟላ ለማንኛውም አቅራቢ ክፍት ነው፡፡
5. አቅራቢዎች ጨረታውን ለዚህ ተግባር በተዘጋጀ ሳጥን ገቢ የሚያደርጉበት ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15ኛው የሥራ ቀን ከቀኑ 9፡00 ድረስ ይሆናል፡፡ ጨረታው በዚያኑ ቀን ከቀኑ 9፡30 ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው ባሉበት ይከፈታል፡፡ ዕለቱ የሥራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን ይሆናል፡፡
6. በጨረታው የሚቀርቡ አይሱዙዎች 35 ኩ/ል እና ከዚያ በላይ ፣ እንዲሁም ሚኒባስ 12 ሰውና ከዚያ በላይ መጫን የሚችሉ መሆን አለባቸው፤ የአይሱዙ እና ሚኒባስ ተሽከርካሪዎች የስሪት ዘመን እ.ኤ.አ 2008 እና ከዚያ በላይ መሆን አለባቸው፤ የሁሉም ተሽከርካሪ የነዳጅ ጌጅ እና ኪ/ሜትር በትክክል የሚሰራ መሆን አለበት፡፡
7. ተጫራቾች የሚያቀርቡትን የጨረታ ማስከበሪያ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሠረት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ ውጭ በኢንሹራንስ ወይም በሌላ መልክ የሚቀርብ የጨረታ ማስከበሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡
8. ተጫራቾች በጨረታ ደንብና መመሪያ መሠረት ጨረታውን ማቅረብ አለባቸው፡፡ ከደንብና መመሪያ ውጭ የሚቀርብ ማንኛውም ጨረታ ተቀባይነት የለውም፡፡
9. ዲስትሪክቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
10. ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 0461-804-426 ሶዶ ዲስትሪክት ፋይናንስና ሎጅስቲክስ ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**ደቡብ መንገዶች ባለሥልጣን ሶዶ ዲስትሪክት ጽ/ቤት**